04-204-0005-1000

ርዕሰ: አንገዉ 2002

ማዉጫ

1. ምዕራፍ አንድ - የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ /ትምህርተ ወንጌል በደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ/
2. ምዕራፍ ሁለት - አባ እባቆም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን
3. ምዕራፍ ሦስት - የሴቶች ቅድስና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን
4. ምዕራፍ አራት - ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በምሥጢረ ሥላሴ ምክንያት የተደረገው ክርክር
   - ክፍል 1. የምሥጢረ ሥላሴ ውዝግብ ከ15ኛው ክፍለ ዘመንና
   - ክፍል 2 የምሥጢረ ሥላሴ መለያየት በዋልድባ
   - ክፍል 3 በመምህር አካለወልድና በቤተክህት ባለሥልጣኖች የተፈጠረው አለመግባባት
5. ምዕራፍ 5 የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምሕራን ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በምሥጢረ ሥጋዌ ያሳዩት መለያየት
   - ክፍል 1 ፀጋ
   - ሀ. የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እስከ 16ኛው ፍለ ዘመን ድረስ ምሥጢረ ሥጋዌ ግዕዝ በግዕዝ
   - ለ. በግራኝ የሰለሙትን ኢትዮጵያውያን መመለሱና የዜማ መጻሕፍት መስተካከል
   - ሐ. ከ1595 - 1674 የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን
   - መ. የመጻሕፍት ትርጓሜ በሳንደር
   - ሠ. ፀጋ የሚለው ቃል ለሳማን እንደተሰጠና በየት እንደተስፋፋ
   - ረ. በራስ ጉጉስ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለፀጋ የተደረገ ጉባኤ
   - ሰ. በ4ኛ ዮሐንስ ስለፀጋ
   - ክፍል 2 ቅብአት
   - ሀ. በፋሲል ዘመን ስለቅብአት የተደረገ ክርክር
   - ለ. በአእላፍ ሰገድ /ጻድቁ/ ዮሐንስ የተደረገ ክርክር
   - ሐ. በአድያም ሰገድ ኢያሱ የቅብአቶች ሁኔታ
   - መ. ቅባቶች በርጉም ተክለሃይማኖት ዘመነመንግሥት
   - ሠ. ቅባቶች በአፄ ቴዎፍሎስ ዘመነመንግሥት /1700 - 1703/

From the Library of

ፍሥሐ አጥላው ወለደ ዮሃንስ

መቅድም

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የጸድቃን የሰማዕታትና የሊቃውንት ምንጭ ሆና ያሳለፈቻቸው ዘመናት ብዙ ናቸው። የሦስቱም ክፍሎች ዋና መገኛዎች ገዳማት ነበሩ። ከሰድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተተከሉ ገዳማት አብዛኞቹ በጉዲት ጠፍተዋል። የገዳምነት ደረጃቸውን እንደጠበቁ እስካሁን የሚገኙ ሲኖሩ የገዳምነቱ ደረጃ በስም ብቻ የያዙም አሉ። ካሁኑ የአፋር ክልል አንስቶ ባጠቃላይ ምሥራቁ ኢትዮጵያ ብዙ ገዳማትና አድባራት ከክርስትና እምነት ጋር ከአካባቢው ተሠርዘዋል። ከነዚያ ሁሉ የገዳምነትን ክብሩ እንደጠበቀ የሚገኘው የዓሰቦት ገዳም ብቻ ነው። ደብረአዘሎ፣ ምዝባዕና ሌሎችም በአካባቢው ለነበሩ ገዳማት ምልክት ናቸው።

ከጉዲት በፊት ተተክለውና ከገዳምነት ደረጃ ወርደው ግብሩ ሳይኖር ስም ብቻ ተሸክመው እስካሁን የሚገኙ አሉ። አከሱም አጠገብ የሚገኘው የአቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም በዚሁ ደረጃ ከሚገኙት ገዳማት አንዱ ነው። ይህ ገዳም ለምሳሌነት የተጠቀሰበት ምክንያት ከዋንታዊነቱ በተጨማሪ አንዳንድ ዓለማቀፋዊ ታሪክችን ያሳለፈ በመሆኑ ነው። ከታሪኮቹ አንዱ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ዘአርማንያን የሚጠቀስ ነው። የአቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም በጉዲት ጥፋት ቢደርስበትም ተመልሶ የገዳምነትን ክብሩ ሊጠብቅ ችሎ ነበር።

አቡነ ኤዎስጣቴዎስ የአቡነ ጴንጠሌዎንን ገዳም ይጎበኙ ነበር። ገዳሙን በጎበኙበት ወቅት የገዳሙ አበምኔት አባ ዘኢየሱስ ይባል ነበር። አቡነ አዎስጣቴዎስ ከአባ ዘኢየሱስና ከሌሎችም የአቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም መነኮሳት ልዩ መንፈሳዊ ፍቅር ነበራቸው። አቡነ ኤዎስጣቴዎስ የሚከተሉት የሁለተኛነበት ክብር ተቀባይነትን በማጣቱ ወደአርመን እንደሄዱ ይታወቃል። የሄዱት በዘመነ ዓምደ ጽዮን /1297 - 1327/ ነው። የሳቸውን ዓፅም ይዘ የአርማንያው ኤጲስ ቆጳስ በዘመነ ዮሐንስ አእላፍ ሰገድ /1624 - 1660/ ወደ ጎንደር መጣ። ኤጲስ ቆጳሱ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ እግረ መንገዱ የእስክንድርያን ፓትርያርክ ሲኖዳ ጋር ስለተገናኘ ከሱ ለኢትዮጵያ የተላከና በዓረብኛ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ መጣ። ዮሐንስ አእላፍ ሰገድ የላከውን ደብዳቤ እንዲተረጉም ሲኖዳን ጠራው። አባ ሲኖዳ ደብዳቤውን ከተረጎመለት በኋላ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስን ዓፅም በክብር እንዲያርፍ አደረገ (Guddi Annales Iohannir... P 38)

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስለክርስቶስ በማልጽ እየመሰከሩ ሰማዕትነትን የተቀበሉ አበው መነኮሳት ቁጥር እጅግ ብዙ ነው። የተድባበ ማርያምና አትሮንሰማርያም መነኮሳት በየጊዜው በሚነሱ አረማውያን ሰማዕት ሆነዋል። ከዘመነ ሱስንዮስ ጀምሮ እስከ ፋሺስት ጣልያን ድረስም ብዙ የደብረሊባኖስ መነኮሳት ሰማዕትነትን ተቀብለዋል። ከገዳማት ውጭም ስለክርስቶስ ደማቸውን ያፈሰሱ ኢትዮጵያውያን ብዙ ናቸው።

የግራኝ የመከራ ዘመን አልፎ ብዙ ሳይቆይ ጉር የተባለው አረመኔ በ1551 ዓ.ም ከቡልጋ ጀምሮ በምሥራቅ ሸዋ የነበሩት ክርስቲያኖች እልቂት ሲሰሙ አፄ ገላውዴዎስ ሊታደጉት ሄዱ። በዚያውም በዕለተ ስቅለት አንገታቸው ተቆረጡ። ከሳቸው ጋር እጨጌ ዮሐንስ፣ አባ ተክለማኅበር፣ አባ

ሠርዛድንግል፣ አባ ኃይለመለኩት፣ አባ መቃርስ፣ አባ አሜር፣ አባ ሀምረአብና አባ ሰሥላሴ ከንጉሡ ጋር ሰማዕትነትን ተቀብለዋል። የነሱ ሰማዕትነት ለአገርም ለሀገተክርስቲያንም ቋሚ ሐውልት እንደሆነ ይኖራል።

ቅድስናን ከመምሕርነትና ከብሕትውና ጋር አስተባብረው በመጠበቅ ይህን ዓለም ያለፉት ኢትዮጵያውያን ስም ዝርዝርዝ ለመግለጽ መሞከር፣ ውቅያኖስን በጭልፋ እንደማለት ያስቆጥራል። የዛሬን አይበለውና ገዳማቱ ሁሉ ብዙ ቅዱሳንን እያፈሩ ነው ያለፉት።

የወንዶችን ያህል አይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሴቶችንም በቅድስና አሰልፋ መንፈሳዊ ድርሻቸውን እንዲወጡ አድራጋለች። ሌላ ቀርቶ የነገሥታት ሚስቶች ሆነው እያለ መልካም መንፈሳዊ ሐውልትን ተክለው ያለፉ ኢትዮጵያውያት ሴቶች ጥቂቶች አይደሉም መስቀል ክብራ በዚሁ ትጠቀሳለች። እሷ የላሊበላ ሚስት ናት ዓረባዊው የቅብጢ ጸሐፊ መስቀል ግብሪት ብሏታል። የላሊበላ ገድል መካን እንደነበረች ያሳያል። በግብፃዊው ምንጭ ላሊበላ ሁለት ልጆች እንደነበሩት እንረዳለን። ከመስቀል ክብራ መወለዳቸውን ግን ግልጽ አላደረጉም ይትባረክ ከሷ መወለዱን እንዳንድ አፈታሪኮች ይናገራሉ።

ይትባረክ የአክሱም ጽዮን ቄሰገበዝ የከርስትና ልጅ ስለሆነ ክሕግንነቱ ጀምሮ በአክሱም እየተማረ ነው ያደገው። በላሊበላና በሐርቤ መካከል ጠብ ሲነሳ ከባልዋ ጋር አብራ መሰደድዋ ታውቋል። ላሊበላ ወደኢየሩሳሌም በሄደ ጊዜም አክሱም አጠገብ ከሚገኘው መደባይ ሄዳ ተቀመጠች። ከኢየሩሳሌም ሲመለስ አብራው ተመልሳ በእተጌነት ልትቆይ ቻለች። አሥራ አንዱ ቢተመቅደሶች ሲሠሩ ከፍተኛ የአመራር ተሳትፎ ነበራት ላሊበላ ሲሞት እንደገና ወደመአባይ ተመልሳ በጸም በጸሎትና በአስተብርኮ ተጠምዳ ከቆየች በኋላ ስትሞት በዚሁ ተቀብራለች ታቦትም ተቀርፆላታል። መታሰቢያዋ ሐምሌ 6 ቀን ይከበራል። /ሥንክሳር በሩ ሥላሴ አምባሰል ወሎ/

ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተነሱ እውቅ መምህራን ጥቂቶች አይደሉም። ከሊቅነታቸው ሙሉነት የተነሳም "ልቄ" የሚል የመዓረግ ስም እየተሠጣቸው ችሎትን ይመሩ ነበር። ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረው የዚህ ባለሞያዎች ናቸው። እነሱም

1. ልቄ ክፍለ እኒህ የቤተክርስቲያን ምሑር ከ32 ዓመት ላላነሰ ጊዜ በመንግሥት ችሎት አገልግለዋል። የተወሰነባቸውን ፍርድ አልቀበልም ያሉት ወንድም ይሁን ሴት በአደባባይ እንዲገረፉ ይደረግ ነበር። ልቄ ክፍሌ ግርሩቱን አስቀርተው ቅጣቱ ባንድ ቀን ጸም ማደር /ራት መከልከል/፣ ከትምባሆ፣ አጣሺነትና ከመደብ ወይም ከአልጋ ላይ መተኛት ለተወሰኑ ቀናት እንዲከለከል በማድረግ ለውጠውት ነበር (EMML 8732 ቅጠል 62r - 67r)
2. በአፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ (1723 - 1747) ብዙ ልቄዎች ነበሩ። ልቄ ተክለሃይማኖት፣ ልቄ ነሮ፣ ልቄ ኢሳያስ፣ ልቄ በትሬ፣ አዛዥ ባሕርይ፣ አዛዥ ቴዎዶስዮስ ከነሱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚያ ወዲህም በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እነልቄ ከኮበልዳ ነበሩ።
3. በ4ኛው ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ልቄ መርዓዊ የፍትሐነገሥት ኃላፊ በመሆን እገልግለዋል። ልቄዎዎች በሙሉ የ4ቱ ጉባኤያት ሊቃውንት ከመሆናቸውም በላይ ልዩ ተሰጥዎ ያላቸው፣ ምሥጢራትን የመተንተን ችሎታ ያላቸው ናቸው። አፄ ዮሐንስ ሲሞቱ ልቄ ምርዓዊ ወደ ትውልድ ቦታቸው ቅስናዋ /ፋርጣ/ ሄደው ተቀ[illegible]ጡ። የደብሩ አለቃም ሆኑ የአካባቢው ሕዝብ ነሐሴ አሥራ ሁለትን እክብሮ ነሐሴ አሥራ ሦስት /የደብረ ታቦር ዕለት/ ሲያርስ አይተው አሥራ ሁለትን አርሳችሁ፣ አሥራ ሦስትን ብታከብሩ ይሻላል፣ ስላሉ መናፍቅ ተብለው አካባቢውን የአስተዳድሩ ከነበሩት ራስ ዘውዴ ዘንድ ተከሰሱ። የተከሰሱበትን ነገር እምነት ክህደት ቢጠየቁ ብያለሁ አሉ።

ራስ ዘውዴ ለምን ይህን ተናገሩ ቢሏቸው ከርስምና ከአፄ ምኒልክ ማን ይበልጣል ሲሉ የጥያቄ መልስ ጠየቁዋቸው /ገዝውን/። እሳቸውም አፄ ምኒልክ አሉ። ልቄ መርዓዊ ከሚካኤልም ጌታ ይበልጣል አሉ። ራስ ዘውዴ "እንዲያውስ እርስዎ ይጠየቁ ነበር እንጂ ይከሰሱ ነበር?" በማለት ይቅርታ ጠይቀውና ካሣ ከሰው ወደ ቀስጥና መለሱዋቸው።

መምህር ኢስድሮስና ዓቃቤ ሰዓት ከፍቴም በሊቅነታቸው ዝናን ያተረፉ ናቸው።

ሀ. መምህር ኢስድሮስ - መምሕር አስድሮስ የተወለዱበት ዓመተ ምሕረት በውል አልታወቀም። በ18ኛው ክፍለ ዘመን መነሳታቸው ግን ተረጋግጧል። የትውልድ ቦታቸው ተምቤን ነው። ከተወለዱ ብ30 ቀናቸው በፈንጣጣ ሁለቱ ዓይኖቻቸው ጠፉ። ግን አራት ዓይና ኢስድሮስ ይባላሉ። አራት ዓይና የሚል የቅጽል ስም መስጠት የተጀመረው በሳቸው ነው። በኋላ እነአለቃ ጎሹም አራት ዓይና ተብለዋል።

መምህር ኢስድሮስ በሕግንነታቸው ተምቤን ውስጥ አባ ሐደራ ወደተባለው ገዳም ገብተው ትምህርት ጀመሩ። የዜማ ነክ የሆኑትን ትምህርቶች አቋቋምን ጨምሮ በዚሁ ገዳም አጠናቀው ተማሩ። ከቅኔ ጀምሮ አራቱን ጉባኤያት በአክሱም አጠናቀቁ ዓራት ዓይና የሚል የቅጽል ስም የተሰጣቸው አክሱም ላይ እያሉ ነው። የተማሩዋቸውን የትምህርት ዓይነቶች በሰዓታት እየከፈሉ በማስተማር በአክሱም ለተወሰኑ ዓመታት ቆይተዋል። ከየገዳማቱና አድባራቱ እየመጡ ሞያቸውን ለመቅሰም የሚኮለኮሉ ምሁራን ስፍር ቁጥር አልነበራቸውም ይባላል። ተጠይቀው በሚሰጡት መልስ የማይደሰት እንዳልነበረም ይነገራል። አንደ ምሑር የውጭ ዜጋ ጠይቋቸው በሰጡት መልስ እጅግ እንደተደነቁ በታሪክ ተመዝግቧል።

በዘመነ ጎንደር የተተረጎሙትን መጻሕፍት አንድ ባንድ መርምረው የግስቲካክል እርምት አድርገውላቸዋል። ይህን ያከናወኑት በጣና ደሴት ሆነው ነው የግዕዝ በግዕዝ ትርጉም የያዙት መጻሕፍት የሚያሳዩት የንትሩስ ዮሐንስ አፈወርቅ አተረጓጎም በግብራራት ላይ ያተኮረ እንጂ አንድምታ ወይም ረጅም ሐተታ የለውም። በዚሁ መንገድ የአራቱ ወንጌላውያን ወንጌል፣ በአፄ

ልብነ ድንግል /1500-1542/ የተተረጎመ ባሕርዳር ጊዮርጊስ፣ በአተረጓጎሙ ተመሳሳይነት ያለው ነገር ግን በግን ዘመን እንደተተረጎመ የሚያታወቅ አንድ ትርጓሜ ወንጌልና የጳውሎስ መልእክታት በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም እስካሁን ይገኛሉ።

መምህር ኤስድሮስ በነዚህ ገዳማት የሚገኙት ጥንታውያን የመጻሕፍት ትርጓሜዎች መነሻነት የአንድምታውን ትርጓሜ ለማታናት በጣና ደሴቶች ዓመታትን አሳልፈዋል የሳቸውን አዲስ አቀራረብ ትምሕርት ብዙዎቹ በደስታ ተቀብለውታል። አንዳንድ ተቃራኒዎች ግን አልጠፉም የሳቸውን አዲስ አቀራረብ እንደመሰሰን የቆጠሩት ነበሩ።

ትምሕርቱንም ሲያጥላሉ "...ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት" "ከመልሰን በፊት የተወለድን ነን..." ይሉ ነበር የተሻሻለውን ትምሕርት ከተቀበሉት ፅውቅ መምሕራን መካከል ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ አንዱ ናቸው። እኒሁ መምሕር አራቱን ጉባኤያት ከለሎች አጠናቀውና ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩ በኋላ ከመምሕር ኤስድሮስ ዘንድ ገብተው ሞያቸውን አሻሽለውታል። የዓቃቤሰዓት ከብቴ ታሪክ በሚቀጥለው ይገለጻል።

የመምህር ኤስድሮስ የትርጓሜ ትምሕርት ወልደአብ፣ ወልደሚካኤል፣ መምሕር አካለወልድ፣ በዜናማርቆስ ገዳም። አስተማሪ የነበሩት መምሕር ወልደ ሚካኤልና አቡነ ይስሐቅ ሌሎችም የመምሕር ኤስድሮስን የትርጓሜ መንገድ የሚከተሉ ነበሩ። የኢትዮጵያ የትርጓሜ መጻሕፍት መምሕራን የመምሕር አሳድሮስን ሊቅነት ሲገልጹ "የመምሕር ኤስድሮስ የትርጓሜ መንገድ እንዲህ ይላል" እያሉ ይጠቅሱታል።

ሀ. በግራኝ ቃጠሎ የተቆነጻጸሉትን መጻሕፍት ንባብና ትርጓሜአቸውን አቃንተው እንዲጸፉ በማድረግ ተጨማሪ መልካም ሥራ ሠርተዋል። ብላቴን ጊታሕሩይ ወልደ ሥላሴ ከግራኝ በኋላ ብዙ መጻሕፍት ንባበቸውና ትርጓሜአቸው ጠፍቶና ተዛብቶ ከቆየ በኋላ መምሕር ኤሳድሮስ በየቦታው እየተዘዋወሩ አቃንተውታል፤ ዛሬ የመምሕር ኤስድሮስ ትርጓሜ እጅግ የተወደደ ሆኖ በየደብሩ ይነገራል በማለት የሕይወት ታሪክ በሚል መጽሐፋቸው በገጽ 59 ገልጸዋል።

መምህር ኤስድሮስ የቀባትን እምነት ለመቀበል ሞክረው ነበር ይባላል። በኋላ ግን አጥብቀው የሚቃወሙት ሆነዋል። በእፄ ኢዮአል (ኢየሱስ ሞአ) ካይላሚዳ ላይ በ1756 ዓ.ም በተጠራው አካላዊ ቃል ከሥጋ ጋር ተዋሕደ የመንፈስ ቅዱስን አክባሪነትንም ተቀብሎ የኛ ሊቀ ካህናት /በኩረ ምዕመናን/ ሆነ የሚል እምነትም በሳቸው ጎልቶ ይነገር ነበር ይባላል።

(I Guidi Annalise Regum Iyasu II Iyaar csco ...(Paris, 1910)፣ ሕሩይ ወልደሥላሴ የሕይወት ታሪክ /አዲስ አበባ 1918 /...The Royal Church of Abysinia 1769-1840 ፤ ድምፀ ተዋሕዶ መጽሔት ቁ. 24 /1972 ዓ.ም/

ለ. ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ ትውልድ አገራቸው ጋይንት ውስጥ ዙራምባ ገዳም አካባቢ ነው። ወላጅ አባታቸው የአራቱ ጉባኤያት መምሕር ነበሩ። ስማቸው መምሕር ሕዝቅያስ ይባላል። ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ ከወላጅ አባታቸው አልተማሩም። ጎንደር ከተማ ውስጥ ከሚገኘው ኔደባባይ ተክለሃይማኖት ከነበሩት መምሕር መልከጼዴቅ ዘንድ ነው የተማሩት። አራቱን ጉባኤያት ካጠናቀቁ በኋላ ወደአትሮንሰ ማርያም ሄደው ቅኔን ተማሩ።

አትሮንሰማርያምና ተድባበማርያም የአማራ ላይንት አካባቢዎች ሲሆኑ የጥንት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ማዕከሎች ከነበሩ እውቅ ገዳማት መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ እንደያዙ የነበሩ ናቸው። ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ አትሮንሰ ማርያም በነበሩበት ጊዜ ሦስት ልደት የፀጋ ልጅ የሚለውን ባሕል ዘሙሉ ልብ ተቀብለውት ነበር። ወደጎንደር ተመልሰው ይህን ትምሕርት አስፋፍተውታል። ከደብረብርሃን ሥላሴና ከአንዳንድ ሌሎች አድባራት በቀር አብዛኞቹ የጎንደር መምሕራን ተቀብለውት ነበር። ይህን በተመለከተ የሚነበብ አጭር የግዕዝ ጽሑፍ እንዲህ ይላል። /... ወበዘመኑ ተንሥኡ ዓቃቤሰዓት ከብቴ ወቂስ አፄ ገብረመስቀል ወአምፅኡ ሃይማኖተ ዘትሰመይ /የፀጋ ልጅ/ ወገብሩ ሁከተ እንዘይሜህሩ ዘንተ ትምሕርተ /በዘመኑ ዓቃቤ ሰዓት ከብቴና ቂስ አፄ ገብረመስቀል ተነስተው "የፀጋ ልጅ" የሚል ትምሕርት ያለበትን ሃይማኖት አመጡ። ትምሕርቱንም በሚያስተምሩበት ጊዜ ሁከት ተነሳ/ ።

አፄ ተክለጊዮርጊስ ተፍፃሜተ መንግሥት /1770 - 1772/ ሲነግሡ ከደብረምጥማቅ አለቅነት ጋር ዓቃቤሰዓትነትን በአዋጅ ሹመዋቸዋል። ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ ለአጸዋማትና ለበዓላት "ሥፍር ሰዓት" የሚል ሠንጠረዥ በማዘጋጀታቸውም ይታወቃሉ። እንደገና በ1789 ዓ.ም የጎንደር በአታ አለቃ ሆነው ተሾመው ነበር። በ1894 ዓ.ም ዓረፉ። ደብረመንክራት ወረታ ቅዱስ ጊዮርጊስ ላይ የሚገኘው ሃይማኖተ አበው "ሠርቀ ጥቅምት በዝ ወርሕ ሞተ ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ አዛል ብእሲ..." በማለት ታሪካቸውን ያወሳል።

ለብዙ ምዕት ዓመታት በአበው ሊቃውንት መነኮሳት ተጠብቆ የኖረው አንድነትን የተላበሰ የቤተክርስቲያን ትምሕርት በጎንደር ዘመነ መንግሥት ብዙ ችግሮች ተጋረጡበት። ትህትናው ቀርቶ በ44ቱ አድባራት የተተከሉ ካህናት እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚል ከመንፈሳዊ ሥነ ምግባር ውጭ የሆነ እንቅስቃሴ ነገሥታቱንም ላይቀር ግራ አጋቡዋቸው። በቤተክርስቲያን ላይም ከፍተኛ ድክመት ተከሰተ። ቀባት ካራና ፀጋ የሚሉ ቃላት የውድድርና የመከፋፈል ሰያሜዎች ሆኑ። መንፈሳዊ የቤተክርስቲያን ፍቅር ጨርሶ ተረሳ።

መግቢያ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ እቅፎ የያዛቸው ቁም ነገሮች በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም እጅግ ብዙ ናቸው። ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ለሦስት በመክፈል አንባቢያን መጠነኛ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ተሞክሯል። በዚሁ ጽሑፍ ደግሞ ከ16ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ያሉትንና ምንነታቸውን ለመረዳት የተቻሉት ብቻ በዚሁ ጽሑፍ ይገለጻሉ። ብዙ ምሑራን እንደሚያምኑበትና አዘጋጂውም በየአጋጣሚው ለመግለጽ እንደሞከረው ታሪክ የውቅያኖስ ያህል ጥልቀት ያለውና አካሄዱም እጅግ የበዛ ነው።

የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ከ12ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በክፈልም ቢሆን ክርስትና ተሰብኩላቸው ነበር። የመጀመሪያው የዚሁ አካባቢ ሐዋርያ አቡነ ተክለሃይማኖት መሆናቸው የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። ከእሳቸው በኋላ የአቡነ ዜና ማርቆስ ሐዋርያነት በአካባቢው ተንጸባርቋል። የእሳቸው ሐዋርያነት በምድረጉራጌ ላይ ያተኮረ እንደነበር ይነገራል።

ከአፄ ዘርአያዕቆብ በፊት የተነሱት አፄ ይስሐቅ በነአቡነ ዜናማርቆስ ተስፋፍቶ የቆየው እምነተክርስትና እንዳይዳከም መምህራንን በአካባቢው መመደባቸው ይታወቃል። ከግራኝ ጥፋት በኋላም የተወሰኑ ነገሥታት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በአዲስ መልክ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ድጋፍ ይሠጡ ነበር። በዚሁ ከፍተኛውን ሥፍራ የያዙት አፄ ሠርፀድንግል ናቸው። አጼ ሱስንየስ /የካቶሊክን እምነት ከመከተላቸው አስቀድሞ/ና አፄ ኢያሱ አድያምሰገድም በዚሁ አካባቢ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ተመዝግቧል።

በግራኝ ዘመንና ከግራኝ ዘመን በኋላ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሐዋርያዊ ተልእኮ ያከናውኑ መምህራን ቤተክርስቲያን ታይተዋል። ዕጨጌ ዕንባቆም ለዚሁ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። ቁጥራቸው ከቅዱሳን ውስጥ የሆኑ ሴቶችም በኢትዮጵያ ተነስተው ነበር። ለአስረጂነት በዚሁ ጽሑፍ የሁለት ቅዱሳት ሴቶች ታሪክ ተገልጿል። እነሱም ማርያም ሳይንትና ወለተ ጴጥሮስ ይባላሉ።

የመጽሐፉ ዋና ክፍል የያዘው ቅባት ካራና ፀጋ በሚል ስያሜ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካህናት የተለያዩበት ምክንያት ነው። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት አለመግባባትም በኢትዮጵያ ተነስቶ ነበር፣ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በደብረቢዘን እንደተጀመረ ሲነገር ሁኔታው ቀስ በቀስ የቤተመንግሥት ጉዳይ ሆኖ ነበር። አፄ ይስሐቅና አፄ ዘርአያዕቆብ የምሥጢረ ሥላሴን ጉባኤ እንዲካሄድ አድርገው ነበር። የዋልድባ መነኮሳት ለብዙ ምዕት ዓመታት በዚሁ ትልቅ የዶግማ ክፍል መግባባት ሳያገኙ ኑረዋል። መለያየታቸው ይፋ የወጣው ግን ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ነው። የነሱ መለያየት እነ መምህር አካለወልድ በተካፈሉበት የደሴ ላይ ጉባኤ ታይቷል። ከዚያ በተያያዘ መልኩ የተፈጠረው ውጣ ውረድ እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ ቀጥሎ ታይቷል። ከምሥጢረ ሥላሴ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በምሥጢረ ሥጋዌ መለያየት ለሦስት ምዕት ዓመታት ስትታመስ ኑራለች። የምሥጢረ ሥጋዌ መለያየት የተጀመረው በ17ኛው ክፍለ ዘመን ነው። አጋ በሚለው ቃል አለመግባባት መፈጠሩ ባይካድም በዚሁ ምክንያት ጉባኤ የተካሄደው በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው። ጉባኤውን የጠሩት ራስ ጉግሣ /1791 - 1818/ ሲሆኑ ጉባኤው የተካሄደውም በደብረታቦር ነው። ጉባኤው ያለውጤት ተበትኗል። በ4ኛው ዮሐንስ መሪነት የካሄደው የቦሩ ሜዳ ጉባኤም አጋን የተመለከተ ነበር። አፄ ዮሐንስ በአንዳንድ ምሁራን ላይ የኃይል ርምጃ ሲወስዱ እነመምህር አካለወልድ በዝምታ ስለተመለከቱ ግብዝነትን አሳይተዋል እየተባሉ ይታሙበታል። በጉባኤው አፈጻጸም መልካም ታሪክ ያተረፉ እጨጌ ቴዎፍሎስ ናቸው።

ከዘመነ ሩሲለደስ ጀምሮ ብዙ ችግር እያስከተለ የኖረው ቅብአት የተባለው ክፍል ነው። በአፄ ፋሲለ፣ በጻድቁ ዮሐንስ፣ በአፄ ኢያሱ አድያምሰገድ፣ በአፄ ተክለሃይማኖት /ርጉም ተክለሃይማኖት/፣ በአፄ ዳዊት /ዘፋኝ ዳዊት/ና በአፄ ቴዎፍሎስ ዘመን ስለቅባት ጉባኤዎች ተደርጓል። አፄ ኢያሱ አድያምሰገድ መምህራኑ ቤተክርስቲያን ትክክለኛውን የቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢር መሠረት አድርገው እንዲወያዩበት ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ አመቻችተው ነበር። ነገር ግን በሰተኋላው ፖለቲካዊ ይዘት ስለነበረው የመገዳደልና የመለያየት ምክንያት እንደሆነ ለዘመናት ቆይቷል። ምሥጢረ ሥጋዌን በተመለከተ ያለመጣጣም የተከሰተው ባልተለመደ ሁኔታ ቅዱሳት መጻሕፍት በአማርኛ ቋንቋ ትንታኔ እንዲደረግላቸው ሲጀመር ነው።

ምዕራፍ አንድ

ክርስትና በኢትዮጵያ
የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ
ምዕራፍ አንድ ትምሕርተ ወንጌል በደቡብና
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ

በደቡብ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትናን ያስፋፉ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ብቻ እንደሆኑ ይነገራል። ሰፊ ጥናት አለመደረጉ እንጂ ከሳቸው በፊትም በአካባቢው የሐዋርያነት ተልእኮ ያከናወኑ ሊኖሩ ይችላሉ። በወላይታና አካባቢው ከሦስት መቶ በላይ አድባራት መኖራቸው ይታወቃል። ከአድባራቱ መካከል አብዛኞቹ የአቡነ ተክለሃይማኖትን ታሪክ የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ከአቡነ ተክለሃይማኖት በኋላ በደቡብ ክፍል ለትምህርተ ወንጌል የተንቀሳቀሱት አቡነ ዜናማርቆስ ናቸው። የአቡነ ዜናማርቆስ ሐዋርያዊ ተልእኮ በይበልጥ ያተኮረው ወደምድረጉራጌ ነው። አቡነ ዜናማርቆስ ክርስትናን የማስፋፋቱ ተግባር በሳቸው እድሜ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር አላደረጉም በሕይወት እያሉ ደቀመዛሙርቶቻቸው የሳቸውን ፈለግ ተከትለው ወንጌልን በምድረ ጉራጌ እንዲያስፋፉ አድርገዋል። አቡነ ዜና ማርቆስ የስብከት ማዕከላቸው ያደረጉት ምሑር የተባለውን ቦታ ነበር። በዘመናቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ጳጳስ ባለመኖሩና እሳቸውም የክህነት መዓረጋቸው ዲቁና ስለነበር አስተምረው ያሳማኑቸውን ምዕመናን ለማጥመቅ ይችሉ ዘንድ ቅስናን ለመቀበል እስከንድርያ ድረስ ሄደዋል። ገርዳን በተባለው አካባቢም ብዙዎቹን አሳምነው አጥምቀዋል ያካባቢው ገዢ የነበረውና "ቀልብግን" በመባል የሚታወቀውን አጥምቀው ገብረማሲሕ ብለውታል። በምሥራቀ ኢትዮጵያ አካባቢም

ሐዋርያዊ ተልእኮ አከናውነዋል። የምረቱን ገዝ አሰግድን አጥምቀው ስመ ክርስትናውን ማርቆስ ብለውታል። እንደዚሁም የአዳልን ሕዝብ አስተምረው ከገዥያቸው ዓብደል ማልጋር አጥምቀዋቸዋል።

ጻድቁ ወደምሑር ተመልሰው ብዙ አብያተክርስቲያናትን አሳንጸዋል ደቀመዛምርቶቻቸውንም በአካባቢው አሰማርተዋል የነበሩበት ከፍለ ዘመን በትክክል ተመዝግቦ አልተገኘም ይሁን እንጂ በ14ኛው ክፍለ ዘመን እንደነበሩ የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች አሉ። ማሕሌተ ጽጌን የደረሱ አባ ጽጌ "ትወፅዕ በትር እምሥርወ እሴይ ወየዓርግ ጽጌ እምኔሃ" የሚለውን የኢሳይያስ ትንቢት በጥሩ ሁኔታ ተረጉመውልኛል ብለው አቡነ ዜናማርቆስን ያመሰገኑበት ንባብ ከገድላቸው ይገኛል። አባ ጽጌ ድንግል በ14ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ናቸው።

አጼ ይስሐቅ በ15ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ በአቡነ ዜናማርቆስ የተሰፋፋው የክርስትና ሃይማኖት እንዲቀጥል ማድረጋቸው ይነገራል። አፄ ይስሐቅ ከ1399-1414 ዓ.ም የነበሩ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ናቸው። ስለፈጸሙት ተግባር ዝርዝር ሁኔታ ግን ለማግኘት አልተቻለም። ክግራኝ ወረራ በኋላ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት የክርስትና ሃይማኖትን መሠረት አድርገው ክምድረ ጉራጌ እስከጅማ ድረስ ተንቀሳቅሰዋል በዚህ የሚነገርላቸው አፄ ሠርፀ ድንግል ናቸው። ዜና መዋዕላቸው እንደሚያስረዳው አፄ ሠርፀ ድንግል ከ1555 - 1588 ባለው የዘመነ መንግሥታቸው ጊዜ ከጉራጌ እስከ ጅማ እየተመላለሱ ነዋሪዎቹ ትምርሕርቱ ወንጌልን የሚያገኙበት መመርያ አውጥተው ተክተለዋቸው ያሄዱትን መምህራን በየክፍሉ በመመደብ ቋሚ ትምሕርት ቤትም እንዲኖር አድርገው ነበር።

በባለባትነት የነሳ መሪነቱ ይታወቅ የነበረው "ባሻሹም" በተሠጠው ትምሕርት ደስተኛ ሆኖ ክርስትናን መነሳት ስለፈለገ አፄ ሠርፀድንግል በተገኙበት ሚያዚያ 23 ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ ክብረ በዓል በሚካሄድበት ዕለት ተጠመቀ የክርስትና ስሙም ጊዮርጊስ ተባለ። አፄ ሠርፀድንግል እሱንና ወገኖቹን የሚያስተምር ካህን መድበውለት ሲያበቁ ሌሎችንም ተመሳሳይ ተልእኮዎች እያከናወኑ ቆይተው ወደመንበረ መንግሥታቸው ተመልሰዋል። አፄ ሠርፀ ድንግል ያሳነጹዋቸው አድባራት እስከአሁን ይታወቃሉ። በነማን እንደተተከሉ ያልታወቁ ብዙ አድባራትና ገዳማት ከደቡብ ምዕራብ እስከ ደቡብ ምሥራቅ የኢትዮጵያ ክፍል መኖራቸው ይነገራል። በጅማና አካባቢው ከዘመን ብዛት የተነሳ አጠራራቸው ጥቂት ለወጥ ብሎ የሚጠቀሱ አሉ። የጅማ አዋሳኝ ሁኖ ጋሮ በመባል የሚታወቀው ቦታ ከእነሱ አንዱ ነው። በዚሁ ክፍል አድራባትን ግራኝ እንዳልነበሩ አድርጓቸዋል። አፄ ሠርፀ ድንግል ወደነዚህ ቦታዎች የደረሱ አይመስልም ከግራኝ በኋላ አንድም አስተማሪ እንዳልነበኖቸው ብቻ ነው የሚገለጸው። ማራ የተባለው ቀበሌ የመድኃኔዓለም ደብር አዶ በተባለው ቀበሌ የተከለሃይማኖት ደብር፣ ዴታ በተባለው ቦታ የገብርኤል ደብር፣ ሌሎችም የእመቤታችንና የጊዮርጊስ አድባራት እንደነበሩ የሚጠቅሙ ምልክቶች ይታያሉ። ምልክታቸው ጠፍቶ የቀሩ ሌሎች አሥራ ሁለት አድባራትም እንደነበሩ ያካባቢው ሕዝብ በአፈ ታሪክ መልክ ያቀርበዋል።

በግራኝ ወረራ አብያተክርስቲያናቱ ቢያጠፋም ክርስቲያናቹ አልጠፉም ነበር፤ ያለ ማንም አስተማሪ ለብዙ ዘመናት እምነታቸውን እንደጠበቁ ኑረዋል። በኋላ ግን ከፋዎች አካባቢያቸውን በመውረር አስገድደው የእስልምናን እምነት እንዲቀበሉ አደረጉ፤ ከፋዎች በ1863

ዓ.ም ነው የወረሩዋቸው። ያም ሆኖ ክርስቲያንነታቸው ለብዙ ምዕት ዓመታት የኖረ በመሆኑ የክርስቲያንነት ምልክታቸው አሁንም እንዳንጸባረቀ ነው። ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር በተያያዘ አኳኋን ጋሮ አማራ እየተባሉ ይጠሩ ነበር። ይህ ስያሜ እስካሁን በነሱ ዘንድ አለ። ጋሮ አማራ ማለት በአሮምኛ ጋሮ ተብሎ በሚጠራ ቦታ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ማለት ነው። በአንዳንድ የአሮምኛና አማርኛ ተናጋሪዎች እስላምና ክርስቲያን ለማለት እስላምና አማራ ይባላል። /ጋሮ አማራ የሚለው ቃልም ይህንኑ ያመለክታል። በጋሮ አማራ ስያሜ የሚጠሩ ብሔረሰቦች አሁንም አሉ ግን የሰልምና እምነት ተከታዮች ናቸው። ይሁን እንጂ ብዙ የክርስትና እምነት ባሕሎች በነሱ ዘንድ ይታያሉ፤ ረቡዕና ዓርብ ይጾማሉ፣ ወንድ ልጅ ሲወለድ በ40 ቀኑ ወደዋሽው ይወስዱትና በኩስኩስት በተቀዳ ውሃ እንዲጠመቅ ይደረጋል።

ከመካከላቸው የካህን ዘሮች እንደሆኑ የሚነገርላቸው ወገኖች አሉ፣ ከነሱ ውስጥ አንዱ ተንበርክኮ በመጸለይ በቀረበው ውሃ ሕፃኑን ያጠምቀዋል። ሕፃናቱን የሚያጠምቁበት ዋሽ በግራኝ ወረራ ዘመን ታቦታት ተደብቀውበት የነበረ ነው። ታቦታቱ በከሰል ላይ ተሸፍነው እንደተቀመጡ ይነገራል፣ ይህ የሆነበት ምክንያት ከዘመን ብዛት ብልሽን እንዳያደርስባቸው ነው። ከጋሮ አማራ መካከል የቁስ ዘር የሆነው ዋሻውን ይጠብቀዋል።

እነዚህ የቁሶች ዘሮች ከጥንት አባቶቻቸው የተላለፉትን መጻሕፍት ጠብቀው ይኖራሉ። ንጉሥ ወልደጊዮርጊስ አካባቢውን በነበጁበት ወቅት ብዙ መጻሕፍትን አግኝተዋል። ኪዚያ በኋላም በ1912 ዓ.ም የቁሶቹ ዘር የሆነውና አባጋዲ በመባል የሚታወቀው ያካባቢው ተወላጅ ኖሳ በተባለው ሥፍራ ተቀብረው የኖሩትን አርጋኖን፣ ውዳሴ አምላክና አረመርት ተአምረ ማርያም የቤተክርስቲያን መጻሕፍት አምጥቶ ለመንግሥት ማስረከቡ ይታወቃል።

አባጋዲ ጥንታውያን አባቶቻችን ይከተሉት የነበረውን የክርስትና እምነት እኔና ወገኖቼ ለመከተል እንፈልጋለን፤ ቤተክርስቲያን ይሠራልን። ስላለ በአዬ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ በእመቤታችን ስም የሚጠራ ቤተክርስቲያን ተተክሎላቸዋል። ቤተክርስቲያኑ የተተከለበት ቦታ ሐረቤ ይባላል። የአካባው ሕዝብ ለሰባት ዓመት ያህል አምልኮተ እግዚአብሔርን ሲፈጽምበት ከቆየ በኋላ ቃለ እግዚአብሔር እንዳይነገርና እግዚአብሔር እንዳይመለክ የሚፈልጉ ምቀኞች ቤተክርስቲያኑን አቃጠሉት። አባጋዲ ቤተክርስቲያኑ ከመሠራቱ ቀደም ብሎ ከ130 ወገኖቹ ጋር በ1915 ዓ.ም ተጠምቋል። የተጠመቀውም አዲስ አበባ በሚኖረው በቦካ ደብረሣህል ቀጭስ ሚካኤል ነው። የሱ የክርስትና እምነት ቀናኢነት ያላስደሰታቸው ሙቀኞች አባጋዲን ብዙ ሳይቆይ ገደሉት። /2/

ከአቡነ ዜናማርቆስ በኋላ በምድራችን ለብዙዎቻችን እንግዳ እንዳንቀሰቀሱ የምባገኘው ማለፊያ አጥጋቢ አይደለም። በነጋቹው ከፍል ዘመን አዬ ቀሲል አካባቢውን እንደነበሩ ዜና ምኞዳቸው ያስረዳል። በአካባቢው የተንቀሳቀሱት ንቅናቄ ከመሠናቸው በፊት ነው። አካባቢውን ያስተዳድር የነበራውንና ሰዱ የሚባለውን በመተት ወንቀውታል። ከሱ በኋላ ወይምድሬ አቦሞ መሄዳቸው ተገልጿል። ቀደም ሲል በዚሁ ከልል ስለቤተክርስቲያን አንዳንድ ነገሮች ማከናወናቸውን የሚጠቁሙ ምልክቶች በአቦምዶ አካባቢ አሁንም ተጠብቀው ይገኛሉ። ምዕራብ ጃሞ ሙሰጥ በአቀማመጡና በአካባቢው ልምላሜ እጅግ የሚማርክ ሐይቅ አለ። ሐይቁ ውንጭ ይባላል። በሐይቁ

መካከል የቂርቆስ ቤተክርስቲያን ይገኛል። በቤተክርስቲያኑ የሚገኘው ደወል የአፄ ፋሲል ስም ተጽፎበታል።

አፄ ኢያሱ አድያምሰገድ ከደቡብ እስከ ጅማ ጉብኝት ማድረጋቸው ይነገራል። ስለሃይማኖት በዚሁ አካባቢ ምን እንደሠሩ ግን አልተመዘገበም ምድረ ጉራጌን ጨምሮ የምዕራቡና የደቡብ ክፍል ከማዕከላዊ መንግሥስትጋር የነበረው ግንኙነት ከ17ኛው መጀመሪያው አጋማሽ ጀምሮ እንደተቋረጠ ይታመናል። የጉራጌ ሕዝብ ከርስቲያን ሆኖ እያለ አስተማሪ አለማግኘቱ የታወቀው በአፄ ዮሐንስ ዘመን ነው። ተወላጅነታቸው ከብሔረ ጉራጌ የሆነ አንድ መነኩሴ ስለ ጉራጌ ሕዝብ ክርስቲያንነት ለአፄ ዮሐንስ ገለጹ። መነኩሴው በብሔራቸው አባ ጉራጌ ይባሉ ነበር። /3/ አፄ ዮሐንስ ሕዝቡን እንዲጎበኙ አፄ ምኒልክን አዘዙዋቸው። የአፄ ምኒልክ ጉብኝት ግን አሳዛኝ ሆነ ከሕዝቡ ጋር ጦርነት ገጥመው ከሳቸው ወታደርና ከሕዝቡ የብዙ ሕይወት ረገፈ። አፄ ምኒልክን ተክተለው ከሄዱት እውቅ ሰዎች መካከል የአፄ ቴዎድሮስን ታሪክ በመጻፋቸው የሚታወቁት አለቃ ዘነበን ጨምሮ ብዙ መምህራን ሞቱ ያጦርነቱ ምንስኤ አልታወቀም። የአፄ ምኒልክ ወታደሮች በሕዝቡ ያልተለመደውን አንዳንድ ሕጋዊ ድርጊት በነዋሪው ሕዝብ ላይ ስላሳዩ ሕዝቡ ተቆጥቶ ጦርነት ሳይገጥማቸው አልቀረም ተብሎ ይገመታል።

ክግራኝ አስከሱስንዮስ የተነሱ የኢትዮጵያ ነገሥታት ማዕከላዊ ቤተመንግሥት ሳይኖራቸው ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ዘመናቸውን ያሳለፉ እንደነበር፣ በየአጋጣሚው መገለጹ ይታወሳል። ለዚሁም ሁለት ምክንያቶች ነበሩት 1ኛው አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ የወደሙትን አብያተክርስቲያናት ለመሥራትና ለማደስ ሲሆን 2ኛው ደግሞ

በየአትጣጫው የሚነሱ አልገዛ ባዮች ስላስቸገሯቸው ነው። የአፄ ልብነ ድንግል ልጅ ሚናስ ለመጀመሪያ ጊዜ ባሁኑ አጠራር ደቡብ ጎንደር ውስጥ ትንሽ ከተማ መሥርቶ ነበር። የሱን ዙፋን የወረሰው ልጁ ሠርፀድንግል ያደገው በዚችው ከተማ ስለነበር የመንግሥት መሪ ሲሆንም ከተማዋ የሱ ቤተመንግሥት እንድትሆን አደረገ /3/ ስለዚህ የጎንደር መንግሥት የተጀመረው በዚሁ ነው በማለት የታሪክ ምሑራት ይስማማሉ።

አፄ ሱስንዮስም ንጉሥ ከመሆናቸው አስቀድሞ በምድረ ጉራጌ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ማድረጋቸውን ይነገራል። አፄ ሠርፀድንግል ሲሞቱ ልጃቸው ያዕቆብን ገና ሕፃን እያለ መኳንንቱ አነገሱት። የሕፃኑ በዙፋን መቀመጥ ለደስሙላ ስለነበር መኳንንቱ ሥልጣኑን ተቀራመቱት ጸጥታ ተበላሸ ሕፃኑ ያዕቆብ አድጎ መንግሥቱን መምራት ሲጀምር ከሥልጣን አወረዱት። በሱም ምትክ የአጎቱን ልጅ ዘድንግልን አነገሱት /4/። ዘድንግል ብዙ ሳይቆይ የገዛ መኳንንቱ ገደሉት ሱስንዮስ መኳንንቱ እሱንም እንደሚገድሉት ስላወቀ ከአማራው ወደ አሮሞው ከአሮሞው ወደአማራው እየተዘዋወሩ ቆዩ። በወቅቱ ከደብረሊባኖሶች ጋር ግንኙነት መሥርተው ነበር። ደብረሊባኖስን ያስተዳድሩ የነበሩት ዕጨጌ አብርሃም የደብረ ሊባኖስን መነኮሳት አሳምነው የአፄ ሱስንዮስን ስም በጸሎት እንዲነሳ አደረጉ። ይህን ምክንያት አድርጎ ያዕቆብ ገዳሙን ለማጥፋትና ዕጨጌውን ለማሰር ወደዚያው ለመሄድ ተነሳ። ነገር ግን በሚኖርበት አካባቢ ሽፍቶች ስለተነሱበት ያሰበውን ጉዞ ሰረዘ።

ሱስንዮስ ወድያው እንደነገሡ፣ ከደብረታቦርና ከደንቀዝ በተጨማሪ ሌሎች 18 ከተሞችን በደቡብ ጎንደር ዙርያ እንደቆረቆሩ ይነገርላቸዋል። /5/ ቀራንዮ የተባለው የጎኛም መድኃኔዓለምንም የሠሩት

እላቸው ናቸው። ከአፄ ያዕቆብ ጋር ባደረጉት ጦርነት የእላቸው ተክታዮች አባ ጴጥሮስ የተባለውን የኢትዮጵያ ጳጳስ ስለገደሉ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስማቸው መጉደፍ ጀመረ። በአሮሞ ወይም በጉራጌ ስላከናወኑት መንፈሳዊ ሥራ የተገለጸ ነገር የለም። በማዕከላዊ ክፍለ ኢትዮጵያ ያደረጉት የብዙ ጊዜ ምልልስ ሌላ ምክንያትም ነበረው። ጠንቋዮች "ወልድ ሠአላ" የምትባል ሴት ብታገባ ትነግሣለህ። እሷም በምድረ ሸዋ ነው የምትገኘው እንዳሉዋቸው ይተረካል። በሸዋ ዙርያ ላደረጉት ብዙ አሰሳ ዋናው ምክንያቱ ይኸው ነበር ማለት ነው።

ምዕራፍ ሁለት

አባ እንባቆም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

በተለያዩ አገሮች የተነሱ የታሪክ ሊቃውንት የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያንን ማስረጃዎች መዝግበው አልቋል። እንደነሱ አመዘጋገብ ኢትዮጵያውያን ከማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል በበለጠ የቀይባሕርን ጠረፎች የሥልጣኔአቸው መነሻ አድረገው ይኖሩ ነበር። የቀይ ባሕር አካባቢ ነዋሪዎች ኢትዮጵያውያን ሕይወት በእርሻና በንግድ እንዲሁም በተለያዩ እደጥበባት ሙያ የተመሠረተ ነበር፤ እምነታቸው የክርስትና ሃይማኖት ብቻ ነበር። የእዞና የሌሎችም የባሕር እንስሳት ቆዳ በጥቅም ላይ በማዋል በኩል የታወቁ ነበሩ። የአምልኮት ቦታዎች /አድባራት/ ቁጥር ጥቂት አልነበረም።

ከአሥረኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ግን ክርስቲያኖቹ እየተመናመኑ ሄዱ ከአሥራ ሁለተኛውና አሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ አንድም የክርስትና እምነት ተከታይ በአካባቢው እንዳይታይ ሆነ። ለክርስትናው መጥፋት ዋና ምክንያት በመጀመሪያ የዓረቦች በኋላ የቱርኮች አደገኛ የሆነ የቀይባሕር መቀራመት ነው። የሁለቱ ክፍሎት /ዓረቦችና ቱርኮች/ በአካባቢው መተራመስ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አደጋ ላይ እንዲወድቅ አድርጓል። በዓረቦችና በቱርኮች አስገዳጅነት የእስልምናን እምነት እንዲከተሉ የተገደዱት ኢትዮጵያውያን የቀይባሕር ነዋሪዎች ከወገኖቻቸው ጋር እየተዋጉ መኖር እንደ ባሕል ተቆጠረ። በጦርነቱ ጊዜ የሚማረከው ሰላማዊ ክርስቲያን በባርነት ለዓረቦች ይሸጥ ጀመር በ15ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመን መካከል ብዙ ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያን ለዓረቦች ተሸጠዋል። የአዳል ንጉሥና

የክርስቲያን ንጉሥ በመካከላቸው የሚያደርጉት ረጅም ጊዜ የወሰደ ጦርነት ለክርስቲያኖቹ ባርነት ዓይነተኛ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል።

በባርነት ተሸጠው በዓረብ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል አስደናቂ ታሪክ የፈጸሙ አሉ። በዚህ ሁለት ባልና ሚስት ይጠቀሳሉ። የባልየው ስም ወሰንጌ ይባላል ትውልዱ መራቤቴ ነው። የምስቲየዋ ስም ግን አልተገለጸም። የትግራይ ተወላጅ መሆንዋ ብቻ ይነገራል። ሁለቱ ባልና ሚስት ለአንድ የዓረብ ባለሥልጣን በገፀበረከት ተሠጡ፤ ባልሥልጣኑ ዓረባዊ ሁለት ሚስቶች ነበሩት አንደኛዋ ሚስቱ አይሁዳዊት ነበረች። ከአይሁዳዊቷ ሁለት ልጆችን ወልዷል። የአይሁዳዊቷ አንደኛው ልጅ የእስልምና ስሙ ያልተገለጸው በኋላ እንባቆም የተባለው ነው።

የእንባቆም አባት ብዙ ሳይቆይ ሞተ። እንባቆም ቁርዓን ት/ቤት ገብቶ ትምሕርቱን በሕፃንነቱ ተያያዘው። ትምህርትን የመቀበል ችሎታው እጅግ የላቀ ሆኖ አሥራ አራቱን የቁርዓን ምዕራፎች በቁጥጥሩ አውሎ በውስጥ ስላሉ አንዳንድ ኃይለ ቃላት መመራመር ጀመረ። በቁርዓኑ የሠፈረው የሞትና ትንሣኤ ትርጉም ለማወቅ ፈልጎ ቃዲውን ቢጠይቅ ይህ ኃይለ ቃል እንኳንስ ሊተረጎም እንዲሁ ይታለፋል እንጂ እንደማይነበብ ከቃዲው ተነገረው። እንባቆም በቃዲው መልስ አልረካም ታወከ። የት ሄዶ ማንን ቢጠይቅ አጥጋቢ መልስ ሊያገኝ እንደ ሚችል ያሰላሰል ጀመር። ይህ ሁሉ ሲሆን ለአባቱ በባርነት ለገፀበረከት የተሰጡት ሞግዚቶች ወሰንጌና ሚስቱ በአፅንኦት ይመለከቱት ነበር።

እየቆየ ከሱ ጋር የነበራቸውን የቋንቋ መራራቅ እየተቀራረበ መጣ። ዓረበኛውን እንደልብ መስማትና መናገር ሲችሉ ለተበሳጨበት ነገር መፍትሔ ፈለጉለት፤ ከሁሉ አስቀድመው የሞትና ትንሣኤን

ትርጉም አስረዱት፤ በደበልጥ ግን ወደ ኢትዮጵያ ቢሄድ ስለዚሁና ስለሌሎችም ጥልቅ ምሥጢራት መረዳት እንደሚችል መከሩት ምክራቸውን በመሉ ልብ ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ተነሳ። የሱን ሞግዚቶች ባልና ሚስት ጨምሮ ከኃምሳ ያላነሱ ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያን በማስከተል በመካ በኩል አልፎ በመርከብ በመሳፈር ወደ ዳሕላክ ደሴቶች ደረሰ። ከዚያ ለየብሱ ቅርበት ወዳላት ሐርቂቆ የተባለች ደሴት ተጠጋ። በመጨረሻ ደኅና ወደተባለችው የኢትዮጵያ ወደብ ወጣ። ይህች ወደብ ክርስቲያኖችና እስላሞች በንግድ ይተዳደሩበት ነበር።

ዕንባቆም አምሳያቹን ኢትዮጵያውያን አስከትሎ ከባሕረ ነጋሹ ጋር ተገናኘ። የባሕረነ ጋሹም ስም ዘካርያስ ይባላል። እንባቆም በዘካርያስ የክብር አቀባበልና መስተንግዶ ተደረገለት መሐል አገር ለሚገኘው የኢትዮጵያ ንጉሥ ብልሀ ሰው ከዓረብ አገር መምጣቱን በባሕረ ነጋሽ ተገለጸ። የንጉሡ ስም ማ[redacted] እንደነበር አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን አልገለጹም። ብላቴን ጌታ ሕሩይ ወልደሥላሴ ብቻ በዘመኑ የነበሩ ንጉሥ አፄ ናኦድ መሆናቸውን ጽፏል /6/። በዘመኑ የአዳል አካባቢ ዓረቦች በሚደግፉት የአዳል ንጉሥ ይገዛ ስለነበር በቀላሉ ወደዚህል አገር ለመድረስ አስቸጋሪ ነበር። ዕንባቆም ከባሕረነጋሽ ጋር ሦስት ዓመት ተቀመጠ። እሱን ተከትለው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያን ምድር ከተረገጡ ጀምሮ ወደየቦታቸው ተበታተኑ።

ዕንባቆም የሦስት ዓመት ከባሕነጋሽ ጋር ቆይታ በኋላ፣ ወሰንጌንና ሚስቱን መሪዎች በማድረግ ከንጉሡ ደረሰ። ወሰንጌ ከመማረኩ በፊት የሥልጣን ተጋሪ ነበር። ከሞርኮ በተመለሰ ጊዜም የቀድሞ ሥልጣኑ ተመለሰለት። በብላቴን ጌታ ሕሩይ አባባል ዕንባቆምን ያስተናገደ ንጉሥ ናኦድ እንደሆነ ከላይ ተገልጿል። አንዳንድ

ተመራማሪዎች ደግሞ ዕንባቆምን ያስተናገደ ንጉሥ እስከንድር ሳይሆን አይቀርም ይላሉ።

ዕንባቆም በንጉሡ ከተማ ሁለት ዓመት ያህል ቆየ። በመካከሉ ንጉሡ ሲሞት ለጊዜው የሥልጣን ሽሚያ ስለታየ ዕንባቆም ላይ የሕይወት አደጋ እንዳይደርስ በመስጋት ወሶንጌ ወደ መራቤቴ ወሰደው። በዚሁም ግዕዝን ተማረ ቀጥሎ ምሥጢረ ሥጋዌንና ምሥጢረ ሥላሴን አጠና። ይህ ሁሉ ሲሆን ክርስትና አልተነሳም ነበር። ምሥጢረ ሃይማኖትን ጠንቅቆ ካወቀ በኋላ ደብረሊባኖስ ሄዶ ገዳሙን በሚያስተዳድር አባ ጴጥሮስ እጅ ተጠመቀ። በዓረብኛ የተጻፈ ሐዲስ ኪዳንን በደብረሊበኖስ አግኝቶ አነበበ ብዙ ሳይቆይ አባ ማርቆስ ከተባለው የኢትዮጵያ ጳጳስ የዲቁናን መዓርግ ተቀበለ።

ዕንባቆም ከአባ ማርቆስ የቅብጢ፣ የሦርያ ዕብራይስጥና የአርመን ቋንቋዎችን መማሩ ይነገርለታል /7/። ዕንባቆም በአማካሪነትና በመንፈሳዊ ዳኝነት ጳጳሱን እየረዳ ለተወሰነ ጊዜ ቆይቷል። ጢቆ በተባለው ቦታ በእመቤታችን ስም የተሠራች ቤተክርስቲያን ትገኛለች። ቤተክርስቲያንዋ በእንባቆም የተተከለች ናት። ደብርዋ ቤተልሔም ብሎ ሰይሟታል። አርዑተ ምንኩስናን የተቀበለው ከደብረሊባኖሱ አበምኔት አባ ጴጥሮስ ይሁን ከጳጳሱ ግልጽ አልሆነም። ጳጳሱና እጨጌው አባ እንባቆምን ለኔ ለኔ በማለት ተጣልተውበት ነበር። አፄ ልብነድንግል መምህራኑ ቤተክርስቲያንን ልከው እንዲታረቁ አድርገዋል። ከዚያ በኋላ እየተመላለሰ ሁለቱን እንዲረዳ ስለተወሰነ ሁሉንም ረድቶአቸዋል።

አፄ ልብነድንግል ችሎታውን አይተው የመጻሕፍትን ትርጓሜ ሥራ እንዲያከናውን ስላዘዙት ዮሐንስ አፈወርቅንና አርጋዊ መንፈሳዊን ከዓረብኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተርጉሟል /8/። አባ እንባቆም ከቤተ

ክርስቲያን ሹመት ለመራት ብዙ ጥረት አድርጓል። ከደብረሊባኖስ ወጥቶ እስከዋልድባ ያሉትን ገዳማት በመጎብኘት ያሳለፈው ጊዜ ቀላል አልነበረም፣ ከዋልድባ መነኮሳት ጋር ተገናኝቶ የቤተክርስቲያንን ሕልውና በተመለከተ ብዙ ተወያይቷል። ምናልባትም አረጋዊ መንፈሳዊ የተባለውን መጽሐፍ የተረጎመው እሱ ስለሆነ በአስቄጥሳዊ ሕይወት የሚመሩትን የዛን ዘመን ፍጹማን የዋልድባ ገዳም መናንያን አቋም የተለየ መንፈሳዊ ፍቅር አሳድሮበት ሊሆን ይችላል ከሸዋ ተነስቶ ዋልድባ ድረስ ለመጓዝ ያስገደደው።

ከዋልድባ ወጥቶ አሉ የተባሉትን አድባራትና ገዳማት በመጎብኘት እያለ ሐርከሶ ከተባለው ቦታ ሲደርስ የዓይን ሕመም ይዞት ሰነበተና በዚያው ዓይኑ ታወረ። ዓይነሥውር ሆኖ እየተመራ መቅደሰ እንባቆም ከተባለው ቦታ ደረሰ። በዚያውም አባ በትረማርያም ከተባለው መነኩሴ ጋር ተገናኝ አባ በ[illegible]ረማርያም ወደ ደብረሊባኖስ እንዲመለስ መከረው። ከዚሁ ቦታ ተነስቶ ወደ ደብረሊባኖስ ለመመለስ ነገ ማግስት ሲል ዓይኑ ዳነ። ብዙም ሳይቆይ ወደደብረ ሊባኖስ ተመለሰ፤ ዕጨጌውም አባ ጴጥሮስ ተመልሶ በመምጣቱ ተደስቶ ከሱ ቀጥሎ ዕጨጌ እንደሚሆን ነገረው።

አባ ጴጥሮስ ከአባ እንባቆም ጋር ከተገናኙ በኋላ ብዙ አልቆዩም ባጭር ጊዜ ውስጥ ሞቱ። የአባ ጴጥሮስ ሞት ሲሰማ ብዙ ክርስቲያኖች አዘኑ፣ አለቀሱ፤ ምክንያቱም ቦታ ሳይመርጥ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ወንጌለ ክርስቶስን በማስተማሩ መንፈሳዊ አባትነቱን ብዙ ክርስቲያኖች ተቀብለውት ቆይተዋልና። አፄ ልብነድንግል በተገኙበት ሥርዓተ ቀብሩ ተፈጽሟል። በአባ ጴጥሮስ ምትክ የዕጨጌነቱን መዓረግ አባ እንባቆም ተረከበው።

የአባ እንባቆም የመጀመሪያው እርምጃ የደብረሊባኖስ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ ገዳማት ሴቶችና ወንዶች መነኰሳት ጨርሰው እንዳይገናኙ የሚደነግግ ሕግ ማውጣት ነበር። ዓላማውን ብዙዎቹ ቢደግፉትም የሚቃወሙትም አልጠፉም። ተቃዋሚዎቹ ክፍሎች በቅጥፈት ከአፄ ልብነድንግል ጋር አጣሉት። ልብነድንግል የነገረ ሠሪዎችን ወሬ መሰማቱ ባይቀርም ሁኔታውን በትዕግሥት እየተከተለ ከሦስት ዓመት በላይ ጠብቋል። ነገረሠሪዎቹ ለንጉሡ የሚያቀርቡት የሐሰት ወሬ "አንተ እያለህ ያንተን ልጆች ገላውዴዎስና ያዕቆብን ሊያነግሥ ይፈልጋል፣ በውርደት እንደምትሞት ይናገራል። በጸሎት ጊዜ ያንተን ስም አያነሳም..." የሚል ነበር።

ልብነድንግል ባደባባይ ጠርቶ ለምን እኔን ትቃወማለህ? የሚል ጥያቄ ሲያቀርብለት መልስ ለመስጠት እድል ሳይሰጠው ተቃዋሚዎቹ መነኰሳት የየራሳቸውን ፌዝኾት እያስተጋቡ እጅ እግሩ ይቆረጥ ይደብደብ... በማለት ተመልካቹን ሕዝብ ግራ አጋቡት ከንጉሡ ባለሟሎች አንዱ ወደክፋ ተወሰዶ እንዲታሠር ስላሳሰበ በዚያው ታሠረ። ወዲያው ዝናብ ጠፍቶ ድርቁ ሲጠና እሱን የሚወዱና መንፈሳዊ አባትነቱን የሚቀበሉ መነኰሳት በምክንያቱ ከእሥር ቤት እንዲወጣላቸው ስለፈለጉ ድርቁ በመታሠሩ ለቅጣት የመጣ ነው ብለው ለንጉሡ ተናገሩ። ልብነድንግል የመነኰሳቱን አባባል ተቀብሎ ከእሥር ቤት እንዲወጣ አድርጎ በይቅርታ የዕጨጌነቱን ሥራ እንዲቀጥልበት ጠየቀው እሱ በበኩሉ ደግሞ ወደሹመት እንደማይመለስ ከገለጸለት በኋላ ወደፈለገው ቦታ ይሄድ ዘንድ እንዲፈቀድለት ንጉሡን ለምኖ እንደግብጦን ወደተባለው ሥፍራ ሄደ። ወንጌልን አስተማረ። በ4ቱ እንስሳ ስምም ሶስትክርስቲያን በዘሁ አሠራ። አበው መነኰሳትን አሰባስቦ ቦታው ገዳም

እንዲሆን አደረገ። ሐዋርያዊ ጉዞውን በማራዘም ወደጋፋት ሄዶ ኢአማንያንን አስተማረ በዚያውም ልክ አብምተ ክርስቲያናትን አሳነጸ። የሐዋርያነት ተግባሩ በምዕመናን ዘንድ ታወቀ።

እንደገና ምድሪ በዛን በተባለው ክፍል ተጉዞ ቃለ እግዚአ ብሔርን ሰምተው የማያውቁትን ወገኖች አስተምሮ አጠመቀ። የሐዋርያዊነት ሥራው እጅግ የተቃናለት ሆነ በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ኢትዮጵያዊያን በአሚነ ክርስቶስ እንዲጸኑ አደረገ። የሐዋርያዊነት ተልዕኮው በግራኝ የእሥራ ስድስት ዓመት ወረራ ምንም እንዳልተቋረጠ መግንዘብ ይቻላል። ከሁኔታው ለመረዳት እንደሚቻለው የልብነድንግልን ሞት አልሰማም። የሰማው የልጅ የገላውዴዎስ ሞት ብቻ ነው።

በያጋጣሚው እንደተገለጸው ገላውዴዎስ ጎጃም ውስጥ መርጡለ ማርያምን በማሳደስ እያለ የቡልጋ ክርስቲያኖች የግራኝ ቅሬቶች በሆኑ አረመኔዎች መወረር ስለተነገረው እነሱን ለመታደግ ባስቸኳይ ደርሶ ሲዋጋ በሰለተ ስቅለት አረመኔዎቹ ገድለው አንገቱን ቆረጡት። የአፄ ልብነድንግል ልጅ ወለተጊዮርጊስ የወንድሟን ሞት ስትሰማ አባ እንባቆም ከሚያስ ተምርበት ቦታ ድረስ ተጉዛ መንፈሳዊ መጽናናትን በጸሎቱ እንዲያሰጣት ጠየቀችው። በገላውዴዎስ ሞትም ሁለቱ መሪር ልቅሶ አለቀሱ ይባላል።

ገላውዴዎስ ሲሞት ወንድሙ ሚናስ በትረ መንግሥቱን ጨበጠ። አባ እንባቆም የቤተክርስቲያን ኃላፊነቱን በተስተካከለ ሁኔታ ከሚወጣ በት ተልዕኮው ተነስቶ ሚናስን በወንድሙ ሞት ሊያጽናናውና ለተረከበውም ኃላፊነት እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጥህ ሊለው ሄደ። ሚናስ የአባ ዕንባቆምን የአጽናኝ ትምህርት በታላቅ ትኅትና ከተቀበለ በኋላ ተመልሶ ደብረሊባኖስን እንዲመራለት አጥብቆ ለመነው። አባ

እንባቆም በዚሁ መቅት በጣም በዕድሜ ገፍቶ ነበር። ስለዚህ ያለማወላወል የንጉሡን ጥያቄ ተቀብሎ የእጨጌነቱን ሥራ ይቀጥልበት ጀመር።

ከእጨጌነቱ በተጨማሪ የደብረሊባኖስ መነኮሳት መንፈሳዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አርአያ እየሆነ ሊመራቸው ቆይቶ ከተወለደ በ103 ዓመቱ ሚያዚያ 21 ቀን 1553 ዓ.ም አረፈ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በታላቅ መንፈሳዊ አባትነት ከምትቀበላቸው ቅዱሳን አንዱ አባ እንባቆም ነው። በከህነቱ አምልኮተ እግዚአብሔርን በተሟላ ቅድስና ፈጽሟል፣ በማስተማሩ ሐዋርያዊነቱን ተወጥቷል። አንቀፀ አሚን የተባለ ውንም መጽሐፍ ጽፎ ሕዝበ ክርስቲያኑ ቋሚ ትምህርትን እንዲያገኝ አድርጓል።

ቤተክርስቲያን በአባትነታቸው ለተቀበላቸው የደብረሊባኖስ ጥንታውያን ዕጨጌዎች ከእመቤታችን ስብሐተ ፍቁር ቀጥሎ የተማሕፅኖ ስብሐተፍቁር አላቸው። የአባ እንባቆም ስብሐተ ፍቁር በዚሁ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል /9/። የአባ እንባቆም መጽሐፍ "አንቀጸ አሚን" ግራኝ በክርስቲያኖች ላይ የፈጸመውን ግፍ በመቃወም የተመሠረተ ነው። የግራኝ ባለሥልጣኖች የቁርዓንን ሕግ በማፍረስ ላይ እንደነበሩ ይገለጻል። የምሥጢረ ሥጋዌን አተረጓጎም በመጥቀስ ከአይሁድ አባባል በተሻለ መንገድ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እስላሞች እንደሚቀበሉት ይገልጻል። አንቀፀ አሚን በግዕዝ ብቻ ተጽፎ ይገኛል።

ምዕራፍ ሦስት
የሴቶች ቅድስና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በየዘመናቱ የተነሱ መንፈሳውያን ሴቶች አሏት። ጥንታውያን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አድባርትና ገዳማት አንድ ባንድ ለማዳረስ ከተቻለ በየገድሎቹ ሥንክሳሮቹና ሌሎችም የቤተክርስቲያን መጻሕፍት ስማቸው ይፋ ያልወጣ በታላቅ ቅድስትናና ተጋድሎ ይህን ዓለም አሸንፈው ያለፉ ቅዱሳት አንስት ስም ለማግኘት ይቻላል። ይህን ለማድረግ ግን ከፍተኛ ወጭና ረጅም ጊዜ ይጠይቃል። ለጊዜው ታሪካቸውን በቀላሉ ለማግኘት የተቻሉ ቅዱሳት ሴቶች ከዚህ ላይ እንዲነገሩ ተሞክሯል።

1ኛ. ማርያም ሳይንት - አቡነ ኢዮስያስ በመባል የሚታወቁ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን እንደነበሩ ይታወቃል። በሳቸው የተመሠረቱና ገዳማቸው ያረፈበት ገዳም እስከአሁን ከብሩን እንደጠበቀ ይገኛል። ገዳሙ ከጓድዋ ከተማ በስተደቡብ ምሥራቅ አሥር ኪሎሜትር ያህል ወጣ ብሎ ይገኛል። ይህ ገዳም ለአባ ገሪማ ገዳም ቅርበት አለው። አቡነ ኢዮስያስ የንጉሥ ዓምደ ጽዮን ልጅ እንደሆኑ ገዳሙን በቅርብ ከሚያውቁ መነኮሳት ለአዘጋጂው ተነግሮታል። ገድለ ተክለሃይማኖት "...እሉ አዕማደ ምድር እለተሰምዩ ከመመላእክት የምድር ምስሶች መላእክትን የሚመስሉ..." እያለ ከሚጠቅሳቸውና በእጨጌ ፊሊጶስ አማካይነት ከተሾሙት አሥራ ሁለቱ የደብረሊባኖስ ንቡራነ ዕድ ጋር አባ ኢዮስያስ ተመሳሳይነት ድርሻ እንዳላቸው ይነገራል። የውጭ ጸሐፊዎች ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ለሆኑት አባ ኢዮስያስ ወንጌልን ለማስተማር "ወጅ" የተባለው ቦታ እንደደረሳቸው ጽፏል። /10/

ከአከሱም ከተማ በስተሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ በግምት ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ኪሎሜትር ርቀት ባለው ቦታ ላይ የምትገኝ አንዲት ደብር አለች፤ በዓለ ንግሥዋ ግንቦት 1 ቀን ይከበራል። ነገር ግን አከባበርዋ በእመቤታችን የልደት በዓል ስም አይደለም። በሌላ ጻድቅ ሴት ስም ነው የሚከበረው። የጻድቋ ስም ማርያም ሳይንት ይባላል። ማርያም ሳይንት ተብላ የተሰየመችበት ምክንያት የትውልድ ቦታዋ አማራ ሳይንት በመሆኑ ነው። ትክክለኛው ዓለማዊ ስምዋን ለማወቅ አልተቻለም። በትውልድ ቦታዋ ብቻ ስያሜ ተሠጥቶአታል።

አቡነ ኢየሱያስን ለስብከተ ወንጌል በየቦታው ሲዘዋወሩ ማርያም ሳይንት ዓለምን ንቃ ልትከተላቸው እንደቻለችና ለመንፈሳዊ ተልዕኮዋቸው ብዙ እንደረዳቻቸው ይታመናል። ወደ አከሱም አካባቢ ልትሄድ የቻለችውም አቡነ ኢየሱያስን በመከተል ነው። ስለፈጸመችው ተጋድሎ የሚገልጽ ጽሑፍ በአባ ኢየሱያስ ገዳም እንደሚገኝ ይነገራል። እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ የማርያም ሳይንት ደብር በአባ ኢየሱያስ ገዳም ሥር ይተዳደር ነበር። እሷን የመሰሉና ብዙ የሥጋ መከራን እየታገሱ የቤተክርስቲያንን ቅድስና የተላበሱ ብዙ ሴቶች ከአሥራ አራተኛው እስከ አሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በኢትዮጵያ እንደተነሱ የሚገልጹ ማስረጃዎች ጥቂቶቹ አይደሉም።

2. ወለተ ጴጥሮስ . ድዋሮ በመባል የምትታወቀው ቦታ በይበልጥ የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚኖሩባት ናት። ይሁን እንጂ ከዚች ክፍል ብዙ ስመጥር ታላላቅ ሴቶች ወጥተዋል። ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ብዙ አስደናቂ ተገባራትን መፈጸማቸው የሚነገርላቸው እቴጌ እሌኒ የድዋሮ ባላባት ልጅ ናቸው። ከእስልምና እምነት ተከታይ ቤተሰብ ተገኝተው ነው ብዙ የቤተክርስቲያንና

የቤተመንግሥት ቁም ነገር የፈጸሙት የሳቸው ታሪክ በክፍል ሦስት ክርስትና በኢትዮጵያ ስለተገጸ አሱን መመልከት ይቻላል። ከዚህ አሁን የሚገለጸው የወለተ ጴጥሮስ ታሪክ ነው። ወለተ ጴጥሮስ ከድዋሮ ታላላቅ ቤተሰቦች ትውልድ ያላት ናት። ነገር ግን የክርስቲያን ቤተሰብ ልጅ እንደሆነች ነው የምንረዳው። ባልዋም ከፍተኛ የሥልጣን መዓረግ ነበረው። ምንም ልጅ ሳትወልድ ባልዋ ኅዳር 17 ቀን የሚነበበው ሥንክሣር አዒ ያዕቆብ /1588 - 1545/ በግፍ እንደገደሉት ይገልጻል። ዕለቱንም የእሱ እረፍት ቀን በማለት ይጠቅሰዋል።

ወለተ ጴጥሮስ ለሁለተኛ ጊዜ ሥዕለ ክርስቶስ የተባለውን ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን አገባች ከሱም ሦስት ልጆች ወለደች። ነገር ግን ሦስቱም በጨቅላ ዕድሜአቸው ሞቱ። ባልዋ ሥዕለ ክርስቶስ የንጉሥ ሱስንዮስ የጦር መሪ ነበር። ዋና መኖሪያው ጋይንት ውስጥ ልዩ ስሙ ሰማዳ በመባል የሚታወቀው ሥፍራ ነበር። የመኖሪያው ግንብ ምልክት እስከአሁን ይታያል። የሚገኝበት ቦት ከቆማ ፋሲለደስ ብዙም አይርቅም።

በሱስንዮስ የካቶሊክ እምነት መቀበል ምክንያት ለዘጠኝ ዓመት የኢትዮጵያውያንን ደም ያፈሰሰው ጦርነት የመራው ሥዕለ ክርስቶስ ነው። አመራሩም አርቶዶክሳውያንን ለማጥፋት ነበር። ምክንያቱም ሥዕለ ክርስቶስ የሱስንዮስን ዓላማ ከደገፉት የመንግሥት ባለሥልጣኖች የመጀመሪያው ስለነበር ነው። በአንጻሩ ወለተ ጴጥሮስ በተዋሕዶ ሃይማኖት የጸናችና የካቶሊክን እምነት በጽኑ የምትቃወም ነበረች ብዙ ኢትዮጵያውያን የካቶሊክን እምነት በመቃወም በጦርነቱ አልቀዋል። የተዋሕዶ ሃይማኖትን ተከታዮች በመምራት በጦርነቱ የተሠለፉት የታወቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ አባ ዲዮስቆሮስና ጳጳሱ አባ ስምኦን

ናቸው። ከመኪንንት ውስጥ ደግሞ ራስ የማነ ክርስቶስ ልጃቸውን ያገባው ራስ ዩልዮስና ሌሎችም አምስት የራስ መዓረግነት ያነበራቸው ነበሩ። እነሱን ተከትለው የተሰለፉ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሥፍር ቁጥር የላቸውም ይባላል ግን አብዛኞቹ በጦርነቱ ረግፈዋል።

ከባዱና ብዙ ሕዝብ እንደቅጠል የረገፈበት ጦርነት ከሰሜን ጎንደር ርዕሰ ከተማ በስተደቡብ በሚገኘውና "ፀዳ" በመባል በሚታወቀው አካባቢ ነው። ሊቁ አባዲዮስቆሮስና ጳጳሱ አባ ሰምአንን ጨምሮ አብዛኞቹ ካህናት ያለቁት ፀዳ ላይ ነው። በአቶ ተከለጻድቅ መኩርያ አመዘጋገብ አባ ሰምአንን የገደለው አንድ ስሙ ያልታወቀ ወታደር በጦር ወግቶ ነው /11/። በሌላ በኩል የወለተ ጴጥሮስ ባል ሥዕለ ክርስቶስ ከጦርነት ውለው ወደቤቱ ሲመለስ የሚቹን አባ ሰምአን /ጳጳስ/ ልብስ የገዳይነትን ምልክት በማድረግ ወደ ቤቱ ይዞ እንደተመለሰና የገደላቸውም እሱ እንደሆነ ገድለ ወለተ ጴጥሮስ ይገልጻል። ወለተ ጴጥሮስ ጳጳሱን ገድሎ ልብሱን ይዞ በመምጣቱ ሥዕለ ክርስቶስን በአረመኔነት ተመለከተችው ከሱም ለመለየት ቆረጠች። በዚሙኑ የጣና ቂርቆስ ገዳም አበምኔት አባ ፈትለ ክርስቶስ ይባል ነበር። ወለተ ጴጥሮስ በምሥጢር እየተላላከች ከአባ ፈትለ ክርስቶስ ጋር ግንኙነትን መሠረተች። የካቶሊክን እምነት ከመከተሉም በላይ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ደም አፈሰሶ የጳጳስን ልብስ የገዳይነትን ምልክት በማድረግ ከሚፎክረው ሰው ጋር በሚስትነት ለመኖር እንደማትፈልግና ከሱ ተለይታ የምትሸሽግበትን ቦታ እንዲጠቁማት ተማጸነችው። አባ ፈትለ ክርስቶስ ሁለት የገዳሙ ሴት መነኩሳይያትን ልኮ ይዘዋት እንዲሸሹ አደረገ።

መነኮሳይያቱ ወዳልታወቀ ቦታ ይዘዋት ተደበቁ። ሥዕለ ክርስቶስ ካለችበት ተይዛ በግድ ወደቤቷ እንድትመለስ ለማድረግ አዳኝ ወታደሮችን በብዙ ቦታ አሠማራ። ነገር ግን ሊያገኙዋት አልቻሉም። ከሁለቱ መነኮሳይያት ጋር የተደበቀችበት ሥፍራ ጥቅጥቅ ባለደን የተሸፈነ ነበር። ይህ ሥፍራ እስካሁን ሣጋ ወለተ ጴጥሮስ በመባል ይታወቃል። በዚሁ ቦታ በስሟ ቤተክርስቲያን ተተክሏል።

ወለተ ጴጥሮስ ዓርውተ ምንኩስናን ተቀብላ የቅድስና ተግባር ዋን ማከናወን ጀመረች። የሱስንዮስንም ዓላማ በግልጽ እየተቃወመች ኢትዮጵያውያን ከርስቲያን በእምነታቸው እንዲጸኑ ትመክር ነበር። እሷን አድኖ ለመያዝ ባንድ በኩል ባልዋ የነበረው ሥዕለ ክርስቶስ በሌላ በኩል ሱስንዮስ ብዙ ደከሙ እሷ ግን ካንዱ ወደሌላው እየሸሸች ክርስቲያኑን ሕዝብ የማጽናናቱን ተግባር ቀጠለችበት። የሱስንዮስም ስም በቤቱክርስቲያን ጸሎት እንዳይነሳ አደረገች። ሽሽቷ ግን ዘላቂ አልነበረም። አንድ ጊዜ በንጉሡ አዳኞች ተይዛ መጣችና ከንጉሡ ፊት ቀረበች። ንጉሡ የሚከተለውን ሃይማኖት የተቃወመችበትን ምክንያት እንድታስረዳ ብትጠየቅ ምንም መልስ ሳትሠጥ ቀረች። ሱስንዮስ የቁም እስረኛ ሆና እንድትቆይ አዘዘ። ከቁም እሥረኛነቷ በለሊት ጠፍታ ጣና ውስጥ ወደሚገኘው የዘጌ ገዳም ገባች። ይህ ሁሉ ሲሆን ወለተ ጳውሎስና እንተ ክርስቶስ የተባሉ ሁለት መነኮሳይያት ከሷ አልተለዩም። እነዚህ መነኮሳይያት በጣና ቂርቆሱ አበምኔት አባ ፈትለ ክርስቶስ ተልከው ከቤቷ ይዘዋት ይሸሹ ሳይሆኑ አይቀሩም።

ከዘጌ ወደዋልድባና ጸለመት በመዘዋወር ሕዝቡ በካቶሊክ እምነት እንዳይበከል ትመክር ነበር። በድጋሚ ከጸለምት ተይዛ ወደንጉሡ ተወሰደችና ሦስት ካቶሊካውያን አግባብተው ወደ ሮማ

እምነት እንዲያስገቡዋት ተመደቡ። እምነቷን ልትለውጥ ስላልቻለች በግዞት ወደ ዳር አገር እንድትላክ ሱስንዮስ አዘዘ። ነገር ግን መልክዐ ክርስቶስ በተባለው ሰው አማላጅነት አዘዞ ተቀምጣ እልፎኩስ እየተመላለሰ እንዲአዉጣት ተመደበ። እሱም ከወርሐ ፀደይ እስከ ወርሐ መጸው ድረስ ሊያሳምናት ብዙ ደከመ ድካሙም ከንቱ ሆነ።

ሱስንዮስ በጽናቷ ተበሳጭቶ ሸዋል በተባለው ቆላማ ሥፍራ እንድትታሠር ወታደሮች ላከባት። የወታደሩ ተንጋግቶ መምጣት የተመለከቱ ጓደኞቿ ወለተ ጴውሎስና አንተ ክርስቶስ ትተዋት ሸሹ። ብቻዋ ወደተጠቀሰው ቆላማ ሥፍራ ተወስዳ ሦስት ዓመት ያህል ታሠረች። በመንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ የነበራቸው ዘድንግልና ዮሐንስ የሚባሉ ወንድሞች ነበሩዋት። ሁለቱ ወንድማማቾች በእጎታቸው መጉላላት ቅር ይሰኙ ነበር። ዮሐንስ የተባለው ወንድሟ በዕድሜ ጓደኛው የነበረውን የንጉሡ ልጅ ፋሲለደስ እንዲያግልደውና እንድትፈታ ጠየቀው። በዚሁም ተፈታች። ሸበል የተባለው ሥፍራ ብዘመነ ሱስንዮስ የተቃዋሚዎች መቀጣጫ ቦታ ነበር። ወለተ ጴጥሮስ ከሸበል ስትወጣ ከሷ በፊትና በኋላ የተጋዙት ሁሉ ሥወንዶችና ሴቶች/ ኣብሮዉ ተፈቱ።

ከሸበል ወጥታ ደምቢያ ውስጥ ጫንቆ በተባለው ሥፍራ ተቀመጠች። በተለያየ ምክንያት ቆባቸውን አውልቀው የቆዩ ብዙ ሰዎች ወደሷ ተሰበሰቡ። የተከታዮቿን ብዛት ተመልክቶ ወንድሟ ዘድንግል እንፍራስ ወደሚገኘው ርስቱ ሄዳ ብትቀመጥ የሚገዶ እጥረትና የምግብ ችግር እንደማይገጥማት ነገራት። በንጉሡ የተፈቀዳላት ግን ጣና ቂርቆስ ገብታ እንድትቀመጥ ነው። ፈቃዱን ለመፈጸም መሄድዋ ባይቀርም በዚሁ ለመቀመጥ ፈቃደኛ አልነበረችም። ብዙ ሳትቆይ ጣና ቂርቆስን በመተው ምዕሌ ወደተባለው ቦታ ሄደች።

በዚሁ ብዙ ሴቶችና ወንዶች መነኮሳት ወደሷ ተሰበሰቡ። ካቶሊኮችን የሚቃወሙ ኢትዮጵያውያንን እያደነ ለመከራ የሚዳርግ ስሙ መዝራዕተ ክርስቶስ የሚባል የሱስንዮስ መልእክተኛ ባካባቢው መታየቱን ስትሰማ ምዕሌን ትታ ወደሌላ ሄደች ሁኔታው ሲረጋጋ እንደገና ወደምዕሌ ተመለሰች።

የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በድብቅ ተሰብስበው የሚኖሩበት መንዞ የተባለ ቦታ መኖሩን ስትሰማ ወደዚያው ሄደች። ምሥጢረ መጻሕፍትንም ከነሱ ተማረች። ከምሑራኑ መካከል አባ ፀጋ ክርስቶስ የሚባል ሊቅ በመንዞ ይገኝ ነበር። ይህ ሊቅ መጽሐፈ ሐዊን እያብራራና እየተረጎመ አስተምሯታል። ሐዊ ማለት እስትግቡዕ ማለት እንደሆነ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ተገልጿል። በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከሚገኙት እጅግ ብዙ የብራና ቅጠል ያላቸው መጻሕፍት አንዱ መጽሐፈ ሐዊ ነው። በኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ ከምትገኘውና "ደብረ ሲቅ" በመባል የምትታወቀው ቦታ ተቀምጦ "አንትያኩስ" የተባለው ሊቅ እንዳዘጋጀው የመጽሐፉ መግቢያ ያስረዳል። ጽሑፉን ያዘጋጀበት ምክንያት ቅዱሳት መጻሕፍትን በቀላሉ መረዳት የማይችሉ ምዕመናን ማስተማርያ እንዲሆን ፈልጎ መሆኑ መጽሐፉ ያስረዳል። ከመግቢያው ለማስረጃ ያህል በከፊል በሚከተለው ቀርቧል። "... ዝንቱ አብ ሊቅ አንትያኩስ ዘእምደብረሲቅ ዘሐለወት በምሥራቀ ኢየሩሳሌም እስመ ውእቱ ረክበ በዛቲ ደብር ፍናተ ሐዲጎታ በምክንያት ዘይደሉ ጽሑቆታ ወአስተጋብአ በህየ እመጻሕፍት ሐዲሳት አምላካውያት መጽሐፈ ወሰመዮ ስም ሐዊ ዘውእቱ አስተጋባኤ ሮወጊ ዖታት እስመ ውእቱ ያኤምር ላእለ ግብራት ብዙኅት ወፀአታ እመጻሕፍት ቅዱሳት ቀኖናውያት..."

ሱስንዮስ ከሥልጣን ወርዶ ፋሲል ስለነገሠ የሮማ እምነት በአዋጅ ተገታ። አባ ማርቆስ የተባለው ግብፃዊ ጳጳስ ወደኢትዮጵያ ሲመጣ ሥናር ድረስ ሄዳ ወለተ ጴጥሮስ አቀባበል አደረገችለት። በ1636 ዓ.ም ነው የመጣው። አባ ማርቆስ በጦር ሚዳ ስለተገደለው አባ ስምዖንና ከሱ ጋር ለማዕትነትን ስለተቀበሉ ሌሎች ክርስቲያን ምክንያት ተቃውሞ ከባልዋ ከተለየች ጀምሮ የፈጸመችው ተጋድሎ በግብፅ ክርስቲያኖች ዘንድ ስለተሰማ በቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሥፍራ ያላት መሆኑን ገለጸላት።

የሰላም ጊዜ ሲመለስ ወንዶችና ሴቶች የሚገኙበት ገዳም መሥርታ ትኖር ጀመር። ወደ ከተማም እየተመላለሰች የሥጋ ዘመዶችዋን ትጎበኝ ነበር። የካቶሊክን እምነት ተቀብለው ለመመለስ ያስቸገሩትን ወለተ ጊዮርጊስና ጓደኞቿ በመምከርና በማስተማር ወደ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲመለሱ ለማድረግ ችላለች። ወለተጊዮርጊስ ከሮማ እምነት ላለመመለስ ብዙ ማስቸገርዋ ይነገራል። ንጉሡ ፋሲል ሳይቀር እሷን ለመመለስ ብዙ ደክሞ አልተሳካለትም ነበር ይባላል። አልሆን ሲለው አርሷንና ዓመተ ክርስቶስ የተባለችውን ጓደኛዋ ከወለተ ጴጥሮስ ዘንድ ላከችው። ወለተ ጴጥሮስም እነሱን ለመመለስ ብዙ ጊዜ ወስዶባታል።

የወለተ ጴጥሮስን አርአያ በመከተል በዘመኑ ብዙ መናንያት ሴቶች ወደምንኩስና ዓለም ገብተው ነበር። እነ ወለተ ጳውሎስ በዚሁ ይጠቀሳሉ። በአጽንኦ በዓት መጽሐፈ መነኮሳት እንደሚያዘው ከፍተኛ ተጋድሎን እየፈጸሙና ሥጋቸውን ለመክራ አሳልፈው በመስጠት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ እንደኖሩ ተመስክሮላቸዋል።

ወለተ ጴጥሮስ በ50 ዓመት ዕድሜዋ መስከረም 17 ቀን ዓረፈች። በዓለመ ሥጋ 24 ዓመት በምነና 26 ዓመተ ኑራለች። የወለተ ጴጥሮስ ገድልና ታሪክ በብዙ የአውሮፖ አገሮች በብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል /12/።

ምዕራፍ 4
ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በምሥጢረ ሥላሴ ምክንያት የተደረገው ክርክር ክፍል 1 የምሥጢረ ሥላሴ ውዝግብ ከ15ኛው ክፍለ ዘመንና ከዚያ በፊት

የደብረቢዘን መነኮሳት ስለቅዳሜና እሁድ አከባበር በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መለያየትን አምጥተው በዚሁ ለብዙ ዘመናት የዘለቀ አለመግባባት እንደተፈጠረ በክፍል አንድ ክርስትና በኢትዮጵያ ሰፋ ብሎ ተገልጿል። የምሥጢረ ሥላሴ መለያየትም ከደብረቢዘን መመን ጨቱን የሚናገሩ አሉ። መጽሐፈ ብርሃን የሚል መጽሐፍን ማዘጋጀት የተጀመረው በደብረቢዘኖች እንደሆነ የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው። የዓመተ ምሕረት ዘገባ አይታይባቸውም እንጂ አንዳንድ ቁንጽል ጽሑፎች በግዕዝ የተዘጋጁና ሁለት ወይም ሦስት የደብረቢዘን መነኮሳት ስም ባዘጋጅነት የተጠቀሱበት በተለያዩ ቦታዎች ይገኛሉ። መጽሐፈ ብርሃን በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ የሚገኘው ሁሉ በይበልጥ የሚያተኩረው ወደ ምሥጢረ ሥላሴ ነው።

ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ብዙ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሃይማኖት ነክ መጻሕፍትን ጽፏል። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በዚሁ ከፍተኛ ሥፍራ አላቸው። የምሥጢረ ሥላሴን፣ የሚሥጢረ ሥጋዌን ጥንታውያን መናፍቃን በማውገዝና በመዝለፍ ላይ የተመሠረተ መጽሐፈ ምሥጢር በመባል የሚታወቀውን መጽሐፍ ጽፈዋል። መጽሐፈ ምሥጢር ሰባልዮስና ዮሐንስ ተአቃቢ ከሚያወግዛቸውና ከሚዘልፋቸው መናፍቃን በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። ሁለቱ የምሥጢረ ሥላሴ መናፍቃን ናቸው። ሰባልዮስ የሥላሴ ገጽ አንድነው በማለቱ ዮሐንስ ተአቃቢ አብ ለብቻው ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ፣

ለመልድም ለመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ በማለታቸው ከቤተክርስቲያን የተለዩ፣ የተወገዙ ናቸው። የአባ ጊዮርጊስ ጽሑፍ አርጌንስንም በምሥጢረ ሥላሴ መናፍቅነት አስቀምጦታል። ስለ አርጌንስ ከመጽሐፈ ምሥጢር የሚከተለውን በአራት ደረጃ የተከፈለ ጽሑፍ እናገኛለን። "...ንበልኬ ዘለፋሁ ለአርጌንስ ዘይቤ ኢይከል ወልድ ይርአዮ ለአብ በእንተእበይ ዘላእሌሁ ለአብ፣ ወኢይከል መንፈስ ቅዱስ ይርአዮ ለወልድ በእንተዕበይ ዘላእሌሁ ለወልድ፣ ኢይከሉ መላእክት ይርአይዎ ለመንፈስ ቅዱስ በእንተ ዕበይ ዘላእሌሁ ለመንፈስ ቅዱስ፣ ኢይከሉ ውሉደሰብእ ይርአዩዎሙ ለመላእክቱ በእንተ እበይ ዘላአሌሆሙ ለመላእክተ ሰማይ..." አማርኛ አርጌንስ ዘለፉ ይገባዋል። ወልድ አብን አያየውም አብ ከሱ ስለሚበልጥ መንፈስ ቅዱስ ወልድን አያየውም ወልድ ከሱ ስለሚበልጥ፣ መላእክት መንፈስ ቅዱስን አያዩትም መንፈስ ቅዱስ ከነሱ ስለሚበልጥ የአዳም ልጆች /ሰዎች/ መላእክትን አያዩዋቸውም መላእክት ከነሱ ስለሚበልጡ ስላሉ።

የአርጌንስ መናፍቅነት በምሥጢረ ሥላሴ መሆኑ ባይካድም በዓለም ዓቀፋዊው የቤተክርስቲያን ታሪክ ስለሱ የሚገለጸው ከአባ ጊዮርጊስ አቀራረብ ጨርሶ የተለየ ነው። እሱም "ዮም" በሚለው ቃል መሠረትነት ይገለጻል። ቃሉ እንዳለ በግዕዝም በአብራይስጥም ይነገራል። በአተረጓጎምም በሁለቱ ቋንቋዎች ተመሳሳይነት አለው። "ዮም" በእኛ ዛሬ ነገ የሚል ትርጉም ከሰጠነው በኋላ ዮም ወንጌል እንላለን። ይህን ስንል ዘመነ ሥጋዌን ማጠቃለላችን ነው። እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙሞ በዚህ ተመርኩዘው ስለትምህርተ መለኮት ብዙ ገለጻ አድርገዋል። አርጌንስ የአካላዊ ቃልን ቀዳማዊ ልደት ቅዱሳት መጻሕፍትን

እየተመረከዘ የተለየ ትርጉም ሠጥቶታል። ወልድየ አንተ ወእነ ዮም መለድኩከ እግዚአብሔር አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድኩህ /13/ ተብሎ በመዝሙረ ዳዊት የተነገረውን ሲተረጉም ዮም የሚለውን ቃል ሁልጊዜ ብሎ ተርጉሞታል። በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድን መውለድ በአንድ ጊዜ የተፈጸመ አይደለም። የፀሐይ ጮራ ሁልጊዜ ከፀሐይ እንደሚወጣ፣ የወልድ ልደትም እንዲሁ ነው ብሏል።

አባ ጊዮርጊስ ፈጢኖስ የተባለውን መናፍቅ ጨምሮ ብዙ የምሥጢረ ሥጋዌን መናፍቃን ገስጸዋል። በአባ ጊዮርጊስ ጽሑፍ ብዙ ከቤተክርስቲያን ታሪክ ጋር አብረው የማይሄዱ አባባሎች አሉ። ልዮንን የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ብሎታል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ከፍሉ የኬልቄዶን ጉባኤ ተካፋዮች ከኒቅያ ጉባኤ አባቶች በእጥፍ አብዝተው 636 ያደርጉዋቸዋል። አባ ጊዮርጊስ ግን ከዚያ በማብለጥ 737 እንደሆኑ ይገልጻሉ። ነቢዩ ኢሳይያስ አሕማረ ኬልቄዶን /የኬልቄዶን ታንኳዎች/ በማለት የጠቀሰውን አባ ጊዮርጊስ ለኬልቄዶን አባሎች ሠጥተው "ሞገድ ለመቀስቀስ በኬልቄዶን የተሰበሰቡ..." ብለዋቸዋል። እንደ አባ ጊዮርጊስ አባባል የኬልቄዶናውያን ሞገድነት ሠይጣናዊ ነው።

በ15ኛው ክፍለ ዘመን በምሥጢረ ሥላሴ መለያየት ተፈጥሮ ነበር። ገማልያል ዘሚካኤልና አፅቃ የተባሉ ሰዎች ስለ ምሥጢረ ሥላሴ የሚናስቲኮችን መንገድ የተከተለ ትምህርት ይዘው ተነሱ። ገማልያል መጽሐፈ ኩፋሌ ከሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት ውስጥ መቆጠር የለበትም። ሞጽሐፉ በዘመነ ቆስጠንጢኖስ የተጻፈ ወይም ዮሴፍ ወልደኮርዮን የጻፈው ነው በማለቱ አፄ ዘርአያዕቆብ የዮሴፍ ወልደኮርዮንን መጽሐፍ

ከዓረብኛ ወደ ግእዝ ማስተርጎማቸው በክፍል ሁለት መገለጹ ይታወሳል /14/።

እነ ገማልያል ስለተነሱበት ባሕል የሚገልጽ ጽሑፍ በመጽሐፈ ብርሃን ተዘርዝሮ ይገኛል። እሱም ቀጥሎ ይቀርባል። ...ኢመፍትው ለነ ንላዊ ፅሕመነ ወኢንወልጥ ፍጥረተ ብእሲ ውስተካልእ ግእዝ ወእመሰ ትገብር ከመዝ ኮንከ ውፁአ እምሕግ ወርሕቀ እም እግዚአብሔር ዘፈጠረከ በአርአያሁ ወበአምሳሌሁ ጳውሎስኒ ይቤ ለብሔረ ቆሮንቶስ፣ እንዘያርኢ ከመመልከፀ ሥጋሁ ለብእሲ ተገብረ በመልከፀ እግዚአብሔር ይቤ ብእሲ ኢኮነ ርቱዓ ይትገልበብ ርእሶ ሶበይጼሊ እስመ ብአምሳሉ ወበአርአያሁ ለእግዚአብሔር ውእቱ ከመዝ ነገርኖ ለዘሚካኤል ፅልው እስመይቤ አልቦቱ ለእግዚአብሔር መልከፀ ከመሰብእ ወለአጸምኒ ኢገብሮ በአርአያሁ ወበአምሳሊሁ እግዚአብሔርሰ ኢያስተርኢ በከመይቤ ዮሐንስ ወንጌላዊ ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ እፎኬ እብል መልከዓ እግዚአብሔር ከመመልከዓ ሰብእ ውእቱ።

ወንቤሎ ለገማልያል ፍታሕኬ ማዕከሌነ ወማዕከለ ዘሚካኤል በክመስማዕከ ወይቤ ገማልያል በቅድመ ጉባዔ እንሰ ጎበርኩ ምስለ ዘሚካኤል በከመይቤ ወንጌል ለእግዚአብሔር አልቦ ዘርእዮ ግሙራ እምሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ መነኬ ይመስል እብል ወንቤሎ ጸናዕከኑ በዘቃል ወይቤለነ እወ ፀናዕኩ ወንቤሎ ኢትተክሐደነኬ ወይቤ እይትክሐድ ወንቤሎሙ ለካህናቲ ደብተራ ስምዑኬ ከመኢይትክሐደነ ወይቤሉ ካህናተ ደብተራ /15/ ሰማዕነ አ እግዚእነ ንጉሥ ወንቤሎሙ ለዘሚካኤል ወለኖጵቃ ከሐድያነ ሥላሴ ወክሐድያነ መልከዓ ሥላሴ /ክርስቶስ ኢተሰገውኑ ወኢትወልደኑ በፍጹም መልክአ ሰብእ ኢጥዕመኑ ሞተ ዲበ ዕፀመስቀል በእንቲአነ። ወኢተንስአኑ እሙታን

ወኢአርገኑ ውስተ ሰማያት ወኢነበረኑ በየማነአብ ወእመሰ ነበረ በየማነ አብ ወልደ እግዚአብሔር በፍፁም መልክዓ ሰብእ ዘእንበለ እምፍጽምት ድንግል መልክዓ አብ ወመልክዓ መንፈስቅዱስ ኢሥግዋን ይመስልዎኑ ለውእቱ መልክዓ ሰብእ ዘሀሎ በወልድ ወሚመ አይመስልዎ ወሶበሰምዑ ገሣልያል ወዘሚካኤል ወዓፅቃ ደንገፁ ወተሐፍሩ ወብሕሙ ወኢረክቡ ፍኖተ ነገሩ ዘይመይጡ ወንቢሎሙ እመትብሉ ኢይመስልዎ ኮንክሙ ውዑአነ እምሕግ ወኢይደልወክሙ በዊዕ ውስተ ቤተክርስቲያን ወተመጥዎ ሥጋሁ ወደሙ ለዘተሠገወ ኃይል እስመ አባዕከሙ ተውሳክ ዲበሥላሴ መልክዓ ሰብእ ዘኢይመስሎሙ ለመልክዓ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወኮንክሙ ሱታፌሆሙ ለመረብዓን እስመትቤሉ በስሕተትክሙ ዘአሥረፀ ሠይጣን በሕሊናክሙ ወልደ እግዚአብሔርሰ በመልክዓ መለኮቱ ይመስሎሙ ለአብ ወለመንፈስቅዱስ ወበመልክዓ ትስብእቱ ናሁኬ ረሰይክምዎ ፪ኤ አካለ ለወልድ ዋሕድ ዘበእንቲአሁ ይቤ ዮሐንስ ወንጌላዊ ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወሐደረ ላእሌነ ወሠወሮ እምኔነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመስብሐተ ዋሕድ ለአቡሁ። ናሁኬ ወጸፅከሙ እምወንጌለ መንግሥት ዘይዜውእ መሐይምናነ ጎበከ ብካበ መርዓ ሰማያዊ ዘኢየሐልፍ።

ወሰሚአሙ ዘለፉሆሙ ገሣልያል ወዘሚካኤል ወአፅቃ ተመውዑ በኃይለ እግዚአብሔር ወኢተከህሎሙ ይበሉ መልክዓ አብ መልክዓ መንፈስ ቅዱስ እለ ኢለብሱ ሥጋ ኢይመስልዎ ለመልክዓ ወልድ ዘለብሰ ሥጋ ወሶበስዕኑ መይጠቃል እሉውዑአን እምአሚነ ሥላሴ ክህዱ ፍጡነ በቅድሚነ ወበቅድመ ኩሎሙ ካህናተ ደብተራ ንሕነሰ ነአምንሂ ወዓሚነነ ሥሉስ በግቤ እንበለ ተውሳክ በአሐዱ ምልክና ወበሥልጣን ወብነጊዜ ወበሞኩናን እንበልፍልጠት ለአብኒ አልቦቱ መልክዓ ዘእንበለ

መልክዓ ሰብእ እስመ በአርአያሁ ወበአምሳሌሁ ገብሮ ለሰብእ ወመልክዓ ወልድኒ ከመመልክዓ አቡሁ ውእቱ እሩያን በአካል እንበለ ተገርሮ ስፍሑሃን እንበለተደንግኅ። አሐዱ ራዕዮሙ ወብርሃኖሙ ወአሐዱ መለኮቱሙ ወአሐዱ ‘መንግሥቶሙ ወአሐዱ ሕሊናሆሙ ወሰብእ ኢትዮጵያ ሥርግዋን በአሚነ ሥላሴ ወለእመሰምዑ ሥላሴ ዘይቤ አሐዱ ገፅ በብሔረ ሳዕድ ይሰምይዎ አሐዳዌ፤ በግዕዝ የሠፈረው ረዘም ሰላለ አጠር ላለ መንገድ የአማርኛውን ትርጉም ቀዮሎ አናቀርበሞለን፤ የሰው ሥጋ ከእግዚአብሔር ተሠራ ብሎ ጳውሎስ እንደተናገረ ጢሞህን ብትላጭ የተሰጠህን ፀጋ ማበላሸትህን እወቅ ዘሚካኤል እንደ ሰው ያለ መልክ ለእግዚአብሔር የለውም። አዳምንም በአርአያውና በአምሳሉ አልፈጠረውም ዮሐንስ እግዚአብሔርን ያየው የለም ብሏል።

የዘሚካኤል አባባል ትልቅ ስህተት መሆኑን አውቆ ገሣልያልን በኛና በዘሚካኤል መካከል ስላለው መለያየት ፍረድልን ብንለው ራሱ ገሣልያል የዘሚካኤልን አባባል ደግፎ እኔም ዮሐንስ እንዳለው ያየው የለም እላለሁ አለ። የሁሉንም አባባል ካህናተ ደብተራ እንዲሰሙልን ጠየቅናቸው እነሱም መስማታቸውን አረጋገጡልን ሥላሴንና የሥላሴን መልክ የካዱትን ዘሚካኤልና አፅቃ ሥጋ አልለበሰምን በፍፁም የሰው መልክ አልተወለደምን በመስቀል ላይ ሞትን አልቀመሰምን... በፍፁም መልክአ ሰብእ በአብ ቀኝ አልተቀመጠምን ሥጋ ያልለበሱ የአብ መልክና የመንፈስ ቅዱስ መልክ ለዚያ ሰው መልክ ይመስሉታልን? ስንላቸው ሦስቱ ደነገጡ፣ ፈሩ፣ አፋቸው ተዘጋ፣ የሚናገሩትን አጡ፤ አብና መንፈስ ቅዱስ ወልድን አይመስሉትም ካላችሁ ቤተክርስቲያን ገብታችሁ ሥጋ ወደሙ ልትቀበሉ አትችሉም በሥላሴ ላይ ጭማሪ የሰው መልክ አምጥታችኋልና አራት ገፅ ከሚሉ ጋር አንድ ሁናችኋልና

ወልደ እግዚአብሔርን በመለኮቱ አብና መንፈስ ቅዱስ ይመስላቸዋልና በለውነቱ ወንጌላዊ ዮሐንስ ያ ቃል ሥጋ ሆነ ፀጋንና እውነትም ተሞልቶ በኛ አደረ /ዮሐ. 1÷14/ ብሎ የመሰከረለትን ወልድ ዋህድ ሁለት አካል አደረጋችሁት ከወንጌለ መንግሥትም ወጣችሁ አልናቸው።

ይህን ዘለፋ ሰምተው ገማልያል ዓፅቃና ዘሚካኤል በእግዚአብሔር ኃይል ተሸነፉ። ሥጋን ያልለበሱ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ሥጋን የለበሰውን ወልድ አይመስሉትም ለማለትም አልቻሉም። እነዚህ ሥላሴን ከማመን የወጡ ሰዎች በኛና በደብተራ ካህናት መካከል ከሐዲዎች መሆናቸው ተረጋግጧል። እኛ ግን ሦስት ገፃትን ያለ መደባለቅ እናምናለን እናስተምራለንም አንድ አገዛዝ አንድ ሥልጣን አንዲት መንግሥት ያለመለያየት በማለት እናምናለን።

ከሰው መልክ በቀር ለአብ ሌላ መልክ የለውም፤ በአርአያውና በአምሳሉ ሰውን ፈጥሮታልና የወልድ መልክ እንዳባቱ ነው። የመንፈስ ቅዱስ መልክም እንደ አብና እንደ ወልድ መልክ ነው። በአካል ትክክል ናቸው ያለ ድንጋጌ ሱፉሐን ናቸው። ራዕያቸውና ብርሃናቸው አንድ ነው። መለኮታቸውም አንድ ነው። መንግሥታቸው አንድ ነው። ሕሊናቸውም አንድ ነው። ኢትዮጵያውያንስ ሥላሴን በማመን የተዋቡ ናቸው።

መጽሐፈ ብርሃን በመባል በተለያዩ ጊዜያት ብዙ የሥርዓትና የትምህርተ መለኮት መጻሕፍት ተጽፏል /16/። በቤተ ክህነት የሚገኘው መጽሐፈ ብርሃን ሌላ በተለያዩ ቦታዎች እየተቆነፀሉ የተፃፉና መጽሐፈ ብርሃን እየተባሉ የሚሰየሙ ጥቂቶች አይደሉም። ከክርስቶስ ዕርገት ጀምሮ ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ግኖስቲኮች በተሳሳቱ መንገድ ቅዱሳት መጻሕፍትን ተርጉመዋል። የተሳሳተ ትምህርትንም አስፋፍ ተዋል። እግዚአብሔርን ወደማመን የሚደረሰው ክፍተኛ የፍልስፍናን

ትምህርት በመማር መሆኑን ያስተጋቡ ነበር። የዚህ እምነት አራማጆች ግኖስቲኮች በመባል ይታወቃሉ ግኖስቲክ ማለት ዕውቀት ማለት ነው። ግኖስቲኮች ባንድ መሥመር አልተጓዙም። ብዙ ተለያይተዋል አሥራ አንድ ዓይነት የግኖስቲክ መንገድ አለ። ከመካከላቸው በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የጳውሎስ መልክታትንና የሉቃስን ወንጌልን ብቻ የሚቀበሉ ነበሩ። ለዚሁም የሚሠጡት ምክንያት ሁለቱ መጻሕፍት የሥነ ጽሑፍን ሕግ የተከተሉ ናቸው የሚል ነው።

ሞኖፊዚት በሚለው ቃል የሚመሩ ግኖስቲኮችም ነበሩ። እስካሁን ድረስ በዚህ ቃል ትክክለኛ መልስ የሚነግረኝ ሰው አላገኘሁም። የቲአሎጂ ትምህርት ያላቸው ግሪኮችም ቢሆኑ የቃሉ ትክክለኛ አባባል ለማስረዳት አይችሉም። ብዙዎች ግሪኮች ስለዚሁ ጠይቄአቸው የተለያየ ትርጉም ያለው መልስ ነው የሠጡኝ /17/።በዚሁ ሐረግ /በሞኖፊዚት/ የተመሠረተ የፍልስፍና መንገድ ይዘው የተነሱ ግኖስቲኮችም ነበሩ። የነሱ ትምህርት በሰባልዮስ ተገልጿል። የሰባልዮስ የክህደት ትምህርት በሥላሴ አንድ ገፅ ብቻ አለ የሚል ነው። ሌሎቹ አብ ለብቻው ቃል እስትንፋት ልብ አለው ወልድና መንፈስ ቅዱስም ለያንዳንዳቸው እንዲሁ ይሉ ነበር። ዮሐንስ ተአቃቢ የነሱን ትምህርት ይዞ የተነሳ ነው። በሦስተኛ ተራ ቁጥር የሚመደቡት ሉጎስ የሚለውን የግሪክ ቃል በመነሻነት የተጠቀሙ ናቸው። በመሠረቱ ሉጎስ ማለት ቃል ማለት ሲሆን ለአካላዊ ቃል ለወልደ እግዚአብሔር የተሰጠ ስያሜ ነው። ግኖስቲኮቹ ከፍልስፍና ጋር አደባልቀው ስለተጠቀሙበት ፈጽሞ መሥመሩን ለቀቁ። ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር ከሁሉ በታች የመጨረሻ ትንሿ ኢለመንት ወይም ሞሎክዩል፣ በመካከላቸው ሉጎስ እንደ ተላላኪ ሆኖ ያገናኛቸዋል

አሉ። ይህ የመናፍቅነት ትምህርት ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እንደተነሳ የቤተክርስቲያን ታሪክ ሊቃውንት ያስረዳሉ።

ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሰውን ይመስላል ሰውም እግዚአብሔርን ይመስላል የሚሉት እግዚአብሔር በአርአያውና በምሳሌው ፈጠረው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዓርፍተ ነገር ይዘው ነው። አፅቃ ግሣልያልና ዘሚካኤል ለመለየታቸው ዋና ምክንያት ያደረጉት ዮሐንስ 1÷18 ነው። ከአፄ ዘርአያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በፊት ተመሳሳይ የዶክትሪን /ምሥጢረ ሥላሴ/ መለያየት ተነስቶ ነበር። ይኸውም በአፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥስ መሆኑ ነው። ከመጽሐፈ ብርሃን ስለዚሁ የተጻፈው የግዕዝ ጽሑፍ እንደሚቀጥለው ይነበባል። /...አንሰ ሰማዕኩ ቀዳሚ በመንግሥተ እሁየ ይስሐቅ እንዘይብሉ ሰብእ ይቤ አባ በርተሎሚዎስ ጳጳስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ ገጽ ወሶበሰምዓ እኁየ ይስሐቅ ዘንተ ነገረ ፈነዎሙ ኅበ አባ በርተሎሚዎስ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ ለቀሲስ ፀሐይ ተክስተ ብርሃን ወለዮሴፍ ዓቃቤ ሰዓት ዘይስሐቅ ወለጊዮርጊስ ካህን ዘይትበአስ በእንተ ግፃዌ ሥላሴ ወካለአነሂ ካህናተ ደብተራ ይጠይቁ ለእመኮነ እሙነ ይህትትዎ ለጳጳስ ለእመይቤ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ገፅ ወበጺሆሙ እሙንቱ ኅበ ጳጳስ ተሠአልዎ በእንተዝ ነገር ጳጳስኒ ጸሐፈ ሃይማኖተ ርትዕተ በእንተ ግፃዌ ሥላሴ። በመዋዕሊነኒ ረከብናሆሙ ካሰበ ለዘሚካኤል ወለገግልያል ለዓፅቃ ወለእለከግሆሙ እንዘከሕዱ በእንተ ግፃዌ ሥላሴ ወይብሉ አልቦቱ መልክዓ ለእግዚአብሔር ወተሞኡ በቃለ መጻሕፍት።

<u>አማርኛ</u> . በወንድሚ ይስሐቅ መንግሥት ዘመን ጳጳሱ አባ በርተሎሚዎስ ሳይቀር ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አንድ ገፅ ብቻ አላቸው ይላሉ ስለተባለ ቀሲስ ፀሐይና ዓቃቤ ሰዓት ሌሎችም ካህናተ

ደብተራ ጨምሮ ወንድሚ ይስሐቅ ሁኔታውን ለመረዳት ላካቸው እነሱን ሃይማኖቱ ምን እንደሆነ ጳጳሱን ሲጠይቁት የሥላሴን ፍፃሜ መነሻ አድርጎ ስለቀናች ሃይማኖት ጻፈ። በዘመናችንም ለእግዚአብሔር መልክ የለውም የሚሉትንና የሥላሴን ግፃዌ የሚክዱትን እነዘሚካኤልን አገናኝ ተው በቃለ መጻሕፍትም ተሸነፉ።

የነዘሚካኤል የመጨረሻ ሁኔታ አልታወቀም። በነሱ ምክንያት የተደረገ ጉባኤ ታሪክም ለማግኘት አልተቻለም። ክላይ በመጻሕፍት ቃል ተሸነፉ የሚል ዓርፍተ ነገር ተጠቀሷል። ዓርፍተ ነገሩ ሰምቹን የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ተከራከረው እንዳሳመኑዋቸው ያመለክታል። መታሠርና መባረር ቀርቶላቸው በክርክር ብቻ ሊያምኑ መደረጉ ደግሞ ትክክለኛ የቤተክርስቲያን ዓላማን መከተል እንደሆነ እንረዳለን።

ሚካኤላውያን በሚል ስያሜ የተነሱ የሃይማኖት ቡድኖች ያቋቋሙት አፄ ዘርአያዕቆብ በጠሩት ጉባኤ እንደተወገዘ የተጻፈ ታሪክ አለ። ቡድኖቹ ይህን እምነት እንዳያስፋፉ ማስጠንቀቂያ እንዳተሠጣቸውና መሪያቸው ጊዮርጊስ በቤተ መንግሥት እንደታሠረ ተገልጿል። ይዘውት የተነሱ የዶግማ መንገድ አልታወቀም። እነ ዘሚካኤል ከነሱ ጋር ይሁኑ ወይም ለብቻቸው ግልጽ አልሆነም። ጊዮርጊስ ዕለተ ዕረፍቱ ሲቃረብ ዮሐንስ የተባለውን ካህን አስጠርቶ ስለፈጸመው በደል ተናዟል /18/።

ክፍል 2

የምሥጢረ ሥላሴ መለያየት በዋልድባ

የዋልድባ ገዳማት ሦስት ናቸው። እነሱም ሰቋር፣ ደልቂሐና አብረንታንት በመባል ይታወቃሉ። የአብርሃንት መነኮሳት ከሌሎቹ ተለይተው ከግራኝ ዘመን በፊትና በግራኝ ዘመን ብዙ መከራን አሳልፈዋል። ገዳሙ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ጨርሶ ከጠፋ በኋላ አባ ወልደ ማርያም የተባሉ ባሕታዊ ከሸዋ ሄደው እንደ አዲስ ቆረቆሩት እንደ ቀድሞው አስተካከሉት። ብዙ መነኮሳት ተሰባሰቡላቸው በመልካም መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ገዳሙን ሲመሩ ቆይተው በሞት ሲለዩ በምትካቸው አምኔት ለመምረጥ መነኮሳቱ ሲግባቡ ስላልቻሉ ተለያዩ አባ ጣዕመ ክርስቶስና አባ ሚናስ በተባሉ መነኮሳት ለሁለት ተከፍለው ይመሩ ጀመር። ይህ መለያየታቸው ከ4 ምዕት ዓመታት ለበለጠ ጊዜ እንደቀጠለ ኖረ። በዚህ መካከል ያ በአፄ ዘርአያዕቆብ ዘመን የተነሳው የምሥጢረ ሥላሴ መለያት ወደ እነሱ እንደገባ ይገመታል። የሳንደር ነገሥታት በተፈራረቁ ቁጥር አንዴ የአባ ሚናስን ቡድን ሲደግፉ ሌላ ጊዜ የአባ ጣዕመ ክርስቶስን ሲደግፉ ኑረዋል።

ቅባቶችና ቫሮች አጼ ኢዮአስን ጉባኤ ከፍተው ያከራከሩን እያሉ ሲያስቸግሩዋቸው በዘመናቸው ጳጳስ ስላልነበር ጳጳስ በሌለበት እኔ ሊቀመንበር ሆኜ ስለ ሃይማኖት ማክራከር አይገባኝም አሉ /19/። ነገር ግን ከሳንደር ከተማ በስተደቡብ በሚገኘው ካይለሚዳ /20/ ካሮች ጉባኤ ጠርተው ቅባቶች ከሳንደር ከተማ እንዲባረሩ በማስወሰን ውሳኔውን ለአፄ ኢዮአስ እንዲደርሳቸው አድርገዋል ጉባኤውን በዋነኝ ነት የመሩት ዋልድቦች መሆናቸው ታውቋል። ይሁን እንጂ የአባ ጣዕመ

ክርስቶስ ክፍል ይሁን የአባ ሚናስ ክፍል ጉባኤውን የመራው የታወቀ ነገር የለም። ካሮችን ወክለው የካይላ ሚዳውን ጉባኤ የመሩት በምሥጢረ ሥጋዌ ጉዳይ ነው። የምሥጢረ ሥላሴው መለያየታቸው ግን ወደሌላ ሳይዛመት ነው ለብዙ ምዕት ዓመታት የኖረው።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የምሥጢረ ሥላሴ መለያየታቸው ከወደምሥራቅ እየተዛመተ ሄደ። የደብረ ዓባይ መነኮሳት ነገሩን ይፋ አወጡት። በግለሰቦች ደረጃ ብዙ የትግራይን ካህናት አዳረሰ። ከዚያ በፊት ጎንደር ውስጥ እንደታየው የደም መፋሰስ ባያስከትልም በመነታቀፍ ደረጃ ጎልቶ ስለታየ አሳሳቢነቱ እስከ ማዕከላዊ መንግሥት በግልጽ ታይቷል። በ19ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ምኒልክ ለትግራይ ማኅበረ ክርስቲያን ምሥጢረ ሥላሴን በተመለከተ የላኩት ጽሑፍ ሁኔታውን በግልጽ ያስረዳል። በብዙ የትግራይ ገዳማትና አድባራት አንድ መለኮት ሦስት መለኮት በሚለው ሐረግ ጭቅጭቅ መነሳቱ ከጽሑፉ መረዳት ይቻላል። የጽሑፉ መግለጫ ከአበው ሐዋርያትና ሦስት መቶ ሊቃውንት ትምህርት መዘጋጀቱን ይገልጻል። ከብሉይ ወይም ከሐዲስ አንድም ቃል አልተጠቀሰበትም።

ከሃይማኖተ አበው ብቻ የተውጣጣ ነው። አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ፣ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ፣ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ዮሐንስ ዘኢየሩሳሌም፣ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙና ሌሎችም ስለምሥጢረ ሥላሴ የሰጡት ምሥክርነት በጽሑፉ ተቀነባብሯል /21/።

የጽሑፉ ሙሉ ቃል ቀጥሎ ቀርቧል ... ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይድረስ ከትግራይ ካሉ ምዕመናን ከሊቃውንቱም ከመኳንንቱም እንዴት ሰነብታችኋል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ።

በሃይማኖት ነገር አንድ መለኮት ሦስት መለኮት በማለት እርስ በርሳችሁ ስለተጣላችሁበት ነገር አባቶቻችን ሐዋርያት ሦስት መቶ ሊቃውንት ከጻፉት አውጣጥተን ጻፍንላችሁ ቃሉም ይህ ነው "... አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራዒ ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራዒ መለኮት በአካል፣ በግብር፣ በሰም ሦስት ናቸው። የግብር ሦስትነታቸው በመውለድ፣ በመሰረጽ ነው። በመለኮት በባሕርይ በፈቃድ በሊላው ሁሉ አንድ ናቸው እንጂ ሦስት መለኮት ብሎ አይነገርም /በአሥራ አንድ አንቀጽ/። ስለዚህ ምሥክር የሚሆን አግናጥዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ዛቲ ሥላሴ እሪት ዘእንበለ ፍልጠት ወዘእንበለ ውላጤ በቮ አካላት ወበአሐዱ መለኮት" ብሏል። ሁለተኛም ሠለሥቱ ፍፁማን ዲበ መንበረ ስብሐት ወአሐዛን በጽምረት አሐዱ መለኮት ዘውእቱ አሐዱ፤ ብርሃን ዘይሠርቅ እምኔሁ ሥላሴ ወይመልእ ኩሎ ብሏል።

አትናቴዎስ ሐዋርያው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አምላክ ውእቱ አብ አምላክ ውእቱ ወልድ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ወኢይትበሃሉ ፫ቱ አማልክት አላ አሐዱ አምላክ ብሏል። ሁለተኛው ወመጻሕፍትሂ ቅዱሳት ይቤይና ከመአሐዱ መለኮት ዘሥሉስ ቅዱስ ዘውእቶሙ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ውእቱ መለኮት ተዋሕዶቶሙ ውእቱ መለኮት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በዝንቱ አእመርነ ከመ አሐዱ ውእቱ መለኮተ ፫ቱ መውእቱ ዕሩይ ምስሌሁ በመለኮተ ሥሉስ ፍፁም ሠለስቱ አካላት ከመፈጢኖስ ወመቅደንዮስ ርጉማን እለኢየአምኑ በአስማተ ፫ቱ አካላት አሐደ መለኮተ ዘሥሉስ ቅዱስ ዘከመ ከሀደ አርዮስ ብሏል።

ባስልዮስ የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስም ይደልወነ ናእምር ኅብረተ ተዋሕዶተ መለኮት ሠለስተ አካላተ ወናስተዋድድ በአእምሮ ዘዚአሆሙ አሐዱ መለኮት ንእመን በሃይማኖት ከመይትወሐድ መለኮት በአብ እስመ እምአብ ተወልደ ወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ ወጽአ እምኔሁ እንዘ ኢይቀድም አሐዱ እምካልኡ ወካልኡ እምሣልሱ ወበልዩተ ወልድ ወፀአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ መለኮተ ሥላሴሁ ለአምላክነ ብሏል።

ቄርሎስም የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አብ አሐዱ ፍፁም በአካሉ ወልድ አሐዱ ፍፁም በአካሉ መንፈስ ቅዱስ አሐዱ ፍፁም በአካሉ ወአኮ ከመ አለ መሣረን መንግሥት አላ አሐዱ መለኮቶሙ ብሏል። በሰባ ስምንት አንቀጽ ዮሐንስ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ወነአምን ከመእሙንቱ ሠለስቱ አካላት ፍፁማን በገፃት ወእሩያን በመለኮት ብሏል። /ዘጠና ሰድስት አንቀጽ/ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ይቤ በእንተ ቅድስት ሥላሴ መቅድመ ኩሉ ነአምን በሥላሴ ዕሩይ ወቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሥላሴ በተዋሕዶ መለኮት ዘኢይትሌለዩ አካልሰ ለለ አሐዱ ፍፁም ውእቱ ብገፁ ወበመልከው ዘኢይትሌለዩ /በሦስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ አንቀጽ/ በመለኮት ብሏል።

ዮሐንስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ንሕነሰ ንትአመን ከመወልድ ይትዋሀድ በመለኮት ምስለ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወእመቦ ዘኢየአምን ከመአሐዱ መለኮት ዘሥላሴ ንሕነ ናወግዞ ብሏል /በመቶ ዘጠና ሰምንት አንቀጽ/። ብንያሚ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት /ንብል ንሕነ ነአምን በአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሥሉስ ቅዱስ ዕሩይ፣ ወሰብሐ ሠለስተ አካላተ ዕሩያነ ብኩሉ ግብር ወምግባር ወምንባብ ሠለሥቱ ገፃት በመለኮት ብሏል። ባስልዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት አአምን ወእትአመን ከመእሙንቱ መለኮት ወሕላዌ ወኢይብል ከመአምአካላት ካልአት

ባስልዮስ የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስም ይደልወነ ናእምር ኅብረተ ተዋሕዶተ መለኮት ሠለስቱ አካላተ ወናስተዋድድ በአእምሮ ዘዚአሆሙ አሐዱ መለኮት ንእመን በሃይማኖት ከመይትወሐድ መለኮት በአብ እስመ እምአብ ተወልደ ወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ ወጽአ እምኔሁ እንዘ ኢይቀድም አሐዱ እምካልኡ ወካልኡ እምሣልሱ ወበልደተ ወልድ ወፀአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ መለኮተ ሥላሴሁ ለአምላክነ ብሂል።

ቄርሎስም የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አብ አሐዱ ፍፁም በአካሉ ወልድ አሐዱ ፍፁም በአካሉ መንፈስ ቅዱስ አሐዱ ፍፁም በአካሉ ወአሀ ከመ አለ ሮሜረገ መንግሥት አላ አሐዱ መለኮቶሙ ብሂል። በሰባ ስምንት አንቀጽ ዮሐንስ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ወነአምን ከመእሙንቱ ሠለስቱ አካላት ፍፁማን በገፃት ወእሩያን በመለኮት ብሂል። /ዘጠና ስድስት አንቀጽ/ ኅርንርዮስ ዘእንዚናዙ ይቤ በእንተ ቅድስት ሥላሴ መቅድመ ኩሉ ነአምን በሥላሴ ዕሩይ ወቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሥላሴ በተዋሕዶ መለኮት ዘኢይትሌለዩ አካልሰ ለለ አሐዱ ፍፁም ውእቱ በገፁ ወበመልክዑ ዘኢይትሌለዩ /በሦስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ አንቀጽ/ በመለኮት ብሂል።

ዮሐንስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ንሕነስ ንትአመን ከመወልድ ይትዋህድ በመለኮት ምስለ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወእመቦ ዘኢየአምን ከመአሐዱ መለኮተ ዘሥላሴ ንሕነ ናወግዞ ብሂል /በመቶ ዘጠና ስምንት አንቀጽ/። ብንያሚ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት /ንብል ዓሕነ ነአምን በአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሥሉስ ቅዱስ ዕሩይ፣ ወሰብሐ ሠለስቱ አካላተ ዕሩያነ በኩሉ ግብር ወምግባር ወምንባብ ሠለሥቱ ገፃት በመለኮት ብሂል። ባስልዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት አአምን ወእትአመን ከመእሙንቱ መለኮት ወሕላዌ ወኢይብል ከመአምአካላት ካልአት

የሚያስተጋቡ የዋልድባ መነኮሳት ምሥጢሩ የገባቸው አልነበሩም። በትምህርት የበሰለ አእምሮ አልነበራቸውም። በመካከላቸው ድብደባ ይካሄድ ነበር ቤተክርስቲያኑንም አቃጥለውታል።

በአፄ ምኒልክ የተላከው የምሥጢረ ሥላሴ ጽሑፍ በብዙ የትግራይ ገዳማትና አድባራት በሃይማኖት ምክንያት መለያየት መፍጠሩን ያመለክታል። ከዚያ በፊት በዘመነ መሣፍንት ራስ ወልደ ሥላሴ ትግራይን ይገዙ ነበር። በዘመናቸው ክአባ ገሪማ፣ ከደብረ ዳሞና ከሌሎችም የትግራይ ገዳማት ፀጋ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመተርጎም የተሠለፉ ግለሰቦች እንደነበሩ አለቃ ኪዳነ ወልድ ገልጸዋል። ይህ ደግሞ ምሥጢረ ሥጋዌን ተከትሎ የሚነሳ ጥያቄ እንጂ ከምሥጢረ ሥላሴ ጋር የሚሄድ አይደለም። የአፄ ምኒልክ ጽሑፍ እንድነትን አላመጣም፣ የባሰ መለያየትን አስከተለ እንጂ ደብዳቤው ወደትግራይ ከመላኩ በፊት የዋልድቦችም ሆነ የደብረ አባዮች አለመግባባት በይፋ ወደ አደባባይ አልወጣም ነበር። ከዚያ ወዲህ ግን ነገሩ አስተጋባ /መለኮት በአካል ሦስት/ ማለት ከደብረ አባዮች ሲነገር መለኮት በአካል ሦስት አይባልም መለኮት አንድ ነው በማለት አክሱሞች ተቃወሙ። ከደብረ አባዮች የአክሱሞችን አባባል የሚደግፉ፣ ከአክሱሞች የደብረ አባዮችን አባባል የሚደግፉ ነበሩ። ከአክሱሞች መካከል የደብረ አባዮችን አባባል ከሚደግፉ አንዱ አፈንቡረአድ አብርሃ ይጠቀሳሉ።

ነገሩ ግልጽ ሆኖ የታወቀው ስለዚሁ በተደረገው ጉባኤ ነው። የጉባኤው ቦታ ደሴ ነበር። ጉባኤውን የመሩት መምህር አካለ ወልድና ግብፃዊ የኢትዮጵያ ጳጳስ ናቸው። ጉባኤው ከመጀመሩ በፊት በሃይማኖት ተጣልተው ለመግባት የመጡት አክሱሞችና ደብረአባዮች እንዲታረቁ ሁለቱ የጉባኤው መሪዎች ብዙ መጣራቸው ይነገራል።

የሚያስተጋቡ የዋልድባ መነኮሳት ምሥጢሩ የገባቸው አልነበሩም። በትምህርት የበሰለ አእምሮ አልነበራቸውም። በመካከላቸው ድብደባ ይካሄድ ነበር ቤተክርስቲያኑንም አቃጥለውታል።

በአፄ ምኒልክ የተላከው የምሥጢረ ሥላሴ ጽሑፍ በብዙ የትግራይ ገዳማትና አድባራት በሃይማኖት ምክንያት መለያየት መፍጠሩን ያመለክታል። ከዚያ በፊት በዘመነ መሣፍንት ራስ ወልደ ሥላሴ ትግራይን ይገዙ ነበር። በዘመናቸው ከአባ ገሪማ፣ ከደብረ ዳሞና ከሌሎችም የትግራይ ገዳማት ፀጋ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመቀርጎም የተሠለፉ ግለሰቦች እንደነበሩ አለቃ ኪዳነ ወልድ ገልጸዋል። ይህ ደግሞ ምሥጢረ ሥጋዌን ተከትሎ የሚነሳ ጥያቄ እንጂ ከምሥጢረ ሥላሴ ጋር የሚሄድ አይደለም። የአፄ ምኒልክ ጽሑፍ እንድትን አላመጣም፣ የባሰ መለያየትን አስከተለ እንጂ ደብዳቤው ወደትግራይ ከመላኩ በፊት የዋልድቦችም ሆነ የደብረ አባዮች አለመግባባት በይፋ ወደ አደባባይ አልወጣም ነበር። ከዚያ ወዲህ ግን ነገሩ አስተጋባ /መለኮት በአካል ሦስት/ ማለት ከደብረ አባዮች ሲነገር መለኮት በአካል ሦስት አይባልም መለኮት አንድ ነው በማለት አክሱሞች ተቃወሙ። ከደብረ አባዮች የአክሱሞችን አባባል የሚደግፉ፣ ከአክሱሞች የደብረ አባዮችን አባባል የሚደግፉ ነበሩ። ከአክሱሞች መካከል የደብረ አባዮችን አባባል ከሚደግፉ አንዱ አፈንቡረእድ አብርሃ ይጠቀሳሉ።

ነገሩ ግልጽ ሆኖ የታወቀው ስለዚሁ በተጀረገው ጉባኤ ነው። የጉባኤው ቦታ ደሴ ነበር። ጉባኤውን የመሩት መምህር አካለ ወልድና ኅብፃዊ የኢትዮጵያ ጳጳስ ናቸው። ጉባኤው ክመጀመሩ በፊት በሃይማኖት ተጣልተው ለሙግት የመጡት አክሱሞችና ደብረአባዮች እንዲታረቁ ሁለቱ የጉባኤው መሪዎች ብዙ መጣራቸው ይነገራል።

ለጊዜው በአክሱሞችና በደብረ አባዮች መካከል የተሰማው መለኮት በሚለው የትምህርተ መለኮት /ዶግማ/ አጠራር መለያየት ሆኖ ደብረ አባዮች ሦስት መለኮት ለማለት ያስቻላቸው በቅዳሴ ማርያም የተጻፈው እንደሆነ ተናገሩ፣ አክሱሞች ደግሞ አንድ መለኮት በሉ እንጂ አሐዝ ሠጥታችሁ የመለኮትን ስም መጥቀስ የለባችሁም አሉ። ከሁሉ በበለጠ ግን ያገናኛቸው የጥቅም ጉዳይ እንደሆነ ይነገራል። ታላላቅ የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት አክሱም ላይ ቦታ ነበራቸው ሁኔታው የዓለም ከርስቲያን ኢየሩሳሌም ውስጥ የየራሳቸው የሆነ የቦታ ይዞታ እንደሚኖራቸው ዓይነት ነው። አክሱም ላይ የግል ቦታ የነበራቸው የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት ሁሉ በአክሱም መንፈሳዊ አገልግሎት የመሳተፍ ድርሻ ነበራቸው። በሁለቱ የቆየው በምሥጢረ ሥላሴ የባሕል አጠራር ወደ ዶግማ ስለተለወጠ አክሱሞች ደብረ አባዮችን እንዳይቀድሱ ከለከሉዋቸው ጣባቸው የአደባባይ ምሥጢር የሆነ ከዚህ ጀምሮ ነው።

ንጉሥ ሚካኤል ዘሥልጣኑ ጽሑፍ ዲበ መትከፍቱ ሚካኤል ንጉሠ ጽዮን ተብለው ነግሠው የወሎ፣ የትግራይና የጎጃም ንጉሥ ሆነው ነበር /23/። በዘመኑ ሥመጥር የነበሩ መምህራን ይገኙ የነበሩት ወሎ ውስጥ ነው። ደሴ የንጉሥ ሚካኤል የመናገሻ ከተማና የሊቃውንት መናሐርያ ሆና ስለነበር የአክሱሞችና የደብረ ዓባዮች መለያየት በዚሁ እንዲታይ ዓይነተኛ ምክንያት ሆነ።

አክሱማዊው አፈንቡረእድ አብርሃ መለኮት በአካል ሦስት የሚሉትን ደብረ አባዮች ደግፈው ከነሱ ጋር ተሰልፈው ቆሙ። ታላላቅ መምህራንም አባባላቸውን ደግፈው በሻል ፍላጎታቸው ከነሱ ጋር መቆማቸው ይነገራል። መምህር አካለወልድም የደገፉት የኸው ነው።

ለጊዜው በአክሱሞችና በደብረ አባዮች መካከል የተሰማው መለኮት በሚለው የትምህርተ መለኮት /ዶግማ/ አጠራር መለያየት ሆኖ ደብረ አባዮቹ ሦስት መለኮት ለማለት ያስቻላቸው በቅዳሴ ማርያም የተጻፈው እንደሆነ ተናገሩ፣ አክሱሞች ደግሞ አንድ መለኮት በሉ እንጂ አሐዝ ሠዋታችሁ የመለኮትን ስም መጥቀስ የለባችሁም አሉ። ከሁሉ በበለጠ ግን ያገናኛቸው የጥቅም ጉዳይ እንደሆነ ይነገራል። ታላላቅ የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት አክሱም ላይ ቦታ ነበራቸው ሁኔታው የዓለም ክርስቲያን ኢየሩሳሌም ውስጥ የየራሳቸው የሆነ የቦታ ይዞታ እንደሚኖራቸው ዓይነት ነው። አክሱም ላይ የግል ቦታ የነበራቸው የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት ሁሉ በአክሱም መንፈሳዊ አገልግሎት የመሳተፍ ድርሻ ነበራቸው። በሁለቱ የቆየው በምሥጢረ ሥላሴ የባሕል አጠራር ወደ ዶግማ ስለተለወጠ አክሱሞች ደብረ አባዮችን እንዳይቀድሱ ከለከሉዋቸው ጠባቸው የአደባባይ ምሥጢር የሆነ ከዚህ ጀምሮ ነው።

ንጉሥ ሚካኤል ዘሥልጣኑ ጽሑፍ ዲበ መትከፍቱ ሚካኤል ንጉሠ ጽዮን ተብለው ነግሠው የወሎ፣ የትግራይና የጎጃም ንጉሥ ሆነው ነበር /23/። በዘመኑ ሥመጥር የነበሩ መምህራን ይገኙ የነበሩት ወሎ ውስጥ ነው። ደሴ የንጉሥ ሚካኤል የመናገሻ ከተማና የሊቃውንት መናሐርያ ሆና ስለነበር የአክሱሞችና የደብረ ዓባዮች መለያየት በዚሁ እንዲታይ ዓይነተኛ ምክንያት ሆነ።

አክሱማዊው አፈንቡረእድ አብርሃ መለኮት በአካል ሦስት የሚሉትን ደብረ አባዮች ደግፈው ከነሱ ጋር ተሰልፈው ቆሙ። ታላላቅ መምህራንም አባባላቸውን ደግፈው በግል ፍላጎታቸው ከነሱ ጋር መቆማቸው ይነገራል። መምህር አካለወልድም የደገፉት የኸው ነው።

ክፍል 3

በመምህር አካለወልድና በቤተክህነት ባለሥልጣኖች የተፈጠረው አለመግባባት

ከጉዲት ውድቀት ጀምሮ እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዋና ማዕከል ሆና የኖረችው ወሎ ናት፣ ይህም ሲባል በመልከዓምድር /ጂኦግራፊ/ አቀማመጧ የጥንቱና የአሁኑ አንድ ዓይነት ነው ማለት አይደለም ብዙ ይለያያል።

ቅድስናን ከሊቅነትና ከሐዋርያነት ጋር አስተባብረው የተነሱ አባቶች በተጠቀሱት ዘመናት ከወሎ ተነስተዋል። የወሎ ክፍል በመልከዓምድር አቀማመጥ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክፍል የምታጠቃልል መሆኗ ይታወቃል። ስለዚህ ቱርኮችና ዓረቦች ቀይባሕርን ተሻግረው ክርስቲያኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በወረሩ ቁጥር የአደጋ በትራቸው ምንም መከላከያ በሌለው የዋሁ የወሎ ክርስቲያን ሕዝብ ላይ ያርፍ ነበር። የግራኝ የአሥራ ስድስት ዓመት ወረራም ዋና መንደርደርያው ያደረጋት ወሎን ነው። በዚህ ሁሉ መሄጃ ያጣው አብዛኛው የወሎ ሕዝብ ያለፍላጎት የእስልምና እምነት እንዲቀበል ተገደደ።

ከአጼ ገላውዴዎስ እስከ አፄ ፋሲል ድረስ የተነሱ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዋና ትኩረታቸው በግራኝ የሰለሙትን ወደ ክርስትና ለመመለስና የወደሙትን አብያተ ክርስቲያና መጠገን ነበር። ከዚህም የተነሳ የተወሰነ ማዕከላዊ ቤተ መንግሥት አልነበራቸውም። አፄ ፋሲል ጎንደርን ሲቆረቁሩ ግን ያሁሉ ቀረ። ከነገሥታቱ ጋር ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ትምህርተ ወንጌልን ግስፋፋት ቀርቶ በጎንደር ከተማ

ክፍል 3

በመምህር አካለወልድና በቤተክህነት ባለሥልጣናት የተፈጠረው አለመግባባት

ከጉዲት ውድቀት ጀምሮ እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዋና ማዕከል ሆና የኖረችው ወሎ ናት፣ ይህም ሲባል በመልከዓምድር /ጂኦግራፊ/ አቀማመጧ የጥንቱና የአሁኑ አንድ ዓይነት ነው ማለት አይደለም ብዙ ይለያያል።

ቅድስናን ከሊቅነትና ከሐዋርያነት ጋር አስተባብረው የተነሱ አባቶች በተጠቀሱት ዘመናት ከወሎ ተነስተዋል። የወሎ ክፍል በመልከዓምድር አቀማመጥ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክፍል የምታጠቃልል መሆኗ ይታወቃል። ስለዚህ ቱርኮችና ዓረቦች ቀይባሕርን ተሻግረው ክርስቲያኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በወረሩ ቁጥር የአደጋ በትራቸው ምንም መከላከያ በሌለው የዋሁ የወሎ ክርስቲያን ሕዝብ ላይ ያርፍ ነበር። የግራኝ የአሥራ ስድስት ዓመት ወረራም ዋና መንደርደርያው ያደረጋት ወሎን ነው። በዚህ ሁሉ መሄጃ ያጣው አብዛኛው የወሎ ሕዝብ ያለፍላጎት የእስልምና እምነት እንዲቀበል ተገደደ።

ከአጼ ገላውዴዎስ እስከ አፄ ፋሲል ድረስ የተነሱ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዋና ትኩረታቸው በግራኝ የሰለሙትን ወደ ክርስትና ለመመለስና የወደሙትን አብያተ ክርስቲያና መጠገን ነበር። ከዚህም የተነሳ የተወሰነ ማዕከላዊ ቤተ መንግሥት አልነበራቸውም። አፄ ፋሲል ጎንደርን ሲቆረቁሩ ግን ያሁሉ ቀረ። ከነገሥታቱ ጋር ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ትምህርተ ወንጌልን ማስፋፋት ቀርቶ በጎንደር ከተማ

በሚተከሉ አድባራት ብቻ መወሰን የግድ ሆነ። በቤተክርስቲያንም ትልቅ ችግር አመጣ /27/። ካህናቱ አብዛኛው ተግባራቸው የፖለቲካ መሣሪያ መሆን ነበር። ከግብፅ የሚመጡ ጳጳሳት አብዛኞቹ ሁኔታውን በገለልተኝነት ሲያልፉት አንዳንዶቹ የግል ቂማቸውን ለመወጣት ነገሥታቱን እያሳሳቱ ክርስቲያኑን ሕዝብ ያስፈጁት ነበር። ለዚሁ አባ ክርስቶዱሱና ሣልስ ሰላማ በማስረጃነት ይጠቀሳሉ /28/።

ወሎ ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ የእስልምና እምነት ተከታዮች ሆነው እያለ ተገደው የሰለሙ መሆናቸው የሚያሳይ ምልክት በብዛት ይታይባቸዋል። እንደ ሌሎች እስላሞች በዓረብኛ ስም አይጠሩም። አበጋዝ፣ አሰፋ፣ መኮንን፣ ፀሐይቱ፣ ብርነሽ፣ ዘነበች... በሚሉ ስያሜዎች እንደማንኛውም የአማራው ክርስቲያን ሕዝብ ይጠራሉ /29/። በመካከላቸው የሚገኙት ጥንታውያን አድባራት እንዳይዘጉ ካህን ቀጥረው አገልግሎት እንዲካሄድባቸው እያደረጉም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ነበሩ። ከአባቶቻችን የወረስነው ትውፊት ነው በማለትም በቤተክርስቲያን መንፈሳውያን ከብረ በዓላት ጠላ ጠምቀው እንጀራ ጋግረው ወደቤተክርስቲያን ይወስዳሉ።

በእጄ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የተቋረጠ ሃይማኖታዊ ሥራ በአጄ ዮሐንስና በአፄ ምኒልክ ዘመን ከሦስት መቶ ዓመት በኋላ ተቀሰቀሰ ሁለቱ ነገሥታት እውቅ መምህራንን በወሎ እንዲመደቡ ተስማማሙ።

አፄ ዮሐንስ መምህር ግርማን አፄ ምኒልክ መምህር አካለወልድን በወሎ እንዲመደቡ አድርገዋል። ሁለቱ ነገሥታት ራሳቸው የክርስትና አባት እየሆኑ የአካባቢውን ባለሥልጣኖች ክርስትና አንስተዋል። አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ሚካኤልን አፄ ምኒልክ የቀድሞ ስማቸው አባ ቅጣው ይባል የነበረውን የደሴ ከተማ ኢማም

ኃይለማርያም በማስኘት የክርስትና አባት በመሆን እንዲጠመቁ አድርገዋል።

መምህር አካለወልድ የደሴውን ኢማም ጠለቅ ብሎ የክርስትና ትምህርት እንዲረዳ በማድረጋቸው በሱ እየተሳቡ ብዙ እስላሞች ክርስትናን እንዲቀበሉ አድርገዋል። በየቀኑ በደሴ ከተማ ይጠመቅ የነበረው ሕዝብ ቁጥር አልነበረውም ይባላል። በአፄ ዮሐንስ የተመደቡት መምህር ግርማ በዘኩላቸው ንጉሥ ሚካኤልን በጥሩ ሁኔታ ትምህርተ ክርስትናን ስላስተማሩዋቸው በሳቸው እየተሳበ ወደ ክርስትና የሚገባው ሕዝብም እጅግ ብዙ ነበር።

መምህር ግርማና መምህር አካለወልድ ሁለቱ ነገሥታት /አፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ/ ተጣልተው በነበረ ጊዜ አስታርቀው ደም መፋሰስን በማስቀረታቸውም ይታወቃሉ። የብሉይ ኪዳን መምህራን፤ መምህር ፈለታዎስ መምህር ወልደ ማርያምና አለቃ ካሳ፣ የሐዲስ መምህራን መምህር ወልደ ሚካኤልና መምህር ወልደ ሰማዕት የመጻሕፍተ መነኮሳት መምህራን መምህር ገብረማርያም መምህር ገብረኢየሱስ /የጅር ገዳም/ መምህር ወልደ ሚካአል የደብረ ከርቤ ከነመምህር አካለወልድ ጋር ተሰልፈው በስብከተ ወንጌሉ እንደተባበሩ ይነገራል /30/።

2. <u>የመምህር አካለወልድ በአባ ማቴዎስ በምሥጢረ ሥላሴ መታማትና ውጤቱ</u>

የአክሱሞችና የደብረ አባዮች የሃይማኖት ሙቅሙቅ ወሎ ውስጥ በጉባኤ እንዲታይ ዋና ምክንያት የሆነው ከላይ እንደተገለጸው ይኸው ከፍል በዘመኑ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ማዕከል ሆኖ በመገኘቱ ነው። ጉባኤው ሲደረግ የመምህር አካለወልድ ንግግር ብቻ ነው የተሰማው

በጉባኤው አሉ የተባሉ መምህራን ሁሉ ነበሩ ግን በመካከላቸው ቃላትን እንደክርማ የሚለዋወቁ ነገረኞች ሰላም እንዳይነሱዋቸው ዝም ማለቱን መረጡ።

መምህር አካለወልድም ከሁለቱም ክፍሎች ጋር ጥቂት ቃላት ስለተለዋወጡ የሐሜት ሐረግ ተመዘባቸዋል። በጉባኤው አብሮ የተካፈለው ግብፃዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ጴጥሮስ ምንም ቃል አልሰነዘረም። ምሥጢረ ሥላሴን ያህል ከባድ የዶግማ ክፍል በሰማበለው ሊገባው እንደማይችል ግልጽ ነው። ሆኖም ይህ ጳጳስ አንዳንድ ተባራሪ ቃላትን እየሰማ በመምህር አካለ ወልድ ላይ ቅሬታ እንደነበረው ይነገራል። የዚሁ ጳጳስ ቅሬታ ውስጥ ውስጡን እያመረቀዘ ሄደ በመምህር አካለወልድና ከሱ በኋላ በተነሱ አቡነ ማቴዎስ ላይ መቀየየሞን አስከተለ መቀያየሙና መለያየቱ ከሐሜት ደረጃ አልዘለለም ምናልባት መምህር አካለወልድ ቦሩ ሥላሴ ሆነው አቡነ ማቴዎስ ደግሞ አዲስ አበባ ተቀምጠው ሲኖሩ፣ ግለሰቦች እየተመላለሱ በያሉበት ያልሆነ ነገር ያቀብሉዋቸው ኑረው ይሆናል። ሁለቱ /መምህር አካለወልድና አቡነ ማቴዎስ/ በአካል ተገናኝተው ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ያነሱበት ታሪክ አናገኝም። ነገር ግን መምህር አካለወልድ ወሎ ሆነው ለአቡነ ማቴዎስ ወደአዲስ አበባ እንደላኩት የሚነገርለት ጽሑፍ ተገኝቷል። ጽሑፉ ቀጥሎ ያለው ነው።

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አብን ወላዲ ወልድን ተወላዲ መንፈስ ቅዱስን ሠራዒ ምንም ለአጠይቆ አካላት በአካል ሦስት ስላልን በባሕርይ፣ በፈቃድ፣ በሕልውና አንድ አምላክ ብለን አምነን የሃይማኖትን ነገር እንጽፋለን።

አምላክ መለኮት፣ እግዚአብሔር ማለት የሦስትነት የአንድነት ስማቸውም ከአካላቸው ከባሕርያቸው አይለይም። ወአኮ እሉ አስማት ዘቦኡ ላእሌሆሙ ድሕረ አላእሙንቱ አካላት /ጎር ዘቄ አንድ/። ባሕርይም ከአካል እንዳይለይ ወምግባርኒ በሕላዌሁ ይትፈፀም ዝንቱ ፍሞሜ /ዮሐንስ ዘእስክንድርያ/። አምላክ በአካል ሦስት ሲሆን መቅድመ ኩሉ ነአምን በአሐዱ አምላክ ዘቦቱ ሠለስቱ አካላት አምላክ ውእቱ አብ፣ አምላክ ውእቱ ወልድ፣ አምላክ ውእቱ መንፈስቅዱስ /አትናቴዎስ አራት ክፍል/። ወአልቦ ካልእ አምላክ ውፁዕ እም ሠለስቱ አካላት /ሱንትንዮስ/። ወለእመለበውነ አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ ውእቱሰ አምላክ ወመለኮት ወሕላዌ ወአካል ዘምሰለ ገፅ...

መለኮቱም በአካል ሦስት ሲሆን ነአምን ኩሎ ዘተብሕለ በእንተ መለኮት ከመቦቱ ሠለሥቱ አካላት /ጎርጎር፣ ዘእንዚናዙ/። ወእሙን ይብል ከመእሙንቱ መለኮት /ዮሐንስ ዘእስክንድርያ/። እግዚአብሔር በአካል ሦስት ሲሆን ነአምን በእግዚአብሔር አብ፣ ወበእግዚአብሔር ወልድ ወበእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነአምሮ ለእግዚአብሔር በሠለስቱ አካላት /ጎርጎርዮስ/።

አሐዱ መለኮት ማለታችንም የአብ ወላዲነት የወልድ ተወላዲነት የመንፈስ ቅዱስ ሠራጺነት ከአብ አሰራጺነት አይለይምና ሰለዚህ ነው አንድ ማለታችን የወልድንም ተወላዲነት ከአብ ወላዲነት አይለይም አለመለየቱን፤ ...ኢየሐልቅ ልደቱ እምኔሁ /አግና/። የመንፈስ ቅዱስም ሠራፂነት ከአብ አሥራፂነት አለመለየቱን ከመነቅዕ እምነቅዕ /ቄርሎስ/ ቀዳማዊ፤ ዘእምቀዳማዊ /አግናጥዮስ/ ብለዋል። እኔም ከቅዱሳት መጻሕፍት የተለየ ቃል፤ አላስተማርኩም ደግሞም ይህን የመሰለ ብዙ አለ። አሁን ግን ነገሩ ሁሉ በወረቀት አያልቅም። በየጥቂቱ ጽፌአለሁ

ሦስት መለኮት የሚል ርጉም ነው። አሁንም ሦስት የሚል ርጉም ነው። አሁንም ሦስት መለኮት የሚል ከተገኘ አባታችን ያውግዙት። አባታችን እኔ ባልተናገርኩት ከፉ ስም ቢያወጡልኝ በዳኛው በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንቋቋማለን /31/።

3. <u>በደብረ ሊባኖስ ተገኘ ስለተባለው አካራካሪ መጽሐፍ</u>

የቤተክርስቲያን ወገኖች እግዚአብሔርን ለማገልገል ሲሰለፉ ፈተና ይደቀንባቸዋል። የፈተናው መንሥኤ አሉባልታ ነው። አሉባልታው ውሎ ሲያድር አካል ሠርቶ የአሉባልተኞች የስንፍናቸውና የሠይጣን ተገዢነታቸው ሽፋን በማድረግ ዓላማ ባላቸው ሰዎች ላይ ጉዳት ያደርሱበታል።

በመምህር አካለወልድና በአባ ማቴዎስ መካከል ለተፈጠረው ልዩነት መንሥኤው አሉባልታ ነበር። መምህር አካለወልድ በሩ ላይ ጉባኤ ተክሏው መጽሐፈ ሊቃውንትንና መጽሐፈ መነኮሳትን ከማስተማራቸው ሌላ ደቀመዘምርቶቻቸውን ሁለት ሁለት በማድረግ ወደየወረዳው እየላኩ ያካባቢው ወገኖች በአሚነ ክርስቶስ እንዲጸኑ ያደርጉ ነበር። ከሰዎች ለዚህ የተሠጣቸው መልስ ግን በመናፍቅነት መፈረጅ ነው። ጳጳሱ ምን እንደሚሉ ምን እንደሚያስተምሩ በትርብ ሳይረዱ ከአሉባልተኞች በቀረበላቸው የሐሰት ወንጀል ብቻ የጥላቻ መነፈስ በሳቸው ላይ አሳደሩ።

በእክሱሞችና በደብረ አባዮች የተጀመረው የሃይማኖት ክርክር ከትግራይ ወሎ ከዚያ አዲስ አበባ ዘልቆ በአዲስ አበባ ካህናትና በደብረሊባኖስ መነኮሳት መካከል መለያየትን አስከትሏል። ለመለያየታቸው ዋና መነሻ የአራቱ ማርያም ዋና አስተዳዳሪ በነበሩ አሊቃ መኮንን እጅ አንድ መጽሐፍ መገኘት ነው። መጽሐፉ ከሃይማኖተ አበው የተውጣጣ

የምሥጢረ ሥላሴና የምሥጢረ ሥጋዌ መግለጫ የያዘ ሆኖ የእጅ ጽሑፍ ነው። መጽሐፉ ሥላሴ በአካል ሦስት የሚለውን ሐረግ በብዛት እንደነበረው ይነገራል። በደብረሊባኖስ የሐዲሳት መምህር የነበሩ መምህር ፍስሐ በትውስት ደብረሊባኖስ አገቡት፣ ሦስት መለኮት የሚል መጽሐፍ ወደገዳማችን ገብቷል እያሉ አንዳንድ መነኮሳት ማጉረምረም ጀመሩ። አባ አፈወርቅ የተባሉ መነኩሴ መጽሐፉን ልመልከተው ብለው ከአባ ፍስሐ እጅ ወሰዱት። የመነኮሳቱ ማጉረምረም በመንበረ ፓትርያርኩ ተሰማ የነገሩን ምንነት ለመረዳት ከአዲስ አበባ አድባራት የተውጣጡ መምህራን በመንበረ ፓትርያሪክ ስብሰባ አደረጉ። ስብሰባው በጠቅላይ ቤተክህነት ባለሥልጣኖች መሪነት ነው የተካሄደው። ጉባኤው የተካሄደበት ወር ታህሳስ 1951 ዓ.ም መሆኑ ታውቋል። መጽሐፉ እንዲጠናና የጎደለ ነገር ካለው ተስተካክሎ በጎትመት ላይ እንዲውል የጉባኤው ተሳታፊዎች ወሰኑ። በፊርማቸውም አረጋገጡ። የጉባኤው ተሳታፊዎች በዚህ ውሳኔ እንዲስማሙ የተገደዱበት ምክንያት መጽሐፉን ያዘጋጁት ለመምህር አካለወልድ እጅግ ቀራቢ የነበሩ አለቃ ገብረመድኅን ያዘጋጁት መሆኑን ስላመኑበት ነው።

የጉባኤውን ውሳኔ የሰሙ አባ አፈወርቅ የደብረሊባኖስን መነኮሳት ሰብስበው ሦስት መለኮት የሚለው መጽሐፍ ይኸው በእሳት እንዲቃጠል ትስማማላችሁን? አሉ መነኮሳቱም ይቃጠል ሲሉ በአንድ ድምፅ ጮኹ። በዚሁ፣ መጽሐፉ ተቃጠለ። አለቃ መኮንን መጽሐፋቸው እንዲሰጡዋቸው ሲጠይቁዋቸው መምህር ፍስሐ መቃጠሉን ነገርዋቸው። መምሕር ፍስሐን ከሰው በከርከር እያሉ አለቃ መኮንን ሞቱ።

አለቃ መኮንን ከነአለቃ ይትባረክ መርሻ ጋር በመሆን መጽሐፈ ሐዊን ከግእዝ ወደአማርኛ የተረጎሙ ምሑር ናቸው። በሳቸው ተሳትፎ የተተረጎመው መጽሐፈ ሐዊ በቤተ መዘክር ይገኛል።

የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት መጽሐፉን ለማቃጠል የበቁት ክእንዳንድ ኢምሁራንና አሉባልተኞች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው በነመምህር አካለወልድ ላይ የተሠነዘረው ያልተስተካከለ ወሬ ስለተንአባረቀባቸው መሆኑ ‘ዮርዮር የለውም። መጽሐፉን ማቃጠል የሃይማኖት ጽኑእነትን ሳይሆን የሚያመለክተው የአርቆ አስተዋይነት ጉድለትን ነው።

ምዕራፍ 5

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምህራን ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በምሥጢረ ሥጋዊ ያሳዩት መለያየት

ክፍል 1. ጸጋ

ሀ. የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በምሥጢረ ሥጋዌ ክርክር አልተነሳም። ከ13 - 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ምሥጢረ ሥጋዌ ግእዝ በእግዝ ከሚተረጎሙ መጻሕፍት በመነሳት ይገለጽ ነበር። የቤተክርስቲያን ሥዕል ከፍተኛውን የመጻሕፍት ትርጉም እንደሚይዝ ይታወቃል። ሙሉ በሙሉ ምርምር ተካሂዶበታል ባይባልም እስከአሁን በተደረገው አንዳንድ ጥናት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥዕል በሦስት እንደሚከፈል ታምኖበታል። አንደኛው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበረው ሁለተኛው ከ16ኛው እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን ሦስተኛው ከ18ኛው እስከ20ኛው ክፍለ ዘመን ያለው ነው። ከ18ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የተሣሉ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥዕሎች የምዕራባውያን ተጽዕኖ እንደሚታይባቸው ተመራማሪዎቹ ይናገራሉ።

እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን መነኰሳት ሮም እየደረሱ ይመለሱ ነበር። ጎርጎርዮስ ዘመካነ ሥላሴ ከሦስት ጓደኞቹ ጋር ቅዱስ እስጢፋኖስ በተባለው የሮም ገዳም ለተወሰኑ ዓመታት ቆይቷል። አባ ጎርጎርዮስና ጓደኞቹ ወደሮም የሄዱት በኢየሩሳሌም በኩል እንደሆነ ታውቋል። መካነ ሥላሴ በግራኝ ዘመን ከፍተኛ ጥፋት ከደረሰባቸው የኢትዮጵያ ገዳማት አንዱ ነው። የመካነ ሥላሴ

መነኰሳት በግራኝ ተከታዮች ታርደዋል። አባ ጎርጎርዮስና ጓደኞቹ ክገዳሙ ጥፋት በፊት ሮም እንደሄዱ ይታመናል።

አባ ጎርጎርዮስ ያግእዝ ቋንቋ ችሎታው ከፍተኛ ነበር። ኢዮብ ሎዶልፍ የሚባል ጀርመናዊ ምሁር ለሊዊድን መንግሥት የሚያገለግል ሰነድ ፍለጋ ወደሮም ሄደ የፈለገውን ሰነድ አላገኘም። በአጋጣሚ ከአባ ጎርጎርዮስ ጋር ተገናኝና ግእዝ ተማረ። ሰውየው በችሎታው አባ ጎርጎርዮስን በጣም ወደደውና ለምኖ ወደአገሩ ጀርመን ወሰደው። ግእዝን ብቻ ሳይሆን አማርኛንም በጥሩ ሁኔታ ከእሱ ተማረ። የኢትዮጵያ ጥናት በአውሮፓ የጀመረው እሱ እንደሆነ ይነገራል። አባ ጎርጎርዮስ ከሮም ተመልሶ ወዳገሩ ኢትዮጵያ በመምጣት ላይ እያለ የተሣፈረበት መርከብ በሚዲቴራንያን ባሕር ስለሰጠመች በዚያው ሞተ። (32) በአፄ ናአድ በአፄ እስክንርና በአፄ ልብነ ድንግል ዘመን ከፖርቱጋል፣ ከአርመን፣ ከግሪክና ከተለያዩ፣ የእስያ አገሮች ብዙ የውጭ ዜጎች ወደኢትዮጵያ መጥተዋል።

ለ/ በግራኝ የሰለሙትን ኢትዮጵያውያን መመለስና የዜማ መጻሕፍት መስተካከል

ከ16ኛው አጋማሽ እስከ አሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ብዙ ቁም ነገሮች ተሠርተዋል። ብዙዎች ኢትዮጵያውያን በኃይል ተገደው ከገቡበት የእስልምና እምነት ተመልሰዋል። ብዙ አብያተክርስቲያናት ታድሰዋል። ደብረሊባኖስ መካነ ሥላሴ አትሮንስ ማርያም የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም መርጡለ ማርያም ጎሐ ጽዮን ማርያምና ዋሻ ሚካኤልን ጨምሮ 29 አብያተ ክርስቲያናት በአፄ ገላውዴዎስ ብቻ ታድሰዋል (33)። የሰለሙትን ወገኖች ለመመለስ ከፍተኛ ትኩረት ተሠጥቶት እንደነበር

የምንረዳው የመጽሐፈ ቄድር ከዓረብኛ ወደ ግእዝ በዚሁ ዘመን መተርጎም ነው። መጽሐፈ ቄድርን በንዝሐተ ማይና በንስሐ ብዙዎች ወደቅድስት ቤተክርስቲያናቸው እንዲመለሱ በዘመኑ የነበሩ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባቶች ተጠቅመውበታል።

ከአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት ላይ ብዙ የማስተካከል ሥራዎች እንደተካሄዱ ይታመናል። የማስተካከሉ ሥራ ያተኮረው በምልክት አቀማመጥ ላይ ነው። አዛዥ ሂራና አዛዥ ራዑኤል በዚሁ የዜማ ምልክት አስተካካይነት ግንባር ቀደም ሆነው ሲጠቀሱ ይኖራሉ (34)። በድጓው ውስጥ አዳዲስ ድርሰቶች የተጨመሩትም ቀጥሎ ባለው ጊዜ ነው። የአፄ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ይህና ሌሎችም የቤተክርስቲያን ሥራዎች ተከናውነውበታል (35)። ከዓረብኛ ወደግእዝ ብዙ መጻሕፍት የተተረጎሙት በአፄ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው። ጊዮርጊስ ወልደአሚድ በአፄ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ከተተረጎሙት መጻሕፍት አንዱ ነው። መጽሐፉን ከዓረብኛ ወደ ግእዝ የተረጎመው ቅብርያል ይባላል። ቅብርያል መዓርጉ ዲያቆን ነው። የግብፅ ተወላጅ እንደሆነ ከአንዳንድ ሰዎች ይነገራል (36)። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለሁለት መቶ ዓመታት ያህል (ከ4 - 6ኛው ክፍለ ዘመን) በዮናኒ (ፅርዕ) ቋንቋ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ስትጠቀም ቆይታለች። ከ6ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን መንፈሳዊ አገልግሎትም ሆነ መንፈሳዊ ትምህርት በግእዝ ብቻ እየተሰጠ ኖሯል።

የምዕራባውያን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የኢትዮጵያውያን መነኮሳት ወደምእራብ መመላለስና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጻሕፍት በአዲስ አሠራር በአማርኛ መተርጎም የተወለኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማመሥጠር ሲነሱ ግራ

የሚያጋቡ ነገሮች ያጋጠሙዋቸው ይመስላል። እነ አልፎንሶ የተሳሳተ የትምህርተ መለኮት ሥርጭት ቢያሳዩም ለጊዜው እንዲገታ ተደርጎ ነበር። እንቅስቃሴው የተገታው በአፄ ገላውዴዎስና በአፄ ሚናስ ነው። ከዚያ ወዲህ ለአጭር ጊዜ ሁኔታው ጋብ ብሎ ነበር። እስከ አፄ ያዕቆብ (1588 - 1595) ሃይማኖታዊ ውጣ ውረድ አልተከሰተም።

ሐ/ ከ1595 - 1674 የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

አፄ ያዕቆብን ገድሎ ሱስንዮስ ሲነግሥ መንፈሳዊው የቤተ ክርስቲያን ሥራ ተገታ። ሱስንዮስ 27 ዓመት ሙሉ በሥልጣን ላይ ተቀምጧል። አሥራ ስምንቱ ዓመታት የድብቅ ተንኮል የተሸረበባቸው ሲሆኑ ዘጠኙ ዓመታት ደግሞ አስከፊ የደም መፋሰስ የተካሄደባቸው ናቸው። ሱስንዮስ የካቶሊክን እምነት ለመከተል ሁለት ነገሮች እንደ ገፋፉት ይታመናል። አንደኛው በናቱ የፖርቱጋል ወታደር የልጅ ልጅ መሆኑ፣ ሁለተኛው አልፎንሰን ተቀብሎ የከብር ቦታ መስጠቱ ናቸው (37)።

በሱስንዮስ የዘጠኝ ዓመት ጦርነት ብዙ ሰዎች እምነታቸውን ለውጠው የምዕራባውያኑን እምነት ተቀብለው ነበር። ብዙዎቹ የካቶ ሊክን እምነት ተከታይነታቸውን ደብቀው እስከ ጳድቁ ዮሐንስ ድረስ ሊቆዩ ችለዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ ሱስንዮስ ከሥልጣን እንደወረደ በፋሲል ዘመን በይፋ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች መሆናቸውን ራሳቸው ስለተናገሩ ካሉበት ደብር እንዲባረሩ ተደርገዋል። በዚሁ ምክንያት ከአዘዞ ተክለሃይማኖትና ከሌሎችም የጎንደር አካባቢ አድባራት የተባረሩ ካህናት ብዙ ናቸው።

የሱስንዮስ የልጅ ልጅ አእላፍሰገድ ዮሐንስ (ጻድቁ ዮሐንስ) (38) በነገሠ በሁለተኛው ዓመቱ የካቶሊክን እምነት ስለተቀበሉ ኢትዮጵያውያን ጎንደር ላይ ጉባኤ ከፈተ። ጉባኤው በ1661 ዓ.ም ነው የተደረገው። ይህ ጉባኤ ምዕራባውያን አንድም ሳይቀር ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ወሰነ። ውሳኔው በሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጳጳስ ሆኜ መጣሁ በማለት ንጉሡን አታለለ። ንጉሡ እውነት መስሎት በክብር ተቀብሎ የክብር ቦታ ሰጠው። የሰውየው ስም ዮሴፍ አፍርንጊ ይባላል። ዮሴፍ አፍርንጊ ብቻውን አልነበረም ሌላም ተከታይ ነበረው። ብዙ ሳይቆይ አታላይነቱ ታውቆ "ሙይ" ወደተባለው ቤጌምድር ውስጥ ከተከታዩ ጋር ተወስዶ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ። በሃ ክርስቶስ የተባለ ኢትዮጵያዊ ካህን ደግሞ የካቶሊክን እምነት ተከታይ ሆኖ ስለተገኘ ንጉሡ የገዳማችንና የአድባራትን ካህናት ጠርቶ ጉባኤ ከፈተ። የጉባኤው ተካፋዮች ክርስቶስ ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ባሕርይ እንጂ ሁለት ባሕርይ አይደለም በማለት ማስረጃ እያቀረቡ ለማስረዳት ሞከሩ። እሱ ግን በነሱ ምክርና ተግሳጽ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም። "አሪንጎ" ወደተባለው ቦታ ተወስዶ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ። ስለ በሃ ክርስቶስ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ስለ መሆኑ የሚቀጥለውን የግእዝ ንባብ እንመለከታለን። "...ወካእበ ጥረከበ አሐዱ ብእሲ ዘኮነ ልደቱ በብሔረ ኢትዮጵያ ዘስሙ በሃ ክርስቶስ እንዘይከሕዶ ለክርስቶስ ወደሬስዮ ፪ተ ጠባይዓተ እስመተምህረ ትምህርተሙ ለእሉ ከሐድያን አፍሪጋውያን..." <u>አማርኛው</u> "በሃ ክርስቶስ በመባል የሚታወቅ አንድ ኢትዮጵያዊ ክርስቶስን ከዶና የፈረንጆችም ትምህርት ተቀብሎ ተገኘ"

መ/ <u>የመጻሕፍት ትርጓሜ በጎንደር</u>

የግእዝ ቋንቋ የኢትዮጵያውያን የሥነ ጽሑፍ ባለቤት እንደሆነ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ቆይቷል። የቤተክህነትና የቤተመንግሥት ደብዳቤዎች እስከዚሁ ክፍለዘመን ድረስ በግእዝ ብቻ ይጻፉ ነበር። የሁለቱ ክፍሎች (ቤተመንግሥትና ቤተክህነት) የሥነ ጽሑፍ አቀናባሪዎች የቤተክህነት ሰዎች ብቻ ነበሩ። በ17ኛው ክፍለ ዘመን በ4 ጉባኤ የተከፈሉት የቤተክርስቲያን መጻሕፍት በአማርኛ ተተርጎመዋል (39)። በዚሁ ጎን ለጎን ብዙ አድባራት በጎንደር ከተማ በመተከል ላይ ነበሩ። የአድባራቱ ብዛት 44 ደርሶ እንደነበር ይታወቃል። ብዙዎቹን አድባራት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ደርቡሾች ስላፈረሱዋቸው አሁን ያሉት ከሃያ አይበልጡም።

ከ44 አድባራት መካከል የትኛው መጽሐፍ በየትኛው ደብር እንደተተረጎመ በታሪክ ተመዝግቦ የተቀመጠ ነገር የለም። ጻድቁ ዮሐንስ ቤተመጻሕፍትን ከፍቶ ነበር። ለቤተመጻሕፍቱ የተሠራው አዳራሽ በዘመኑ የቤተክርስቲያን መምህራን እንደተጠቀሙበት ይታመናል። ከአንዳንድ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምህራን, እንደሚነገረው /...ቅዱሳት መጻሕፍት በአማርኛ ሊተረጎሙ የቻሉት ከፋሲል ግንብ ባንዱ አዳራሽ መምህራን እየተሰበሰቡ ባደረጉት ጥረት ነው። ነግሥታቱ መጻሕፍቱን ለሚተረጉሙ መምህራን ድጋፍ ከማድረጋቸውም በላይ የመምህራኑ ምግብ በቤተመንግሥቱ እየተዘጋጀ ቦጥንቃቄ ይቀርብ እንደነበር ይነገራል። ከሁኔታው መረዳት እንደሚቻለው ግን መጻሕፍቱ ባንድ ጉባኤ ወይም ባንድ ቦታ በተሰበሰቡ ምሁራን የተተረጎሙ አይመስልም። በእያንዳንዱ ደብር ብዙ ካህናት በትክለኝነት ተሰብስበው ነበር። በመጻሕፍት ትርጉም ብቻ ሳይሆን በቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ

አገልግሎት ሥርዓትም ብዙ ልዩነት አላቸው። የመጻሕፍት አተረጓጎምም የዚያን ያህል ተለያይቷል። በዶግማ የመለያየቱ ምክንያት ከእልፎኑስ መንጭቶ ቁርንጭኒ ተከለሃይማኖትና ኤዎስጣቴዎስ የተባሉ ሁለት ሰዎች በጎኗምና በሸዋ እንዳስፋፉት ብዙ ሰዎች ጽፈዋል (40)። ግን አባባሉ በፍጹም ስህተት ነው። ከአልፈኑስና ተከታዮቹ የካቶሊክን እምነት በግልጽ የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ከላይ ተገልጿል። ከዚህ አልፎ ግን ኢትዮጵያውያን ቅባት፣ ጸጋ በሚል የመለያየት ምክንያትን ከፈረንጆች ሊወርሱ አይችሉም። መለያየታቸው የተከሰተው 1ኛ. ለመጀመሪያ ጊዜ መጻሕፍትን በአማርኛ ለመተርጎም በመጀመራቸው 2ኛ. ተለያይተው የትርጉምን ሥራ በማካሄዳቸው፣ 3ኛ. ከመካከላቸው ቀደም ሲል የላቲንን ቋንቋ እያጠኑ ከሮም የተመለሱ አንዳንድ ምሁራን ኢትዮጵያውያን በመኖራቸው 4ኛ. የመጻሕፍትን ምሥጢር ጠልቀው ያልተረዱ ሰዎች በትርጓሜ መጻሕፍት ሥራ መሰለፋቸው 5ኛ. አንዳንድ የጎንደር ነገሥታት የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ማሳየታቸውና ሌሎችም ያልተጠቀሱ ምክንያቶች ለዶግማ መለያየቱ ዓይነተኛ ምክንያቶች እንደነበሩ መገንዘብ ይችላል።

ሠ. <u>ጸጋ የሚለው ቃል ለነማን እንደተሰጠና በየት እንደተሰፋፋ</u>

ክርስቶስ አውቆ ወዶ የሰውን ሥጋ ለብሶዋል። ስለዚህ ከጋጢአት በቀር ሰው የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ሠርቷል። ልደቱም ከአብና ከእመቤታችን ብቻ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጭምር ነው። የመንፈስ ቅዱስ ልደቱ የመከበር (የጸጋ) (በሕድረት ወይም በንሥአት) ነው እንጂ የባሕርይ ልደት አይባልም በማለት የተመሠረተ በጎንደር የመጻሕፍት አተረጓጎም ጊዜ ተከሰተ ይህን አባባል መሠረት ያደረጉ መምህራን

ቃልና ሥጋ መባረዝና መለያየት ሳይኖርባቸው በተዓቅቦ ተዋሕደዋል፤ ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት አይባልም እስመ ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ ብሏልና (ቄርሎስ) ካሉ በኋላ ወኮነ ወልደ በሐብት (አበው ኤራቅሊስ፣ ሳዊሮስ) የሚለው ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ ለኛም ለመላእክትም በኩር የተባለበት ያስረዳል። አብ ሰጭ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ወልድ ተቀባይ ናቸው። በዚሁም ክርስቶስ ኮነ ሰብአ ከማነ (41) የምንለው ከጋጢአት በስተቀር ሰው የሠራውን ሥራ ሁሉ ሠርቷል። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። እኛ ጽሕነትን ፈላጊዎች ነን መድኃኒቶች አይደለንም፤ ክርስቶስ ነቢይ ተብሎ ነቢያት፣ ሐዋርያ ተብሎ ሐዋርያት፣ ካህን ተብሎ ካህናት፣ ንጉሥ ተብሎ ነገሥት፣ ወልድ ተብሎ ውሉድ አሰኝቶናል። እነዚህ ሁሉ የሥጋ ሥራዎች ናቸው፤ በዚሁም በኩረ ምእመናን ይባላል ይላሉ።

በዚህ ትምህርት የተስማሙ ብዙ መምህራን ነበሩ። ነገር ግን ከዚህ አባባል የተለዩ ሌሎች ነበሩ። እነሱ ቅባት በሚል ሰያሜ የተጠሩ ናቸው። እነዚህ ቡድኖች አክራክሩን አሟግቱን በማለት ለሁከት የተሠለፉ ነበሩ። በአፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመነ መንግሥት ቅባቶች ጉባኤ ተክፍቶ የቅብአትን እምነት ካልተቀበሉ ሁሉ ጋር ከርክር እንዲያደርጉ ንጉሡን ይወተውቱዋቸው ጀመር። ቅብአቶች ውስጥ ውስጡን የሚያራምዱት የፖለቲካ አዝማምያም ነበራቸው። ሱስንዮስ የአፄ ኢያሱ ቅድመ አያት ነው። (ሱስንዮስ - ፋሲል - ጻድቁ ዮሐንስ /አእላፍ ሰገድ/ - ኢያሱ)

ይስሐቅ በመባል የሚጠራ አንድ ግለሰብ የሱስንዮስ ልጅ ነኝ ብሎ ተነሰቶ ነበር። በሃይማኖት ስም መነገድ መመሪያቸው ያደረጉ ቅባቶች ሕዝቡ አፄ ኢያሱን መከተል ትቶ ይስሐቅን እንዲከተል ቅስቀሳ

ጀመሩ። አፄ ኢያሱ ግን ነገሩ ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ደም ከማፍሰሱ በፊት ፖለቲካዊ መስመራቸውን አስተካክለው ሕዝቡ ሰሕተት መሆኑን ተረድቶ ይሰሐቅ የተባለውን ሰው መክተሉን እንዲያቆም አድርገዋል። ይህም የአፄ ኢያሱን ጠንካራ ጎድን ከሚያመለክቱ ፍሬ ነገሮች አንዱ ነው። "ከዚህ የበለጠ ሌላ ጠንካራ ጎድንም አላቸው" (አፄ ኢያሱ)

ሊቀ መንበር ሆነው ያከራከሩን እያሉ የሚያስቸግሩዋቸውን ቡድኖች የመንግሥት መሪ እንጂ የቤተክርስቲያን መሪ አለመሆናቸውን ገልጸው በርስት ወይም በሌላ የማኅበራዊ ኑሮ ዘርፍ የተጣሱበት ካለ በሥጋዊ ፍርድ ደረጃ ሊታይ እንደሚችል፣ የሃይማኖት ችግር ካለ ግን የታወቁ መምህራን ብቻ ተሰብስበው እንዲመለከቱት እንጂ ጉዳዩ እሳቸውን እንደማይመለከት አሰረድተዋቸው ነበር። ይህን የተመለከተ የግእዝ ጽሑፍ ከዚህ ቅጥሎ ቀርቧል /...ወአመ ሠላሳሁ ለጥቅምት ገብረ ጉባኤ በእንተ ነገር ዘሃይማኖት እስመተገአዙ ሰብእ ደብረ ሊባኖስ ዘቤተ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ምስለ ሰብአ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ንጉሥኒ ሰሚያ ነገሮሙ ምስለ አባ ሲኖዳ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ አባ ጸጋ ክርስቶስ ወምስለ ኩሎሙ መኳንንቲሁ ይቤሎሙ ኩሉ ነገር ዘሃይማኖት ዘትትገአዙ ቦቱ አንትሙ ይቁም ዘበስምዓ ኮኑ ዓቃቤ ሰዓት አባ አሠረክርስቶስ ወቀይስ አፄ አባ ማቴዎስ ከመቆመ በጉባኤ እመ ዘመነሐ ፀጌ አእላፍ ሰገድ አቡየ እመኒ ባእድ ነገር ብክሙ በምክንያተ ብሂለ ርስት ዘእገሌ ወእገሌ ይብቋዕክሙ ፍትሕ።

ወተሠጥው እሙንቱ ወይቤሉ ይኩን በከመ ትእዛዘ ንጉሥ ወሶቤሃ ከዊኖሙ ስምዓ በጽድቅ ወበርትእ ዓቃቤ ሰዓት አባ አሠረ ክርስቶስ ወቀደሰ ሐዲ አባ ማቴዎስ ነሠቱ ዓረፍተ ፅልእ ዘማዕከሎሙ

እሙ እሙንቱ ምሁራኑ መጻሕፍት ወማዕምራኑ ነገረ ሃይማኖት ዘቆመ በጉባኤ እመዘመነ ሐፀጌ እእላፍ ሰገድ።

አማርኛ ...የደብረ ሊባኖስ ሰዎች ከአባ ኤዎስጣቴዎስ ሰዎች ጋር ክርክር ስላነሱ ንጉሡ ጳጳሳቱ አባ ሲኖዳ ከእጨጌው አባ ጸጋ ክርስቶስና ከመላ መኳንንቱ ጋር በመሆን ጥቅምት ሠላሳ ቀን ጉባኤ አደረገ፣ የምትከራከሩበት ነገር ሁሉ ዓቃቤ ሰዓት አባ አሠረ ክርስቶስና ቀይስ አፄ አባ ማቴዎስ በሚወስኑት ውሳኔ ይለቅላችሁ። ከሃይማኖት ውጭ የሆነ ነገር ካላችሁ ወይም የእገሌ የእገሌ ርስት እደላችሁ የምትጣሉበት ነገር ካለ ፍርድ ይዳኛችሁ አላቸው። ሁለቱ የተጣቀሱት መምህራን መጻሕፍትን የቋጠሩና የሃይማኖትን ነገር ጠንቅቀው የሚያውቁ ስለሆነ የንጉሡን ትዕዛዝ ተቀበሉ። ዓቃቤ ሰዓት አባ አሠረ ክርስቶስና ቀይስ ሐፀጌ አባ ማቴዎስም የእውነት ምሥክሮች በመሆን በሁለቱ ወገኖች የተጋረጠውን የጠብ ግድግዳ አፈረሱ። እነዚህ ሁሉ መምህራን ከዚያ በፊትም በአእላፍ ሠገድ (ጻድቁ ዮሐንስ) ዘመን በተደረገው የሃይማኖት ጉባኤ መጻሕፍትን በማብራራት መልካም ውጤት ያሳዩ ናቸው (42)።

ይህ ገፀ ንባብ በሃይማኖት ለሁለት ተከፋፍለው የቆዩ ሁለቱ ከፍሎች መጠላታቸውን አስወግደው ለመስማማት እንደቻሉ ያመለክታል። ግን ከሱ ጋር የተያያዘ ሌላው ጽሑፍ ደግሞ በዚሁ ሊስማሙ ስላልቻሉ የቆስጠንጢኖስን ምሳሌነት እየጠቀሱ ንጉሡ የመራው ጉባኤ ካልተከፈደ መፍትሔ አናገኝም በማለት ንጉሡን ፅሪፍት እንደነሱት የሚገልጽ ታሪክ ተጽፏል። ንጉሡ የቅባቶችና ካሮች ቅጥ ያጣ ግትርነት የአመራር ችግር ይፈጥርብኛል ብለው ስለሠጉ በታላቅነቱ የሚነገርለትን ጉባኤ ለበሰቡ አባ እደክርስቶስና አባ ኒቆላዎስን ጨምሮ ስምንት

የአዘዘና የደብረ ሊባኖስ ምሁራን በቅባት የባሕርይ ልጅ ሆነ የሚለውን የቅባቶች ትምህርት ለመቃወም አፈጉባኤዎች ሆነው ሲነሱ አባጥበበና አባ ሥልጣነ ክርስቶስን ጨምሮ አራት የቤተ ኤዎስጣቴዎስ መነኮሳት ቅባትን ወክለው አፈ ጉባኤዎች ሆኑ።

አፄ ኢያሱ ግራ ቀኙ "ተጠየቅ፣ ልጠየቅ" የሚለውን የዘመኑ የሙግት ፎርሙላ ከማንሳታቸው አስቀድሞ ቸርደም የተባለው ሊቅ ሁለቱን ከፍሎች ሊያስማማ የሚችል ትምህርት እንዲሰጥ አዘዙት። ቸርደሞም በመድረክ ላይ ቆሞ ትምህርተ መለኮትን ያቀፈ አስደናቂ ትምህርት ሰጠ። ትምህርቱ የተሰጠው በግእዝ ብቻ ነው። ከዚሁ ትምህት ተጽፎ የተገኘውን በከፊል ቀጥሎ ቀርቧል።

"...ከመተቀብአሂ ሕይወቶ መንፈስቅዱስ በሰብእናሁ እግዚአብ ሔር ቃል ይቤ ቄርሎስ ለሊሁ ውእቱ ዘይቀብዕ ርእሶ በመንፈሱ ባሕቲቱ፤ ዳዊትኒ ኅበ ይብል በእንተዝ ቀብአከ እግዚአብሔር አምላክከ ወልድየ እንተ ወአነኦም ወለድኩከ አንስ ተሰየምኩ ንጉሠ በላዕሌሆሙ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመሚመቱ ለመልከ ፄዴቅ፣ ኢሳይያስኒ ይቤ ኅበይብል ትወፅዕከትር እምሥርወ እሴይ ወየዓርግ ፅጌ እምኔሃ፣ ወየሐድር ለእሌሁ መንፈሰ እግዚአብሔር መንፈሰ ጥበብ መንፈሰ ምክር መኃይል ጴጥሮስኒ ኅበይብል ወቀብአ እግዚአብሔር መንፈስቅዱስ ወኃይለ አማን አንገለጉ አሕዛብ ለእለቅዱስ ወልድከ ዘቀባዕኀሁ፤ ወረሰዮ መሲሖ ዮሐንስኒ ኅበይብል እስመ አኮ በመሥፈርት ዘይሁብ እግዚአብሔር መንፈሶ፤ ወኑ ውእቱ ሐሳዊ ዘእንበለ ዘይከህድ ወይብል ከመኢየሱስ ኢኮነ መሢሐ ሙሴኒ ኅበ ይቤ ያነሥእ ለክሙ ነቢየ አምአሐዊክሙ ዘከማየ፤ ለሊሁኒ እግዚእነ ኅበ ይቤ በወንጌለ ሉቃስ ኢይደልዎ መዊት ለነቢይ በእፍአ ዘእንበለ በኢየሩሳሌም፣ ለሊሁኒ

እግዚእነ ኅበይብል በወንጌለ ዮሐንስ አብሰ ኢይኬንን ወኢመነቢ ኮነኒሁ ዘፈቀደ ተውህበ ሊተ ኩነኔ ሰማይ ወምድር ሳሙሎሽ ኅቡዓንሰ እንበይነዝኒ ርቱዕ ይትመሰሎሙ ለአሐዊሁ በኩሉ ከመይኩኖሙ መሐሬ ወሊቆን ካህናት ምእመነ ለመንገሌ እግዚአብሔር ከመይሰረይ ሐጢአተ ሕዝብ ሠርዓ ይኩን በአምሳለ ወልዱ ከመይኩን ውእቱ በኩረ በላእለብዙኃን አሐው፣ ቄርሎስኒ ኅበ ይብል ለቋላድዮስ ከመዝ ተሠሞየ ነቢየ ወሐዋርያ ወሊቀ ካህናት እንዘ ዋሕድ ኮነ በኩረ በላእለብዙኃን (43)።

የቸርደም ትምህርት ከሊቃውንት ውስጥ ቄርሎን ብቻ ነው የጠቀሰው ከሃይማኖተ አበው ግን ምንም የጠቀሰው ነገር የለም ከመዝሙረ ዳዊት፣ ከትንቢተ ኢሳይያስና ከሐዲሳት ብቻ የተውጣጣ ሆኖ እናገኘዋለን። በዘመኑ የመጻሕፍት በአማርኛ መተርጎም ታሪክ ቢነገርም በአማርኛ ትምህርት መሥጠት ግን የተለመደ እንዳልነበር ከዚሁ ለመረዳት እንችላለን። የረቀቀ ምሥጢርን ያዘሉ ኃይለ ቃላት ብቻ ጥቅሶች ናቸው በዚሁ ትምህርት የሠፈሩት። ምናልባትም የመጻሕፍትን ምሥጢር በሰከነ አእምሮ ያልተረዱ ጥራዝ ነጠቆች አማርኛውን በማጣመም ፈተና ውስጥ እንዳይከቱዋቸው መምህራኑ ይሠጉ ኑረው ይሆናል። (44)።

ጸጋ የሚለው ቃል አልፎ እያመለጠ በመውጣት ለወሬ ያህል የሚነገር እንጂ ይህን ያህል ግልጽ የሆነ መለያየት ተነሥቶ ለጉባኤ ሲበቃ አልታየም የቸርደም ትምህርት ይህንኑ እንደሚደግፍ ምሑራን ይናገራሉ። ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው አገላለጹ እጅግ የረቀቀ በመሆኑ ለነገር የተሰለፉ ግለሰቦች ከዚሁ ውስጥ አንዲት እንኳ ለመንቀፍ አልደፈሩም በጉባኤው የተካፈሉ ሁሉ ትምህርቱን በአድናቆት

ለመቀበል ተገደዱ። ከዚያም አልፈው ስለምሥጢረ ሥጋዌ ከዚሁ ትምህርት የተለየ ሐሳብ ያለው ካለ የተወገዘ ይሁን እያሉ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ሁሉ ገዘቱ። የቸርደም ትምህርት ለጊዜው ነገሩ እንዲረግብ ቢያደርግም እያደር የቅባቶች በሽታ ከማገርሸት አልዳነም። ዝርዝር ሁኔታው በሚቀጥለው ክፍል ይገለጻል።

የጸጋ ትምህርት ከጥንት ጀምሮ በላሊበላ፣ በዙራምባ፣ በቤተልሔም፣ ተድባበ ማርያም፣ ደብረ ሊባኖስና ሸዋ ውስጥ አንኰበር ዙሪያ በጣም ተስፋፍቶ ነበር። ሦስት ምሑራን መነኰሳት ከተድባበ ማርያም ወደ ደብረ ሊባኖስ በመጡ ጊዜ የጸጋ እምነት ምንነት ገሐድ ወጣ ሦስቱ መነኰሳት ለጊዜው በደብረ ሊባኖስ ተቀባይነትን አላገኙም ከገዳሙ ተባረሩ። ጊዜው 18ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነበር። እነዚህ መነኰሳት ከገዳሙ ለመባረር ያበቃቸው የትምህርት አቀራረብ /... ቃል ከሥጋ ጋር ከተዋሐደ በኋላ አንድ አካል እንጂ ሁለት አካል አይባልም ያለመለወጥ ያለመበረዝ (ያለመደባለቅ) በተዓቅቦ ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ ማለት ነው። ስለዚህ ክርስቶስ የሚለው ቃል የወልድ በኩረ ምእመናንነት ስም ነው የሚል ትምህርት ስላስተማሩ ነው።

መነኰሳቱ ከሸዋ ሳይወጡ ባንድ ዋሻ ተቀመጡ በወቅቱ የሸዋ መስፍን አምሐ ኢየሱስ ይባል ነበር። አቶ አምሐ ኢየሱስ (1733 - 1767) ሦስቱ መነኰሳት የመጽሐፍ ሊቃውንት መሆናቸውን ስለተረዳ ካሉበት ዋሻ ድረስ በመመላለስ ተዋወቃቸው። ከሦስቱ አንዱ አስፋወሰን የተባለውን ልጅ እንዲያስተምርለት አደረገ። አስፋወሰን ከምሑሩ መነኩሴ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ተምሯዋል። ሁለቱን ጉባኤያት ብሉይንና ሐዲስን አጠናቅቆ ማወቁ ይነገርለታል።

አምሐ ኢየሱስ ሲሞት አስፋወሰን የመሥፍንነቱን ሥልጣን ተረከበ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ቅባዓት የሚሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ የመክበር ትርጉም እንዳላቸው መሠረት ያደረገ የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት እንዲቀበሉ የደብረ ሊባኖስን መነኰሳት ያግባባቸው ጀመር። ትምህርቱን ከተቀበሉ ከጥንት ጀምሮ የተሰጣቸውን ሲሦ መንግሥት እንደሚመልስላቸው ቃል ገብቶላቸዋል። ደብረ ሊባኖሶች አባባሉን በደስታ ተቀብለው በሥራ ላይ አዋሉት። ትምህርቱንም አስፋፉት ከዚያም አልፈው ለአዘዞ፣ ለቤተልሔም፣ ለጣና ቂርቆስ፣ ለጸጋ እስጢፋኖስ፣ ለዙራምባ፣ ለላሊበላና ለጎንደር በማጎፅነ ማርያም ከመንፈስ ቅዱስ ከብርን (ጸጋን) ተቀብሎ ወልድ በኩረ ምእመናን ሆኗል የሚለው ትምህርት የቀና ሆኖ ስላገኘነው እናንተም እንድትቀበሉት በማለት ደብዳቤ ጽፈው ላኩ (45)።

ረ. በራስ ጉግሣ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ጸጋ የተደረገ ጉባኤ

ራስ ጉግሣ በዘመነ መሳፍንት ከ1791 - 1818 የነበሩ መስፍን ናቸው። በሳቸው ዘመነ ምስፍና ካሮችና ጸጎች ክርክር መግጠማቸው ተጽፏል። የካሮች አፈ ጉባኤ አለቃ ኅሀሱ የጸጎች አፈ ጉባኤ አለቃ ወልደ አብ የቅባዓት አፈጉባኤ አዛዥ ላሚሕ ነበሩ። ፀጎችና ቅባቶች በአንድ ወገን እንደቆሙ ይነገራል። ነገር ግን የቅባዓት ትርጉም በመካከላቸው ከፍተኛ ልዩነት እንዳለው ይታወቃል። ተደጋግሞ እንደሚነገረው ቅባዓቶች አካላዊ ቃል የባሕርይ ክብሩን ካጣ በኋላ እንደገና በቅባዓተ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ሆነ ስለሚሉ ፀጎች ፍፁም ክህደት ነው ይሉታል፣ ያወግዙታልም። ስለዚህ ሁለቱ ተቃራኒዎች በአንድ ሊሰለፉ የቻሉበት ምክንያት እጅግ አጠራጣሪ ነው። በክርክሩ ላይም የቃል

ምልልስ የተለዋወጡት ፀጋን የወከሉት አለቃ ወልደ አብና ካሮችን የወከሉት አለቃ ሣህሉ ብቻ ናቸው። ሁለት ልደት እንጂ እንዴት ሦስት ልደት ትላላችሁ ብለው አለቃ ሣህሉ አለቃ ወልደ አብን ቢጠይቋቸው ሁለት ልደት እንዳለ ሆኖ ሦስተኛው ልደት ወልድ በማኅፀነ ማርያም ከመንፈስ ቅዱስ የተወለደው የመክበር ልደት ነው፣ ይህም ልደት ንሥአት፣ ሕድረት ይባላል። በዚሁም ልደት ዳግማይ አዳም ተብሏል። በአዳም የተወሰደውን ልጅነት በንሥአት (ሕድረት) ከመንፈስ ቅዱስ ተቀብሎታልና። ስለዚህ ከሁለቱ ልደታን ሦስተኛው ልደት ልዩ ነው ብለው መለሱ።

ቅባትን ወክለው የቆሙ አዛዥ ላሚህ ለኔም ጥያቄ ይድረሰኝ ስላሉ ሃይማኖትዎ ምንድር ነው ተብለው ተጠየቁ ለሊሁ ቀባኢ መለሊሁ ተቀባኢ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ እላለሁ አሉ። ማነው ቀባኢ ቢባሉ መንፈስ ቅዱስ አሉ። ሲያከብረው በተዋሕዶ ነው። በሕድረት ሲባሉ "ጥዩቀ አንከ ያእምሩ ቤተእሥራኤል ከመእግዚአኒ ወመሲሐኒ ረሰዮ እግዚአብሔር ለውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአንትሙ ሰቀልክምዎ"

<u>አማርኛ</u> "...እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእሥራኤል ወገን ሁሉ በርግጥ ይወቅ (46)። የሚለውን ጠቀሱ ተብሎ በታሪክ ተመዝግቧል። በርግጥ ለሊሁ ቀባኢ ወለሊሁ ተቀባኢ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ የሚሉት ቅባቶችና ጸጎች ብቻ ናቸው። ይህን ለአዛዥ ላሚህ የቅብዓት ተከታይ የተሰጠው ጥያቄና መልስ በፍፁም ቅባቶችን አይመለከትም"

ስለዚህ ታሪክ መዝጋቢዎች ከዚህ ላይ የተምታታባቸው ይመስላል። ምክንያቱም የፀጎቹን አባባል ነው ለቅባቶች ሲሰጡዋቸው

የሚታየው። ይህ ክርክር በደብረታቦር ኩተማ ነው የተካሄደው ግን በጉባኤው የተወሰነ ነገር የለም። ያለውጤት ተዘግቷል (47)።

ስለፀጋ እምነት ክርክር በደብረታቦር ለመጀመሪያ ጊዜ ቢደረግም ከዘመነ መሣፍንት ጀምሮ ሰፊ ቦታ የያዘው በሸዋ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው የሸዋ መኳንንት እምነቱን ስለተቀበሉት ነው። ደብረ ሊባኖሶች እንኮበሮችና ሌሎችም የሸዋ አድባራትና ገዳማት አንድ ሆነው ተቀብለውት ነበር (48)። ከዘመነ መሳፍንት ጀምሮ ብዙ የሸዋ መጻሕፍት መምህራን አተረጓጎማቸው የፀጋ እምነትን መሠረት ያደረገ ሆኖ እንደቆየ ይነገራል።

ራስ ዓሊ የጎንደር መስፍን ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የሸዋ ንጉሥ በነበሩ ጊዜ ፀጋና ካራ ለሁለተኛ ጊዜ በጎንደር ጉባኤ አድርጓል። ንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ የሚጣቱ አማኑኤል አለቃ በነበሩት አለቃ አሥራት የሚመራ አራት መቶ አባሎች ያሉት የመልእክተኞች ቡድንን ወደጎንደር ላኩ። ማንና ማን እንደተከራከሩ የከርከሩ ርእሰ ምን እንደነበር የተገለፀ ነገር የለም። ከሸዋ የሄዱ መምሕራን ላቀረቡላቸው ጥያቄ አባ ሰላማ መልስ እንዳጡ ብቻ ተገልጿል። አባ ሰላማ መልስ በማጣታቸው ከሸዋ በሄዱ መምህራን ግፊት ወደ ሰሜን እንዲሰደዱ ተደርጓል (49)።

4ኛ/ <u>በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ስለጸጋ</u>

አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ተከለሃይማኖት ቅባትን ከጎጃም ንጉሥ ምኒልክ ፀጋን ከሸዋ እንዲያጠፉ መመሪያ ሰጥተው ነበር። አፄ ምኒልክ ከጥንት አባቶቻቸው ጀምሮ ታላቅ ክብርና ድጋፍ ይደረግላቸው የነበሩትን ፀጎች በሙሉ ልብ ይደግፉ እንደ ነበር ተረጋግጧል። በኋላ እነሱን የጠሉበት ምክንያት አልታወቀም። በአፄ ዮሐንስ መሪነት

የተካሄደው ጉባኤ በቦሩ ሜዳ መደረጉ ይታወቃል። ደሴና ቦሩ ብዙም አይራራቁም። በግራኝ ዘመን የሰለሙትን የወሎ ነዋሪዎች ወደክርስትና ለመመለስ ሲባል ብዙ የታወቁ መምህራን በቦሩና በደሴ እንዲቀመጡ ተደርጎ እንደነበር በምእራፍ ሦስት ተገልጿል። ቦሩ ሜዳ የዘመኑ የሃይማኖት ጉባኤ ማዕከል እንድትሆን የተደረገበት ምክንያት በሦስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፤ አንድ የሲቃውንት ማዕከል ሆኖ በመገኘቷ፣ ሁለት ለአፄ ዮሐንስና ለአፄ ምኒልክ አማካይ ቦታ መሆንዋ ሦስት ንጉሥ ሚካኤል የክርስትናን እምነት ከተቀበሉ ጀምሮ በክርስቲያናዊ ፍቅር የተቃጠሉ ስለነበርና አፄ ዮሐንስም ከልብ ይወዱዋቸው ስለነበር የጉባኤው በሳቸው ቦታ መከሄድ ክርስቲያናዊ ሞራላቸው ከፍ እንዲል ለማድረግ የሚሉ ይሆናሉ።

የቦሩ ሜዳ ጉባኤ ከመጀመሩ አስቀድሞ ዙራምቤ እንግዳ ዋልድቤ እንግዳና ተክለአልፋ የተባሉ ምሑራን ጸንቶ ናቸው ተብለው ስለታመሙ ከያሉበት ታድነው ታሠሩ። ተክለአልፋ ደብረሊባኖስ ላይ ተቀምጠ መጻሕፍትን በማስተማር ላይ ነበር። የታሠሬው በአፄ ምኒልክ ትእዛዝ ነው። የቦሩ ሜዳ ጉባኤ የኢትዮጵያ መምህራን ግልጽ የሆነ ውይይት እንዲያካሂዱበት እድል የሰጠ አልነበረም። የሃይማኖት ክርክርም አልተደረገበትም። የጉባኤው መግለጫ መግቢያ ማርቆስ አባቴ እስክንድርያ እናቴ የማይል ክርስቲን አይደለም የሚል ነበር። ስለሥስት ልደትና ሁለት ልደት ባሕል በፍጹም ለክርክር አልቀረበም። ከብሉይ ክሐዲስና ከመጽሐፈ ሊቃውንት ኃይለቃላት እየተጠቀሱ ጉባኤው የትምህርት መድረክ ሊሆን ይችል ይሆናል፣ ብለው አንዳንድ መምሕራን በታላቅ ተስፋ ጠብቀውት ነበር እየተባለም ይነገራል ግን አልሆነም።

የጉባኤው ሁለተኛ መመሪያ ሆኖ የቀረበው ስለእስክንድርያ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት ምሥክርነትን መያዙ የሚነገርለት ደብዳቤ ነበር ደብዳቤውን ያስመጡት አፄ ዮሐንስ ሲሆኑ በዓረብኛ ቋንቋ ተጽፎ መጥቶ እንደገና በሀገራችን ቋንቋ መተርጎሙ ይነገራል። የተተረጎመበት ቋንቋ አማርኛ ነው። ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ስለሃይማኖታቸው ምንነት መረዳት በትክክል የተሳናቸው ብዙ ግብጻውያን ጳጳሳት ወደኢትዮጵያ መጥተዋል። በአፄ ዮሐንስ ዘመን ከግብጽ የመጣው ደብዳቤም ተመሳሳይ ችግርን ያዘለ እንደነበር ብዙ የሚያሻሙ ዓረፍተ ነገሮች እንደ ነበሩት ይነገራል። ከዓረብኛ ወደ ግእዝ ወይም ወደ አማርኛ ሲገለበጥ ደግሞ ችግሩ እየጎላ እንደሄደ ይገመታል። ደብዳቤውን የላከው ግብጻዊው ፓትርያርክ አባ ቄርሎስ ነው (50)። የደብዳቤውን ፍሬ ነገር ዙራምቤ እንግዳ፣ ዋልድቤ እንግዳና ሌሎችም ሳይቀበሉት እንደቀሩ ነው የሚነገረው ዋልድቤ እንግዳ ሁለት እጆቹና ሀለት እግሮቹ ተቆርጠ ቁስሉ እያመረቀዘበት ተሰቃይቶ ሞተ። ዙራምቤ እንግዳ በበኩሉ የደብዳቤውን መንፈስ በመቀበሉ ከመቄረጥ ተርፎ ነበር። ነገር ግን ከራስ አሉላ ጋር በመነጋገር እያለ የሕዝብን ክብር የሚነካ ቃል ስለተናገረ ምላሱ ተቆረጠ።

ብላቴን ጌታሕሩይ ወልደሥላሴ ታሪኩን ለየት ባለመንገድ ያስቀምጡታል። እንደሳቸው አቀራረብ በቦሩ ሜዳ የተሰለፉት አብዛኛ ዎቹ የሸዋ ሊቃውንት ነበሩ። ከግብጽ መምጣቱ የሚነገርለትን ደብዳቤ ሐሳብ ካልተቀበሉት ምሑራን መካከል ሦስቱ ምላሳቸውን ሲቆረጡ አይተው እጨጌ ቴዎፍሎስ በንዴትና በቁጣ፣ "መጽሐፍ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት ይደልወነ ንክሳው ደመዚእነ ወእኮ ደመካልእን" (መጽሐፍ ስለቀናች ሃይማኖት ደማችንን እንጂ የሌላ ደም ልናፈስ አልታዘዝንም

ይላል) ብለው ስለተናገሩ የሰዎችን ምላስ፣ እጅና እግር የመቁረጡ ተግባር ተገታ በማለት ታሪኩን ገልጸውታል (51)።

ከዓረብኛ ወደአማርኛ ከተገለበጠው የግብጽ ደብዳቤ በስተመጀመሪያው የሠፈረለው ጽሑፍ መካከል የሚከተለውን እናገኛለን "...የተላከ ከአባ ቴርሎስ ዘነበረ በመንበረ ማርቆስ ይድረስ ከልጄ ከወዳጄ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። በኢትዮጵያ ካሉ ምእመናን ሁሉ ልጆቼ ወዳጆቼ ከእኔ በፊት ከነበሩት አባቶቻችን ሃይማኖትና ምግባር የጸና ሰው ፀጋ እግዚአብሔር ትደርበት አምላክ ማርቆስ ይጠብቀው... ቀዳማዊ ልደትን ከአብ ደሐራዊ ልደትን ከድንግል ማርያም ለኛ ሲል እንበለ አባት እንደተወለደ የማያምን ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ፣ ወልድ በተለየ አካሉ ቅብዕ ነው በሰውነቱ የባሕርይ አምላክ በሰውነቱ እንደ አብ እንደመንፈስ ቅዱስ ያውቃል... የማይል ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ በቅብዓት የባሕርይ ልጅ የሚል የአርዮስ የንስጥሮስ የይሁዳ መርገም ይደርበት ከምእመናን የተለየ ይሁን..." (52)

ብላቴን ጌታ ሕሩይ ወልደሥላሴ የቦሩ ሜዳ ጉባኤ ለይምሰል ብቻ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የተካፈሉበት ግልጽ ውይይት ያልተካሄደበት አስቀድሞ በተነበበው ደብዳቤ ብቻ ተመርኩዞ ከደብዳቤው መንፈስ የወጣ አስተሳሰብ ያለው ሰው ማንም ይሁን ማን መወገዝ፣ መባረርና መቀጣት አለበት ተብሎ በተነገረው አዋጅ ብቻ የተደመደመ በማለት ይገልጹታል።

ከቦሩ ሜዳ ጉባኤ ወዲህ ወልድ በማህፀነ ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ከበረ የሚሉ አንድ ሰው ብቻ ተገኝተው ነበር። አባባላቸውን እንዲለውጡ ከባለሥልጣኖች ብዙ ማስጠንቀቂያ ቢደርሳቸውም የሚከተ

ሉትን እምነት ለመለወጥ ፈቃደኛ ስላልሆኑ አዜ ምኒልክ በ1883 ዓ.ም ጉባኤ ሠርተው እንዲለዩ አድርገዋቸዋል። ሰውየው አለቃ ኸቴ ይባላሉ።

ክፍል 2 ቅብዓት

የቅብዓት እምነት ሦስት ክፍል ነበረው። አንደኛው ክፍል በፋሲል ዘመን የነበረ ሲሆን፣ መጽሐፍ "አንደየ ርእሶ" ስለሚል ቃል በተዋሕዶ ጊዜ /ከሥጋ ሲዋሐድ/ የባሕርይ ክብሩ አጣ፤ ለቀቀ፤ ሲቀባ ወደጥንት ክብሩ ተመለሰ በሰውነቱም በአምላክነቱም አንድ ወገን በቅባት የባሕርይ ልጅ ሆነ ይላል። ይህን ያመነጩት እነዘኢየሱስ ናቸው /53/። ሁለተኛው ክፍል ዜጎ የሚለውን አጥብቆ የሚቃወም ሆኖ እስመ ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ ይላልና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል ሆነ እንጂ የአምላክነትን ክብር አላገኘም ሲቀባ ግን ክብር ተላልፎለት ተፈጥሮ ተገብሮ ጠፍቶለታ በቅባት የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ ሆነ ይላል፤ ይህን ያመነጩት እነ አካለክርስቶስ ናቸው። ሦስተኛው ክፍል በሁለቱም ሁሉ በተዋሕዶ ከበረ፣ በቅብዓት ከበረ ይላልና ቅባት ያልተዋሕዶ ተዋሕዶ ያለቅባት ለየብቻቸው አያከብሩም። በተዋሕዶና በቅብት ባንድነት የአምላክነትን ክብር ከብሮ የባሕይ ልጅ ሆነ የሚል ነው /54/። የቅባቶች አባባል ካሮችም ሆኑ ፀንቶ የከሀደት ትምህርት ነው ይሉታል፤ እጅግም ይጸየፉታል። ስለቅባት የተደረጉ ጉባኤዎች ጥቂቶች አይደሉም።

ሀ. በፋሲል ዘመን ስለቅብዓት የተደረገ ክርክር

በፋሲል ዘመን ቅብዓት የሚለውን ቃል በተሳሳተ መንገድ ስለተረጎሙ ሰዎች ጉባኤ መደረጉን አንዳንድ የግእዝ ጽሑፎች

ይጠቁማሉ። የጉባኤው ሊቀመንበርና አፈጉባኤ እነማን እንደነበሩ አይታወቅም። የሆነ ሆኖ አዳም ዘእንፍራዝ ተዋሕዶዎችን ወክሎ ዕውር ዘኢየሱስ ቅብዓቶችን ወክሎ ስለተከራከሩ አዳምዘእንፍራዝ ረታ ዕውር ዘኢየሱስ ተረታ በማለት የጻፉ እሱ /45/።

አዳም ዘእንፍራዝና ዕውር ዘኢየሱስ በፋሲል ዘመን እንደተከራከሩ የሚገልጽ የግእዝ ጽሑፍ አለ። አዳም ዘእንፍራዝ ፀጎችን ወክሎ እንደተከራከረ አባ ወልደሥላሴ በጻፉት አንቀጸ አሚን የተባለው መጽሐፍ ተገልጿል። ይህን በተመለከተ ከተጻፈው የግእዝ ጽሑፍ የሚከተለው ይገኛል ... ወእምድሕረ ተሥዕረ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ተንሥኡ ዳግመ እሉ መናፍቃን ወሶበሰምዓ ንጉሥ ፋሲለደስ ዘውእቱ ዓለምሰገድ ዘንተ ነገረ ገብረጉባኤ ወአስተጋብኦሙ ለኩሎሙ ሰብአ ደብረሊባኖስ ወቆሙ ቅድመንጉሥ ወተስእሎሙ አሐዱ መምሕር እምሰብአ ደብረሊባኖስ ዘይብልዎ አዳም ዘእንፍራዝ ለእሉ መናፍቃን ወይቤሎሙ ምንት ውእቱ ሃይማኖትክሙ በእንተ ተዋሕዶ ወቅብዓት አውስአ ሊቀጉባኤሆሙ ዕውር ዘኢየሱስ ወይቤ አመተዋሐደ ቃል ምስለ ሥጋ ኮነ ነዳየ ባሕርይ፤ ወሐጥአ ብዕሎ ወአመተቀብአ መንፈስ ቅዱስ ከብረ ወኮነ ከመዝ ነአምን ወተሠጥዎ ዝንቱ መምሕር ወይቤሎ አኮ ሃይማኖት ውእቱ አላ ኑፋቄ ወከህደት አመተዋሃደ ቃለ ምስለሥጋ፣ እንዘባዕል ኮነ ነዳየ ወእመአኮ ንብሎ ነድየ እምብዕሰ ባሕርይ መለኮታዊት ወእምልደቱ ቀዳማዊት፣ አላ እምከብረ መንፈስቅዱስ ዘፀጋዎ ለአዳም አመሀሎ ውስተግነት ወእምልደቱ ቀዳማዊት ዘሰደደ አዳም በኃጢአቱ ወተቀብአ በሥጋሁ ቅብአ መንፈስ ቅዱስ ወተቀደሰ ከመሰብአ ወሚጣ ለይእቲ ልደት ወተሰምየ ባቲ ዳግማይ አዳም ውተርእየ ነገረ መናፍቃን ወፈትሑ ንቡራን ተምአ ዕውር ዘኢየሱስ ወኮነ ይዜዕሎሙ ዕውር

ዘኢየሱስ ለእለፈትሑ ቦቱ። ለአሐዱ መምህር ዘምድረሙኛ ይቤሎ የሙኛ በሬ ወለእህቱ እመምኔት ዘይብልዋ እናት በጎ ይቤላ እናት በግ /56/።

<u>አግርኖው</u> - መናፍቃኑ በድጋሚ ተንቀሳቀሱ ዓለምሰገድ የተባለ ንጉሥ ፋሲለደስ የነሱን እንቅስቃሴ ሰምቶ ጉባኤ ጠራ። የደብረሊባኖስ መምህራን ምሑራንም በጉባኤው እንዲሳተፉ አደረገ። ከደብረሊባኖስ መምህራን አንዱ የሆነ አዳም ዘእንፍራዝ ስለተዋሕዶ የምትከተሉት እምነት ምንድር ነው? ሲል ጠየቃቸው የመናፍቃኑ ሊቀ ጉባኤ የሆነው ዕውር ዘኢየሱስ ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሐደ ጊዜ ነዳየ ባሕርይ ሆነ /ከአምላክነቱ ተለየ እንደማለት/ ከብሩንም አጣ፣ መንፈስቅዱስን ሲቀባ ከበረ የባሕርይ ልጅም ሆነ ከበረም ስለተዋሕዶ ያለን እምነት ይህ ነው አለ። ጠያቂው መምህር /አዳም ዘእንፍራዝ/ ይህ ሃይማኖት አይደለም ክህደትና መናፍቅነት ነው። ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሐደ ጊዜ ከቀዳማዊ ልደቱ ከአምላካዊ ባሕርዩ ነዳይ ሆነ /ለቀቀ/ ማለት ፍጹም ክህደት ነው፤ አዳም በገነት ሳለ የተሠጠውን ፀጋ አጥፍቶታል የፀጋ ልደቱንም በኃጢአቱ አጥቶታል። ያ ከአዳም የተወሰደውን ልደት /የፀጋ/ በሥጋው በመንፈስ ቅዱስ ከብሮ /መንፈስ ቅዱስን ተቀብቶ/ እንደሰውም ተቀድሶ መልሶታል። በዚህም ዳግማይ አዳም ተብሏል። አዳም ዘእንፍራዝ ይህን አባራርቶ ባበቃ ጊዜ በፈራጅነት፣ በተመልካችነትና በአፈጉባኤነት የተቀመጡ ሁሉ እጅግ ደስ አላቸው። ገለጻውንም በደስታ ተቀበሉት። መናፍቃኑም ተረቱ።

መናፍቃኑን ወክሎ የቆመው ዕውር ዘኢየሱስ በጣም ተበሳጭቶ ስድብም ይሳደብ ጀመር። በዚህ መሠረት ምድረሙኛ ከተባለው ቦታ የመጣውን ከምሑራኑ አንዱን የሙኛ በሬ ብሎ ሰደበው፣ የዚሁ

መምህር እጎት የሆነችውንና እናት በነ በመባል የምትጠራውን እናት በግ ብሎ ሰደባት።

በነአፄ ፋሲል ዘመን የሃይማኖት ነፃነት እንደነበር ከዚሁ እንመለከታለን። አዳም ዘእንፍራዝና ዕውር ዘኢየሱስ በጉባኤው ክርክር ሲገጥሙ ዕውር ዘኢየሱስ ቅባቶች የመሠረቱትን እምነት እንፀባርቆ ሲያበቃ ለሱ በአዳምዘእንፍራዝ /57/ በተሠጠው መልስ ተቀማጮች መረታቱን ሲመሠክሩ ተበሳጭቶ ሰዎችን ዘልፏል። ይህ ሁሉ ሲሆን ንጉሡ ይመለከቱ ነበር። ነገር ግን በተሳዳቢው ግለሰብ ላይ ምንም የተወሰደ ርምጃ የለም። የመናገር ነፃነት መኖሩን ከዚሁ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚሁ የምናገኘው የቅባት ነጥብ ባጭሩ ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሕዶ ጊዜ የአምላክነትን ክብር አጣ፤ በመንፈስ ቅዱስ ከብሮ /ተቀብቶ/ አምላክ ሆነ /የአምላክነትን ክብር አገኘ/ የሚል ብቻ ነው። በዚሁ ክርክር የተነወረውና የተወገዘው የቅብዓት እምነት ብቻ ነው። ካራ፤ ጸጋ እየተባባሉ መወነጃጀል በዚሁ ፈጽሞ አልተወሳም። አፄ ፋሲል በምዕራፍ 4 እንደተገለጸው ምዕራባውያን የበከሉዋቸውን ኢትዮጵያውያን በማስተካከል ላይ ስለነበሩ በኢትዮጵያውያን መካከል ለሚፈጠረው መለያየት ምንም ትኩረት የሠጡት አይመስልም።

ለ. <u>በጻድቁ ዮሐንስ ዘመን ስለቅብዓት የተደረገ ክርክር</u>

ቅባቶች እምነቱን ከፖለቲካ ጋር በማያያዝ ከጎንደር ነገሥታት መካከል ብዙዎቹ በቁጥጥራቸው ሥር እንዲሆኑ ያደርጉ ነበር። የቅባትን እምነት ካልተከተልህ መንግሥትህ አይጸናም ረጅም ዘመን አትገዛም በማለት ነገሩ ብቃት ባላቸው ባሕታውያን እንደ ትንቢት የተነገረ

በማስመሰል ሌላውን ከፍል በኃይል እንዲያጠፉ ይገፋፉዋቸው ነበር። በጻድቁ ዮሐንስዘመን ቤተ ተክለሃይማኖትን ወክለው በአፈጉባኤነት የቀረቡት መምህር ኒቆላዎስ ሲሆኑ ቤተአዎስጣቴዎስን ወክሎ የቀረበ ደግሞ አካለክርስቶስ ይባላል። ጉባኤውን የመሩት ራሳቸው አእላፍሰገድ /ጻድቁ/ ዮሐንስ ናቸው ጳጳሱ አባሲኖዳን ዕጨጌው ቃለአዋዲም የጉባኤው ተካፋዮች ነበሩ። ቤተ ተክለሃይማኖትን ወክለው የቆሙ መምሕር ኒቆላዎስ አካለክርስቶስን ሥጋ ከቃል ጋር በተዋሐደ ጊዜ አልከበረምን? ብለው ጠየቁት አካለክርስቶስ ሥጋ ከቃል ጋር በተዋሐደ ጊዜ አልከበረም የከበረው መንፈስ ቅዱስን በተቀባ ጊዜ ነው። ብሎ መለሰ መምህር ኒቆላዎስ... ሰው የሆነው አምላክ ነው መለኮትን በመዋሐድ አምላክ የሆነው ሰው ነው ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ለምን አለ? ቢሉት ሌላ ምሥጢር አምጣ እንጂ አምላክ የሚለው ከዚህ ላይ ትርጉም የለውም አለ። መምህር ኒቆላዎስ፣ አምላክ የሚለው ቃል ትርጉም ከሌለው እግዚአብሔር ሙሴን የፈርኦን አምላክ አደርግሀለሁ ለምን አለው፣ ሐዋርው አትናቴዎስም ሥጋ ከቃል ጋር በመዋሐዱ ከብር አገኘ ብለዋል አሉ /መምሕር ኒቆላዎስ/።

በዚሁ ጉባኤ ለሁለተኛ ጊዜ የተረቱት ቅባቶች ናቸው። ጻድቁ ዮሐንስ ራሳቸው የቅባት እምነት ተከታይ እንደነበሩ በሰፊው ይነገራል ግን በጉባኤው ላይ ተጽእኖ ሲያደርጉ ታሪኩ አያመለክትም። ምናልባትም የተከተሉዋቸው ቅባቶች የሚያቀርቡት መልስ ፍሬቢስ መሆኑን ሲመለከቱ ስሕተታቸውን ተረድተው ትተውት ይሆናል። በዘመኑ የጎጃም ቅባቶች በጣም በዝተው ነበር። ከመብዛታቸውም የተነሳም ሕዝቡን አሳምነውና አስተባብረው ያስገለብጡናል እያሉ ነገሥታቱ ይሰጉ ነበር። ከሥጋታቸውም የተነሳ በቅባቶች እንዲመሩ ይገደዱ ነበር። የጻድቁ

/አእላፍሰገድ/ ዮሐንስ ቅባቶችን መደገፍና የቅባት ተከታይ መሆን ከዚሁ የተለየ ላይሆን ይችላል። ቅባቶች በጣም ቢበዙም በጻድቁ ዮሐንስ ዘመን የበላይነትን ለመያዝ ሳይችሉ ቀርተዋል።

ሐ. በአድያም ሰገድ ኢያሱ የቅባቶች ሁኔታ

አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ከተከበለኛው ትምህርተ ተዋሕዶ ፈቀቅ ያሉ ትክክለኛ ክርስቲያን ንጉሥ ነበሩ። ቅባቶች ሰለበዙ እንዲያከራክሩዋቸው የጠየቁዋቸው ቅባቶች አልነበሩም ተዋሕዶዎች ናቸው። በምዕራፍ አራት ክፍል አንድ እንደተገለጸው ጉባኤ ከጠሩ በኋላ ቸርደም በተባለው ሊቅ በተሠጠው ትምህርት ጉባኤው አብቅቶ ነበር።

ከቸርደም ትምህርትና ከጉባኤው ውሳኔ በኋላ ቅባቶች በሌለንበት ነው ጉባኤው የተካሄደው እንደገና ሁላችን የተካፈልንበት ጉባኤ ይደረግልን በማለት አመለከቱ በነሱ ጥያቄ እንደገና ጉባኤ ይደረግ ዘንድ ተፈቀደ። ቅባቶች በበኩላቸው ዳግም ጉባኤ በመፈቀዱ ደስተኞች ቢሆኑም የጉባኤው ጊዜ እንዲራዘም ፈለጉ። ለዚሁ የሠጡት ምክንያት "መጻሕፍትን መርምረንና ዝግጅታችንን አጠናቅቀን ለመቅረብ እንድን ችል" የሚል ነበር። ይሁንና አባባላቸው የተንኮል መሆኑ ታወቀ። ወድያውም ከመጀመሪያው ምን ያህል ልዩነት የሌለው ጉባኤ ተደረገና የመጀመሪያውን ጉባኤ የሚያጠናክር ሆነ የሁለተኛው ጉባኤ በተዋሕዶዎች በኩል አፈጉባኤዎች ሆነው የቀረቡት የዲማ ጊዮርጊስ ካህናት ሲሆኑ ቅባቶችን ወክለው የተሠለፉ ደግሞ የደብረመርቅ ማርያም ካህናት ነበሩ።

መ. ቅባቶች በርጉም ተክለሃይማኖት ዘመን መንግሥት

አፄ ኢያሱ በልጃቸው በርጉም ተክለሃይማኖት እጅ ተገደሉ። ለዚሁ ያበቁት ቅባቶችን ናቸው። አፄ ኢያሱ ከሀምሳ ዓመት በላይ በሕይወት አልኖሩም። ጣና ውስጥ ከሚገኙ ገዳማት በየጊዜው እየገቡ ሱባኤ ያዘወትሩ ነበር፣ በልጆችና ወንድሞች ሞትም ሐዘናቸው በርትቶ ነበር ይባላል በዚህ ሁሉ ጤንነትን የተላበሰ ሕይወት አልነበራቸውም።

ቅባቶች የርጉም ተክለሃይማኖት በሥልጣን መቀመጥ ሲያዩ ያለ ምንም ውጣ ውረድ "በቅብአተ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ሆነ" የሚለው ጎርፍተነገር የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርተ መለኮት እንዲሆን ተብሎ እዋጅ እንዲነገርላቸው ርጉም ተክለሃይማኖትን ጠየቁት እሱ ግን "ሥልጣን ላይ ለመውጣት ተባብራች ሁኖል ብዬ ያለምንም ጉባኤ ሲነገር የቆየውን ሃይማኖት በአዋጅ ብቻ መለወጥ አልችልም" የሚል መልስ ሠጣቸው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደገና እሱንም ማጥላላት ጀመሩ። ቅብዓትን በመደገፍ ላይ የነበሩ መኳንንትና መሳፍን ትም ይበሳጩ ጀመር ጉባኤ እንዲደረግ ቅብአቶች ፈቃደኞች ቢሆኑም እንኳ የተክለሃይማኖት ፍላጎት ቅብዓቶች እንዲሽነፉ እንጂ እንዲያሸንፉ አልነበረም።

በመካከሉ ምንም ጉባኤ ሳይደረግ በዘመኑ የኢትዮጵያ ጳጳስ የነበረው ግብፃዊው የቤተክርስቲያን መሪ በቅብዓት የባሕርይ አምላክ ሆነ የሚሉትን ሁሉ አውግዣለሁ አለ። ተክለሃይማኖትም ከግዝቱ አከታትሎ ዋኖ ዋናዎቹን የቅብዓት መሪዎች አሠረ። ምክንያቱም በአስተዳደር ጣልቃ እየገቡ አስቸግረውት ስለነበረ ነው። ከታሠሩት የቅብዓት

አፈጉባኤዎች መካከል አባ ወልደትንሣኤ የተባለው መሪያቸው ይገኝ ባቸዋል።

የቅብአቶች ተንኮል በዚሁ ሊገታ አልቻለም። ሌላ የተንኮል መንገድ አመጡ /58/። እሱን የሚገድሉበትን ዘዴ ሲያስፈላልጉ ክቆዩ በኋላ ጎጃም ውስጥ በአገው ምድር አደን ቢያካሂድ በቀላሉ የፈለጋቸውን አውሬዎች መግደል እንደሚችል መከሩት እሱም ይገድሉኛል ብሎ ሳይጠራጠር ተከታዮችን ወደኋላ ትቶ እሱን ለመግደል በተዘጋጁ ሰዎች ብቻ እየተመራ ጫካ ገባ በዚያውም ገደሉት።

ሠ. ቅባቶች በአፄ ቴዎፍሎስ ዘመን /1700 - 1703/

ቅባቶች ከአፄ ቴዎፍሎስ ጀምሮ በፖለቲካ የበላይነትን ይዘዋል። ቴዎፍሎስ የመንግሥትን ሥልጣን እንደተረከበ ብዙ ሳይቆይ በትብዓተ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ልጅ ሆነ የሚለውን እምነት ኢትዮጵያውን ክርስቲያን በሙሉ እንዲቀበሉ አወጀ። ተዋሕዶዎች ለምን ያለጉባኤ ይታወጅብናል ቢሉት "የጎጃም ቅባቶች ወዳጆቼ ስለሆኑ የነሱን እምነት ደግፌአለሁ" አለ። በዚሁ መጠነኛም ቢሆን የሱስንዮስ ዘመን ችግር ሊፈጠር ጀመረ። ብዙዎች አዋጁን በመቃወም ሸፈቱ። ከሃይማኖት ውጭ በሆነ የግል ፖለቲካ የሚሸፍቱም እጅግ ተበራከቱ።

በሥልጣን ተቀናቃኝነት ከሸፈቱት መካከል የፋሺስትነት ጠባይ የነበራቸው ነበሩ። ቱጂ የተባለው ሽፍታ በፋሽሽትነት ይጠቀሳል። ቱጂ ከአትሮንሰማርም ቤተክርስቲያን ገብቶ ካህናትን አርዷል። የቤተክርስቲያኑን ንዋየ ቅድሳትንም ዘርፏል። በዘመኑ ተደናቂነትን አትርፎ የነበረው ብራንክሌን የሣላትና በብዙ ሠዓሊዎች ዘንድ ግሩም

ድንቅ ትባል የነበረችው የእመቤታችን ሥዕል በእትሮንሰ ማርያም ቅጣኝ ነበር። እሷም በቱጂ ተወስዳለች።

ቴዎፍሎስ ራሱ ባበላሸው የአመራር ጉድለት ምንም እረፍት ሊያገኝ አልቻለም። ፀጥታን ለማስከበር ወድያና ወዲህ ሲሯሯጥ በወባ በሽታ ተለክፈና በሥልጣን ላይ ሦስት ዓመት ብቻ ቆይቶ ሞተ። የነገሠው በ1700 ሲሆን የሞተው 1703 ዓ.ም ነው። ቴዎፍሎስ የጻድቁ ዮሐንስ ልጅ የአድያምሠገድ ኢያሱ ወንድም ነው።

ረ. ቅብዓቶችና ሣልሳዊ ዳግት /ዘፋኙ ዳግት/

ቴዎፍሎስ ሲሞት አፄ ዮሰጦስ ሥልጣኑን ተረከቡ። አፄ ዮሰጦስ ገዳማትን የመጎብኘት ፍቅር ነበራቸው። ግብፅ ድረስ ተጉዘው የአባ እንጦንስን ገዳም ጎብኝተዋል። ብልህ መሪ ነበሩ። በዘመናቸው የሃይማኖቅ ክርክር አልተነሳም የኢትዮጵያ ሕዝብን በእጅ ሞያ ለማሠልጠን ሦስት የውጭ ዜጎችን አስመጥተው ነበር። ግን ተቀባይነትን አላገኙም። ኢትዮጵያውያን ካህናት አንድን የውጭ ዜጋ በተመለከቱ ቁጥር በሃይማኖት ብቻ ከነሱ ጋር መፋለም እንደትልቅ ባሕል ከቆጠሩት ከአንድ ምዕት ዓመት በላይ ሆኗቸዋል። በመሠረቱ አይፈረድባቸውም በሱስንዮስ ዘመን ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያውያን ለሁለት ተከፍለው ሲተላለቁ የኖሩት ኑሮች ባመጡት መዘዝ ነውና።

የውጭ ዜጎቹ ሦስት ሲሆኑ አንዱ ጀመርናዊ ሁለቱ ሮማውያን ነበሩ። በሳንደር ከተማ ከተቀመጡ ካህናቱ ሃይማኖታቸውን በመጠየቅ ነገር ይቀሰቅሱብኛል ብለው ስለሰጉ አባ ጎርጎርዮስ የተባሉ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ባልደረባ እንዲሆኑዋቸው መድበው በወልቃይት እንዲቀመጡ አደረጉ። ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ወደኢየሩሳሌም የመመላለስ ልምድ

ሸለክበራቸው በዚያው አልፈው እስከ አውሮፖ በመዝለት የውጭ ቋንቋ እያጠኑ ይመለሱ ስለነበር የውጭ እንግዶች ሲመጡ መነኮሳቱ ባስተርጓሚነትና በባልደረባነት ያገለግሉ ነበር። ይህ ልምድ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ጀምሮ የተለመደ እንደነበር ካለፉት ምዕራፎች በየአጋጣሚው መገለጹ ይታወሳል። የጥንታውያን ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ውለታ ብዙ ነው፣ የውጭ አገር የታሪክ ተመራማሪዎች ኢትዮጵያ ከግብፅ ቀጥላ የብዙ ታሪክ ባለቤት መሆንዋን እንዲረዱ ያደርጉ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ናቸው። ከሩስያ ቤተክርስቲያንና መንግሥት ጋር ኢትዮጵያ ግንኙነት እንድትመሠርት ያደረገ ኢየሩሳሌም፣ ይኖር የነበረ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ እንደነበር ሩስያውያን ራሳቸው ይናገራሉ።

የአባ ጎርጎርዮስ ለውጭ ዜጎች በባልደረባነት መመደብ ክቢሙ ልምድ የቀነሳ ነው። አፄ ዮሰጣስ አራት ዓመት ከአራት ወር ብቻ በሥልጣን ቆይተው ሞቱ። በእሳቸው እግር የተተካው ሣልሣዊ /ዘፋኝ/ ዳዊት ነው። የመሪነቱን ሥልጣን ተረክበ ብዙ ሳይቆይ የውጭ ዜጎች በወልቃይት መኖር ተነገረው። ይህን የነገሩት የደብረሊባኖስ ካህናት አባ መዝሙር በተባሉ መነኩሴ መሪነት ከቤተመንግሥቱ ድረስ በመሄድ ነው። የውጭ ዜጎቹ ተጠርተው ወደጎንደር እንዲመጡ ተደረገና እምነታቸው ምን እንደሆነ ተጠየቁ። እነሱም የኬልቄዶንን እምነት እንደሚከተሉ ተናገሩ። እነሱን ለመጠየቅ የተሰየመ ጉባኤ እንዲገደሉ ወሰኑና ወደቆላማ ሥፍራ ተወስደው ተገደሉ። በባልደረባነትና ባስተርጓሚነት ከነሱ ጋር የተገኙት አባ ጎርጎርዮስም አብረው እንዲገደሉ ጉባኤው ወሰኖ ነበር። መነኩሴው ግን ቋንቋ በማወቃቸው በባልደረባነት የውጭ ዜጎቹን እንዲረዱ አፄ ዮሰጣስ ስለመደቧቸው

አብረው ከመገኘታቸው በቀር ከተዋሕዶ ሃይማኖት ያልወጡ መሆናቸውን ገልጸው ለአፄ ዳዊት አቤት ስላሉ ከመገደል ዳኑ። በፈረንጆቹ መገደል እጅግ ቅር የተሰኙ ኢትዮጵያውያን በዘመኑ እንደነበሩ ይነገራል። "ከሀገር አስወጥቶ ወደሀገራቸው ማባረር ይበቃ ነበር። ግድያው ምን አመጣው" ባዮች ናቸው።

ዘፋኝ ዳዊት /ሣልሣዊ/ በፈረንጆቹ ደም የማፍሰሱ ተግባር አንድ ብሎ መጀመሩ ነበር። አባ ከርስቶዶሱን የመሰለ ባንድ ራስ ሁለት ምላስ የሆነ ጳጳስ ለሱ የደም አፍሳሽነት ዓላማ ተጨማሪ ምክንያት ሆነለት። ቅባቶች ከተዋሕዶዎች ጋር እንዲያከራክራቸው ንጉሡን ሲጠይቁት ጉባኤ ሳይጠራ ስለምሥጢረ ሥጋዌ ምን እንደሚል አባ ከርስቶዶሱን እንዲጠይቁት አዘዛቸው። እነሱም አባ ከርስቶዶሱን ጠየቁት። እሱ ግን ቅባቶች መሆናቸውን አውቆ እንዳይጣሉት በመፍራት "ሃይማኖቴ እንደአበቶቼ አባ ቢኖዳና አባ ማርቆስ ነው አላቸው" ቅባቶች ምንም ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ ሳይጠይቁት አንዲን ዓርፍተነገር ብቻ አንጠልጥለው ወደንጉሡ ሄዱና ይህንኑ ነገሩት ንጉሡ ዳዊት አብረውት የተገኙትን መኳንንትና ካህናት የነአባ ቢኖዳ ሃይማኖት ምን ነበር? ብሎ ቢጠይቃቸው በትብአት የባሕርይ ልጅ ማለት ነው ብለው መለሱለት። እሱም ሕዝቡ በትብአት የባሕርይ ልጅ የሚለውን እምነት እንዲቀበል አወጀ። ቤትወደድ ዘጊዮርጊስ የሚባል ከንጉሡ መኳንንት የትብአትን እምነት በአከራሪነት ደረጃ የሚከተል ነበር። አባ ከርስቶዶሱ እሱን ስለሚፈራ ለተጠየቀው ጥያቄ ግራ የሚያጋባ መልስ እንደሰጠ ይተረካል። ተዋሕዶዎች ከደብረሊባኖስ ዕጩ ጋር በመሆን በበኩላቸው አባ ከርስቶዶሱ ዘንድ ሄደው የሚከተለውን እምነት ቢጠይቁት ከቅባት

ተከታዮች መካከል ማንም እንደሌለ ተረድቶ "ክርስቶስ በተዋሕዶ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ነው በመቀባቱ ግን መሲህ ነው ብዬ አምናለሁ" አለ /59/።

ደብረሊባኖሶችና መሰሎቻቸው በአባ ክርስቶዶሉ አባባል ተደስተው ሊመለሱ ጀዊ በመባል የሚታወቁትን አረማውያን ልከው ንጉሡና ቢትወደዱ አስፈጅዋቸው። ንጉሡ /ሣልሣዊ ዳዊት/ ከልቡ ቅባትን የሚደግፍ አልነበረም ይባላል። የብሕትውና ብቃት ያላቸው በመምሰል አታላዮች የቅባትን ሃይማኖት ብትከተል ፬ /አርባ/ ዓመት ሙሉ በንጉሥነት ትቀመጣለህ በማለት ስለታለሉት የቅባቶችን ፍላጎት ለማሟላት መገደዱ ይነገራል። ግን በሥልጣን ላይ የቆየው ከሰድስት ዓመት ላነሰ ጊዜ ነው። ሣልሣዊ ዳዊት ስለፈጸመው ታሪክ የሚገልጽ አጭር የግእዝ ጽሑፍ ቀሞሉ ይኸበላል። ...ነግሠ ዳዊት ወልደኢያሱ ኀምስተ ዓመተ ወተሰዓተ አውራሐ ወተንሥኡ በዘመኑ መናፍቃን እንዘይብሉ በቅብአት ወልደባሕርይ። ወመጽኡ ኀበትፅይንት እስተብዱ በመንግሥተ አቡሁ ኢያሱ ንጉሥ ወተወከፈ ነገሮሙ ወሐነፀ ሎሙ ቤተክርስቲያን በስሙ ለአባ ኤምስጣቄዎስ በመካነ ደብረሊባኖስ አስደ አዋዴ እንዘይብል ሃይማኖትየ በቅብአት ወልደ ባሕርይ ወኪነ ዓቢይ ሁከት በውስተኩሉ ብሔር ተጋብኡ ሰብአ ደብረሊባኖስ ወመጽኡ ብዙሐን መምህራን ካህናት ወመነኮሳት እምአዘዞ ወደቤልዎ ለንጉሥ ሐበነ ጉባኤ መወሀበሙ ወተዋሥኡ ምስለእሉ መናፍቃን ወምእመሙ በነገር ወበመጽሐፍ ሰብአአዘዞ ወሶበኢኮነ ሎሙ ይቤሉ በሃይማኖተ ጳጳስነ ነአምን፣ ወሐሩ ዉስተቤተ ጳጳስ አቡነ ክርስቶዶሉ ወይቤሎሙ ሃይማኖተ እስክንድርያ በተዋሕዶ ወልደ ባሕርይ ወበቅብአት መሢሕ ወበኩር፣ አነሂ ከመዝ አአምን። ወለሚያሙ ዘንተ ካህናት ወጽኡ

በፍሥሐ ወጠኑ በዜማ እንዘይበሉ ንሴብሐ ለእግዚአብሔር ሰቡሐ ዘተሰብሐ ወእንዘየሐልፉ በዓደባባይ ወስተ ቤተ ዕጪ ሲቆሙ ከመይባኡ ሶበ ርእዩ እሉ መናፍቃን ተሐፍሩ ወቀንኡ ወነዱ ወእንሥኡ ፀብአ ወገርምሙ ወቀተልምሙ ወሰደድምሙ ወዓሊያኒሁ ለቢትወደድ ዘጊዮር ጊስ ጀዊ ወዳሞት በዛቲ ዕለት ሞቱ ብዙኃን ካህናት ወመነኮሳት ዘየብስ ወደሰያት ምስለአባ ኒቆሊዎስ፣ወቄስ አፄ አውስግንዮስ ወከኑ ሰማዕተ ወበዉእቱ መዋዕል ሐመ ንጉሥ ወሞተ አመአሥሩ ወሰንዩ ለግንባት በዕለተ ፍልሰቱ ለአቡነ ተክለይማኖት ወቦአ ረበሐሙ ለእሙንቱ መነኮሳት" /60/።

አግርኖ ...የኢያሱ ልጅ ዳዊት አምስት ዓመት ከዘጠኝ ወር ነገሠ። በቅብአት የባሕርይ ልጅ የሚሉ መናፍቃን በዘመኑ ተነሱ። እነዚህ መናፍቃን በአባቱ በኢያሱ ዘመን ተሰደዉ ነበር። ንጉሡ ዳዊት አቀባበል አደረገላቸው። የደብረሊባኖስ ይዞታ በሆነው ቦታም በአባ አዎስጣቴዎስ ስም ቤተክርስቲያንን ሠራላቸው። ሃይማኖቴ በቅብአት ወልደባሕርይ ግለት ነው ብሎ አዋጅ አስነገረ በዚሁም በአገር ሁሉ ሁክት ተነሳ። የደብረሊባኖስ ሰዎች መምሕራን መነኮሳት ከአዘዞ መጥተው ንጉሡን ጉባኤ ይክፈትልን አሉት። እሱም ጉባኤ ከፈተላቸውና ከመናፍቃኑ ጋር ክርክር ገጠሙ። በንግግርና በመጽሐፍም ቅባቶቹን አሸነፏቸው። በጳጳሳቸን ሃይማኖት እናምናለን በማለትም ወደ ጳጳሱ ቤት ሄዱ እሱም የኤስክንድርያ ሃይማኖት በተዋሕዶ ወልደባሕርይ በቅባት መሲሕና በኩር ግለት ነው። እኔም የማምነው ይኸው ነው አለ። ካህናቱ የጳጳሱን ምሥክርነት ሰምተው በደስታ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን በማለት እየዘመሩ ወደ አለቃቸው ዕጪጌ ቤት ለመግባት በአደባባዩ በግለፍ ላይ እያሉ እነዚያ መናፍቃን በቅንዓት ተነሳስተው ሁከት አነሱባቸው

ደበደቡዋቸው፤ የቢትወደድ ዘጊዮርጊስ አሽከሮች የሆኑትን ነገደጸዊና ነገደዳሞትን ልከው አስፈጹዋቸው። በዚሁ ዕለት ብዙ ካህናት፣ መምህራንና መነኰሳት ሞቱ። ከነሱ ውስጥ አባ ኒቆላዎስና አፄ አውስግንዮስ ይታወቃሉ። ንጉሡ ጻዊት ግንቦት 12 ቀን ሞቱ።

ስለአባ ኪርስቶዶሱ አባባል በአባ ወልደሥላሴ ጽሑፍ ከተገለጸው በቢትወደድ ዘጊዮርጊስ የሚደገፉ ትባቶች እምነቱ ምን እንደሆነ በጠየቁት ጊዜ አባ ኪርስቶዶሱ ሰማዕታዊ ሞትን መልሰ "እምነቴ እንደቀድሞ አባቶቼ ነው" ያለው አባ ወልደሥላሴ አልመዘገቡትም። በሌላ አቀራረቡ ግን የሊቁ አባ ወልደሥላሴ ጽሑፍ ግሩም ምሥጢርን ያዘለ ትምህርት ነው። የጥንት ኢትዮጵያውያን መነኰሳት ከቅድስናቸው፤ መልክም ሥነ ምግባራቸውና ሐዋርያነታቸው በተጨማሪ ይህ ቀረሀ የማይባል የማሥጢረ መጻሕፍት ሊቃውንት እንደነበሩ ከአባ ወልደሥላሴ ጽሑፍ መረዳት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምህራን ተበታትነው በመኖራቸው ላስከፈ ችግር እየተጋለጡ ኖረዋል። አንድ ሁሉን የሚያስተባብር አማካይ ቦታ ቢኖራቸው ኑሮ ለአንዳንድ አስመሳዮች ትባልኡሪነት እየተጋለጡ በመካከላቸው መለያየት እየተፈጠረ መለያየቱ ደግሞ ውጪ ፖለቲካ እየተለወጠ ሞያቸውና እውቀታቸው ባልባሌነት ደረጃ ሊውደ አይችልም ነበር። የአቀራረብ ዘዴ ያጥርባቸው እንደሆን ነው እንጂ በአመሥጥሮ መጻሕፍት የሚስተካከላቸው አልነበረም። ነገር ግን ከሊቃውንቱ መካከል ብዙዎቹ መተዳደሪያቸው የሚደገሚላቸው ሲባተሉለት ሞያ ለሌላ የማስተላለፍ እድል ሲመጣላቸው ደረጃ ሲያደራሱ እውቀታቸው የትም ባክኖ ቀርቷል።

በ17ኛው ክፍለ ዘመን የምሥጢረ መጻሕፍት መምህራን በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተነሳስተው ነበር፤ ነገር ግን የመንፈስ እረፍት አግኝተው የተሠጣቸውን መንፈላዊ ሀብት ለትውልድ ለማስተላለፍ አልታደሉም፤ ነገሥታቱን እያሳሳቱና ሰም እየሰጡ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን እንዳያገኙ የሚያደርጉ ግለሰቦች ፋታ ነስዋቸው። ደብረሊባኖስ ለጎንደር ርቀት ስላለው ይመስላል የደብረሊባኖስን ገዳም የሚወክል ደብር በ17ኛው ክፍለ ዘመን በጎንደር አቅራቢያ የተመሠረተው ይህም አዘዘ ተከለሃይማኖት ነው።

ደብረሊባኖስ የብዙ ሊቃውንት ማዕከል ሆና ከመኖርዋ በላይም የደብረሊባኖስ መምህራን አንድ ነበሩ። በመካከላቸው መለያየት አልነበረም። ደብረሊባኖሶች የሌሉበት የቤተክርስቲያን ጉባኤ መካሄድ እንደሌለበት የጎንደር ነገሥታት ስለተረዱ በነሱ የሚመራ ደብር አዘዘ ተከለሃይማኖትን ተከሉላቸው። አዘዞዎችና ደብረሊባኖሶች በአንድ ተጠቃለው ቤተ ተከለሃይማኖት በመባል ይጠቀሳሉ። ቤተ ተከለ ሃይማኖቶች ከ17ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ስለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሕልውና ብዙ ተጋድሎ አድርገዋል።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምህራን ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በቤተመንግሥትም ብዙ አገልግሎት አበርክተዋል። ለመንግሥት አገልግሎት የሚመደቡት ለፍርድ አሠጣጥ ብቻ ነው፤ ልዩ ተሠጥዎ ያላቸውና ፍርሐተ እግዚአብሔር ያደረባቸው ሊቃውንት ለዚሁ ይመደቡ ነበር። የሊቃውንቱ ጉልህ አገልግሎት ከአፄ ኢያሱ ዘመን ይታያል። የጎንደር ከተማ ከ1626 - 1845 ለሁለት መቶ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ያህል የኢትዮጵያ ርዕሰ ከተማ በመሆን ቆይታለች። ከዚሁ በሂደት ብዙ ነገሮች ተከሥተዋል።

የቅዱሳት መጻሕፍት በአማርኛ ቋንቋ መተርጎም ከተከሰቱት ነገሮች አንዱና ዋነኛው ነው። የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም መሠረት ያደረጉ ሌሎች መንፈሳውያን ሥራዎችም ተከናውነዋል። በነአዛዥ ጌራና አዛዥ ራጉኤል የተጀመረው የዜማ መስተካከልም ከፍተኛ ሥፍራ የያዘው ብዚሁ ዘመን ነው። በዚሁ መራሒ ከፍለማርያም ለምሳሌነት ይጠቀሳል። ይህ የዜማ ባለሞያ ተወላጅነቱ ሸዋ ውስጥ ደብረሊባኖስ አካባቢ ነው። ድጓን በመልክ በመልኩ ቀደም ተከተሉን አስተካክሎ በ1678 ዓ.ም ለቤተክርስቲያን አስረክቧል /61/። የጥንት የድጓ መምህራን ይሰጣቸው የነበረ የማዕረግ ስም ከሞያቸው በተያያዘ ሁኔታ "መራሒ" የሚል ነበር። በ19ኛው ክፍለ ዘመን ይህ ስም አልቀረም ነበር። የቤተልሔሙ የድጓ ምሥክር መራሒ ኤስድሮስ ይባሉ እንደነበር ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ /62/።

የሐምሌ ሥላሴ መክበር የጀመረው በእፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመነ መንግሥት ነውና ለዚሁ ከብረ በዓል ለምሥጢረ ሥላሴ ትልቅ የምሥጢር አስተዋጽኦ ያለው ልዩ ዋዜማ በሊቃውንቱ ተዘጋጅቷል /63/። መልከአ ሥላሴ የተባለውና እያንዳንዱ እየተወሰደ ክዓመት እስከ ዓመት ባሉት ክብረ በዓላት በማሕሌቱ መግቢያ ላይ እየገባ ለምሥጋና ሲቀርብ የሚኖረውና የተደረሰውም በዘመነ ጎንደር ሲሆን የተደረሰበት ዐታም የጎንደሩ ደብረብርሃን ሥላሴ ነው /64/።

በ17ኛው ክፍለ ዘመን ምንኩስናን ከሊቅነት ጋር አስተባብረው የያዙ ብዙ መምህራን በየገጠሩ እየሄዱ በመቃብር ቤት በመቀመጥ ሕግናቱን ፊደል እያስቆጠሩ ይቀመጡ ነበር፤ ለዚሁ የሚያበቃቸው የጭቅጭቁና የመለያየቱ ሁኔታ ወደቀቢፀ ተስፋ እንዳይገፋፋቸው

ስለሚሰጉ ነው። አባ ኪራኮስ የተባሉ የቤተክርስቲያን ምሑር ከነሱ አንዱ ናቸው።

አባ ኪራኮስ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የኖሩ ሲሆን የ4ቱ ጉባኤያት ምሑር ከመሆናቸውም ሌላ ጽሕፈትን፣ ድጉሰንና ሥዕልን ይችሉ ነበር። ለሥጋዊ ጥቅም የተሰለፉ ሰዎች አላሠራ ስላሉዋቸው ዓለምን ንቀው ዳዉንት ውስጥ ድባማርያም ከምትባል ቤተክርስቲያን መቃብር ቤት ውስጥ ዘግተው ሕግናትን ፊደል እያስቆጠሩ ይኖሩ ነበር። አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ የተባሉት የ17ኛው ክፍለ ዘመን ጻድቅ ፊደል ቆጥረው እስከ መጻሕፍት ትርጓሜ ድረስ ከአባ ኪራኮስ ተምረዋል /65/።

የግርጌ ማስታወሻ

1. ዜና ግርቆስ በ140 ዓመታቸው /ዕድሜያቸው/ ታኅሣሥ 3 ቀን ዓረፉ ዜና ቤተክርስቲያን 2ኛ ዓመት ቁ. 14
2. ዜና ቤተክርስቲያን ዘኢትዮጵያ 1ኛ ዓመት ቁ. 3 1938
3. ሕሩይ ወልደ ሥላሴ ዋዜማ ገጽ 44
4. ዘድንግል የአቤቶ ልሣነክርስቶስ ልጅ ነው
5. ተክለጻድቅ መኩርያ ገፅ 127 ልብነድንግል - ቴዎድሮስ
6. ዋዜማ ሕሩይ ወልደ ሥላሴ ገጽ 110
7. ሥርግው ሐብለ ለሥላሴ አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁ.9 ገጽ 127
8. ሕሩይ ወልደ ሥላሴ ዋዜማ ገጽ 34
9. የአባ እንባቆም ገድል ባለ 35 ቅጠል
10. EMML: 7013 ቅጠል 140[r]
11. ተክለጻድቅ መኩሪያ ልብነድንግል - ቴዎድሮስ ገጽ 134
12. ገድለ ወለተጴጥሮስ የብራና ጽሑፍ
13. መዝሙረ ዳዊት ም2+7
14. ከፍል ሁለት ክርስትና በኢትዮጵያ ገብረዮሐንስ ገብረማርያም ነሐሴ 1991 ዓ.ም ገጽ 113 አዲስ አበባ
15. የጥንት ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ለይምሰል ማዕከላዊ ቤተመንግሥት ቢኖራቸውም ኢትዮጵያን አስከብረው ለመኖር የቻሉት ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ነው ባንዱ አካባቢ ሁለት ወር ሦስት ወርና ከዚያም በላይ በሄዱበት ይቆዩ ነበር። አብረው የሚንቀሳቀሱ ካህናት በተንቀሳቃሽ ድንኳን የተሟላ መንፈሳዊ አገልግሎት ያካሄዱላቸው ነበር። ታቦት ከነሙሉ የመንፈሳዊ አገልግሎት ንዋየቅዱሳት ጋር ከነገሥታቱ አይለዩም አምልኮተ እግዚአብሔርን በድንኳን ስለሆነ የሚፈጽሙ ካህናቱ ካህናተ ደብተራ ይባሉ ነበር። አንዳንድ አንብበው ያልተረዱ ሰዎች አባባሉን ለብሉዩ ዘመን ይሰጡታል።
16. በቤተክህነት የሚገኘው መጽሐፈ ብርሃን በአፄ ዘርአያዕቆብ እንደተዘጋጀ ራሱ ይገልጻል። ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ክርክር ግን ምንም አልመዘገበም በጽሑፉ ያሰፈርኩት አቶ ታደሰ ምሕረቱ ካዘጋጁት የታይፕ ጽሑፍ ላይ ከገጽ 126 - 131 ድረስ ያገኘሁትን ነው። አቶ ታደሰ መጽሐፈ ብርሃን ከሚባል መጽሐፍ ይህን ግግኘታቸውን በጽሑፋቸው አረጋግጠዋል።
17. በዶግማ ከኛ ጋር አንድ መሆናቸው የሚነገርላቸው አርመኖች ሞኖፊዝነትን አጥብቀው ይታወሙታል ራሴ የጎርመንን ቄስ ሰለዚሁ ጠይቄው ቃሉ ፍፁም የመናፍቃን ቃል ነው አንቀበለውም ብሎኛል። ሞኖ አንድ ፊዚዝ ገጽ ግለት እንደሆነ ብቻ ሰዎች ያውቁታል። ሚቹ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሞኖፊዚቶች ነን የኛ ሞኖፊዚትነት ግን አንደ ብሉይ ኪዳን ሳይሆን እንደ አዲስ ኪዳን ነው ብለዋል። በፊሎዞፊ መንገድ ራሱ የቻለ አገላለጽ ሊኖረው ይችላል።
18. ሥርግው ሐ.ሥ አማ.የቤ.ክ መ.ታ 110 ገጽ 64
19. አፄ ኢዮአስ /ኢየሱስ ሞአ/ ከ1747 - 1764 ነበሩ።
20. ካይላሚዳ የተባለበት ምክንያት ዙርያው የፈላሾች /የአይሁድ/ እምነት ተከታዮች የሠፈሩበት ስለነበር ነው።
21. በአፄ ምኒልክ ለመለ የትግራይ ካህናት የተላከው ጽሑፍ በቄሰገበዝ ተክለሃይማኖት እጅ እንደተገኘና ቀጂው ከቄሰገበዝ ተክለሃይማኖት እንደተላከላቸው አቶ ታደሰ ምሕረቱ ባዘጋጁት የታይፕ ጽሑፍ /ስለቅባት... የተዘጋጀ ጽሑፍ/ ገጽ 80 ያስረዳሉ።
22. አቶ ታደሰ ምሕረቱ መልእክ ብርሃናት አድማሱ ጀምበሬ በቃል ነገሩኝ ብለው በ1907 ዓ.ም በጥቅምት ወር ጉባኤው መካሄዱን ገልጸዋል። ዶክተር ሥርግው ብበኩላቸው ወሩን ሳይጠቅሱ 1905 ዓ.ም መካሄዱን መዝግበዋል /ሥ.ሐ አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር ገጽ 58/
23. ተክለጻድቅ መኩርያ አፄ ቴዎድሮስ አፄ ኃይለሥላሴ ገጽ 154
24. አቶ ተክለጻድቅ መኩርያ አፄ ቴዎድሮስ አፄ ኃይለሥላሴ ገጽ 83
25. ሥርግው ሐብለ ሥላሴ አማርኛ የቤ.ክ መዝገበ ቃላት ቁጥር 6 ገጽ 59
26. ከብላታ መርስኤሐዘን ወልደቂርቆስ የተጻፈ የእጅ ጽሑፍ
27. ካህናቱ የሃይማኖት መለያየትን እያመነጩ የሃይማኖት ጦርነት ያስነሱ ነበር። የአድባራቱ ካህናት እየራሳቸው መወነጃጀል መነቃቀፍ የዘወትር ተግባራቸው ሆኖ ነበር።
28. አባ ክርስቶዶሉ በወላዋይነቱ የአዘዘ ሊቃውንት በአፄ /ዘፋኙ/ ዳዊት አስጨፍጭፈዋል፣ ሣልስ ሰላማ፣ አፄ ቴዎድሮስን ገፋፍቶ የአንኮበርን ክርስቲያን አስፈጅተዋል።
29. ይህን ባሕል ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኑሮ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የስዩሎጂ ምሁራን ይናገራሉ።
30. መምህር አካለወልድ ኑሮዋቸው በብሕትውና ሆኖ በጎጃም፣ በጎንደር በትግራይ፣ በሸዋና በወሎ ጉባኤ እየተከሉ አስተምረዋል። በደሴ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክርስቲያን የተተከለው በሳቸው ነው። በአፄ ዮሐንስ አማካይነት በበሩ ሚዳና በሌላም ስለተካሄደው ያላስፈላጊ ጉዳይ ግን ደካማ ጎን እንዳሳዩ በሐሜት ደረጃ ይነገራላቸዋል። ስለመምህር ግርማ ታሪክ ግን ሰፋ ባለመልኩ ለማግኘት አልተቻለም። ገብረሥላሴ ዘመነ ታሪክ ዘዳግማዊ ምኒልክ የሚለውን መጽሐፍ ዋቢ በማድረግ መምህር ግርማ የአፄ ዮሐንስ ንስሐ አባት እንደነበሩና ከአክሱም ወደሸዋ በመመለስ ሁለቱን ነገሥታት ለማስታረቅ የሸዋንም የቤተክርስቲያን መምህራን ስላስተባበሩ በታሪክ ከፍተኛ ቦታ እንዳላቸው ዶክተር ሥርግው ገልጸዋል። /ሥር.ሐ.አግ.የቤ.መ.ቁ.6 ገጽ 120/
31. ይህን ጽሑፍ አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ ከተባሉ የመምህር አካለወልድ ዘመድ ግግኘታቸውን አቶ ታደሰ ምሕረቱ በጎትመት ላይ ባለዋ የታይፕ ጽሑፋቸው ገልጸዋል የአቶ ታደሰ ምሕረቱ ስለቅብዓት፣ ጸጋና ካራ ታሪካዊ አመጣጥ የሚገለጽ ጽሑፍ ነው።
32. E.Ullendo RFF.The Ethiopians (London, 1960. P.10-11)

33. ተክለጻድቅ መኩርያ ልብነድንግል ቴዎድሮስ ገጽ በ76
34. በዚህ መጽሐፍ ገጽ 77
35. ተክለኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ የእጅ ጽሑፍ
36. ሥርግው ሐብለሥላሴ አማርኛ የቤተክ መዝ. ቁ.12 ገጽ 46
37. የሱስንዮስ እናት ወይዘሮ ሐመልማል ይባላሉ። ባንድ በኩል አባታቸው በዘመነ ገላውዴዎስ ከመጡ የፖርቱጋል ወታደሮች አንዱ እንደሆነ ሲነገር በሌላ በኩል ደግሞ የወግዳው ባለበት የሕርያቆስ ልጅ መሆናቸው ይተረካል መርስኢሐዘን ወልደቂርቆስ መጽሐፈ ሰዋሰው ገጽ 30
38. ጻድቁ ዮሐንስ ከ1600 - 1674 ድረስ ነበር ጻድቅ ሊባል የቻለው ዮሐንስ የቤቱን ወጭ በግብር ከሚሸሰበው ሳይሆን መጻሕፍት ጽፎ ሰሌን ሠርቶ ከሚያገኘው የሽያጭ ገቢ ይሸፍን ስለነበር ነው።
39. መተርጎም ማለት ካንዱ ቋንቋ ወደ አንዱ ቋንቋ ተተረጎመ ማለት አይደለም በመጽሐፉ ላይ ያለው ኃይለቃል በቀላሉ ለሕዝብ በሚረዳ መንገድ ተተነተነ ተብራራ ምሥጢሩ ግልጽ እንዲሆን ተደረገ ማለት ነው። የትርጉም ጉዳይ በአማርኛ ቋንቋ አልፎ አልፎ በግእዝም ሳይቀር ብዙ ግራ እንዳጋባ ይኖራል። አንድ ጽሑፍ ካንድ ቋንቋ ወደአንድ ቋንቋ ተገለበጠ ለማለት "ተተረጎመ" ሲል ይገኛል ይህ ያልተስተካከለ ግዕዝ ነው።
40. አቡነ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ በሚል መጽሐፋቸው ይህንን ገልጸዋል ሌሎችም አባባሉን እየደገፉ ጽፈዋል።
41. ፊሊጵስዮስ 26 /ክርስቶስ ኮነ ሰብአ ከማነ/
42. Guidi Annales Iohannis Iyasue IET Baka FFa Page 63
43. ታደሰ ምሕረቴ ቅባትና ጸጋ የታይኘ ጽሑ ገጽ 24
44. የክርስቶስ በኩረ ምእመናንነትን በሚያብራሩበት ጊዜ ምንም ያልዘገባው /ጉንጭ አልፋው ተማሪ/ ይህማ ጸጋ ማለትም ነው/ እያለ ሲጨቀጭቃቸው ዓቃቤ ሰዓት ከፍቴ አም ስላሉት ጸጋ የሃይማኖት ስም ሆኖ ቀረ ይላሉ አንዳንድ ሊቃውንት
45. አለቃ አዘዘ ተድላ ነገረ ሃይማኖት የእጅ ጽሑፍ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተመጻሕፍት።
46. ግብረ ሐዋርያት 2÷36
47. አለቃ አዘዘ ተድላ ነገረ ሃይማኖት የእጅ ጽሑፍ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተ መጻሕፍት አዲስ አበባ
48. ታደሰ ምሕረቴ ስለፀጋ ቅባትና ካራ የተጻፈ የታይኘ ጽሑፍ ገጽ 40
49. ተወላጅነታቸው ሽዋ የሆኑ የጎንደር ምሑር አለቃ ኃብተሥላሴ በደጃች ውቤ ተልከው ከግብፅ አባ ሰላማን አመጡ ደጃች ውቤ አባ ሰላማን ሰራስ ዓሊ አስረከቡ በሽዋ ሊቃውንት ከጎንደር ሲባረሩ ከራስ ዓሊ ተለዩ እንደገና ወደደች ውቤ ሄዱ /ወደሰሜን/ ደጃች ውቤ መኖርያቸው ሰሜን ሆኖ ትግራይን ያስተዳድሩ ነበር። አባ ሰላማ የአፄ ቴዎድሮስን ብርታት ሲያዩ ተማርኮ ከመወሰድ ከወዲሁ ልግባ ብለው ወደአፄ ቴዎድሮስ ገቡ ቂማቸውን ለመወጣት አፄ ቴዎድሮስን አሳስተው የሸዋን ሊቃውንት አስፈጅተዋል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በቀዳማዊ ሰላማ ትመሠረታለች፣ በካልኣ ሰላማ ትስፋፋለች በሳልስ ሰላማ ትመነምናለች የሚል ንግርት ከጥንት ጀምሮ እንደነበር ገልጸው ጽፈዋል።
50. ፀሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን ጠቅሰው ዶክተር ሥርግው ሐብለሥላሴ ገልጸውታል ሥርግው ሐብለሥላሴ /ዶክተር/ አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁ.7 ገጽ 135
51. ዋዜማ ሕሩይ ወልደሥላሴ 1921 ዓሕጽባሕ ማተሚያ ቤት ገጽ 110
52. ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ገጽ 87 - 89
53. ይህ አንደኛው ክፍል ወደፍጹም ክህደት የሚከት ነው። በምንም መልኩ ተቀባይነት አይኖረውም።
54. ሦስተኛውን ክፍል ያመነጩት በቴዎድሮስ ዘመን የነበሩ እነአለቃ ጎሹ እንደሆኑ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው በተባለው መጽሐፋቸው ገልጸዋል /ኪዳነወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግሥ ገጽ 780/
55. ተክለጻድቅ መኩርያ አፄ ልብነድንግል - አፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ታሪክ ገጽ 148
56. አባ ወልደሥላሴ ነገረአሜን፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ሁለተኛው ደብተር ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት
57. እንፍራዝ ከጎንደር በስተደቡብ የምትገኝ ቦታ ናት። ብዙ መምህራን ከዚች ቀበሌ እንደወጡ ይነገራል። ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር የተያያዘ ከፍተኛ ታሪክም አላት። በአፄ ቴዎድሮስ የተተከለ ደብር በዚችው ይገኛል።
58. ተክለጻድቅ መኩሪያ አፄ ልብነድንግል - ቴዎድሮስ 1953፣ ገጽ 321 /አ.አ/
59. ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ ነው ስለዚህ ክርስቶስ በተዋሕዶ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ በመቀባቱ መሲህ ነው የሚሉት ጸጎች እየተባሉ ተነቅፈዋል።
60. አባ ወልደሥላሴ ነገረአሜን የኢትዮጵያ ታሪክ 22ኛው ደብተር የእጅ ጽሑፍ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት
61. EMML 5497 ቅጠል 3r
62. ትንሣኤ መጽሔት ቁ65/1975 ዓ.ም
63. የሐምሌ ሥላሴ ዋዜማ የኋላ ድርሰት ነው
64. የመጀመሪያው ደብረብርሃን ሥላሴ የሸዋው ሲሆን ሁለተኛው የጎንደር፣ ሦስተኛው የዓድዋ ናቸው። ደብረብርሃን ሥላሴ የተባሉ አድባራት ሁሉ መልአከ ብርሃናት የሚል አለቃ ይሾሙላቸዋል።
65. ተክለሃይማኖት 17ኛው ዓመት ቀን 15/1955 ዓ.ም